አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3584 | ቅዳሜ ሐምሌ 25 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር


## ኢትዮጵያ እየመከረች ነው

# ከተፈጥሮ የተወዳጀች ከተማ

- የፊታችን ሰኞ እንደ ሀገር 800 ሚሊዮን ፣ በአዲስ አበባ አንድ ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል



3

ግራፊክስ - በእዮብ ተፈራ

አዲስ አበባን ከተፈጥሮ የተስማማች ፣ ዛሬንና ነገንም ታሳቢ ያደረገች ከተማ ለማድረግ የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል

## አደጋን ለመከላከል የተዘረጉት የበጎነት እጆች



8

ፎቶ፡- ለይላ መሀመድ

የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎች በትራፊክ ማስተናበር ስራ ላይ

## መጽሐፍት በሲኒማ ስክሪን




11

ፎቶ- ከገፀ ድር

ወደ ፊልም ከተቀየሩ መጽሐፍት መካከል ጥቂቶቹ

## የስፖርት ማዘውተሪያዎቹ በዘመናዊው መንገድ




20

ፎቶ- ኤ አይ ጄሚናይ

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አገልግሎት አሰጣጥ በኦንላይን በመተካቱ ለስፖርቱ አፍቃሪያን እፎይታን ሰጥቷል

# ለጋራ ህመማችን መድኃኒት የሚቀመምበት መድረክ

በሳህሉ ብርሃኑ

አገራት በረጅም ታሪካቸው ውስጥ ለሚያጋጥሟቸው ስር የሰደዱ መዋቅራዊ ችግሮቻቸው እልባት ለመስጠት አብዛኛውን ጊዜ ሁለት መንገዶችን ይጠቀማሉ፤- የመሳሪያ ኃይል ወይም የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት። የጦር መሳሪያ ጊዜያዊ የበላይነትን ወይም የፀጥታ መረጋጋትን ያመጣ ይሆናል፤ ነገር ግን የታሪክ ቁስልን ፈውሶ፣ የጸና አገር የመገንባት አቅም ያለው የፖለቲካ ውይይት እና አገራዊ ምክክር ብቻ ነው።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ- ከገፀ ድር

ኢትዮጵያ ለቆዩ ችግሮቿ ዘላቂ መፍትሔ ለማፈላለግ እየመከረች ነው




# ፅዳትን ዘወትራዊ የማድረግ ጉዞ ከምን ደረሰ?

- በበጀት ዓመቱ 800 ሺህ የሚጠጋ የህብረተሰብ ክፍል በፅዳት ስራው ለማሳተፍ እቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው

በስንታየሁ ምትኩ

"አዲስ አበባ ፅዱ እየሆነች መጥታለች፤ በዘፈቀደ መንገድ ላይ ተጥሎ የምናየው ቆሻሻ ቀንሷል፤ ለእኛ ለፅዳት ሰራተኞች ስራችን እንዲቀል አድርጎልናል" ይላሉ ላለፉት 14 ዓመታት በመንገድ ጥርጊያ ላይ እየሰሩ ያሉት ወይዘሮ ኤደን መኮንን።

የሜክሲኮና ለገሀር አካባቢ ጎዳናዎች ጽዱና ውብ እንዲሆኑ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያደረጉ የሚገኙት ወይዘሮ ኤደን፣ የአዲስ አበባ የፅዳትና ውበት ሁኔታ ከቀድሞው ጋር ፈጽሞ አይወዳደርም። ከዚህ ቀደም በጠዋት በአንድ ዙር ብቻ ከሶስት እስከ አራት የፅዳት ሰራተኞች በመሆን ከሰባት እስከ ስምንት ኩንታል ደረቅ ቆሻሻ ይሰበስቡ ነበር። አሁን ላይ ግን ይህ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሶ አንድ ወይም ሁለት ኩንታል ደረቅ ቆሻሻ ብቻ እንደሚሰበስቡ ይናገራሉ።

በመንገዶች ዳር በሚገኙ ቱቦዎች ቆሻሻ በዘፈቀደ ይጣል ስለነበር፣ በአካፋ ከቱቦ ውስጥ ማውጣት እጅግ ፈታኝና አድካሚ ነበር።

ወደ ገጽ 6 ዞሯል


አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## የዛሬ አረንጓዴ አሻራችን የነገ ተስፋችን ነው!

ዓለም እየተጋፈጣቸው ካሉ ከባድ ፈተናዎች መካከል የአየር ንብረት ለውጥ፣ የደን መመናመን፣ የአፈር መሸርሸርና የብዝሃ ሕይወት መቀነስ ቀዳሚዎቹ ናቸው። እነዚህ ችግሮች አካባቢን የመጠበቅ ጉዳይ ብቻ ሳይሆኑ የኢኮኖሚ፣ የጤና፣ የምግብ ዋስትና እና የትውልድ ዕጣ ፈንታም ጭምር ናቸው። ኢትዮጵያም ይህንን እውነታ በመገንዘብ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን ወደ ተግባር አስገብታለች። ይህ መርሃ ግብር ዛፍ የመትከል ዘመቻ ብቻ ሳይሆን ለቀጣይ ትውልድ የሚተላለፍ የተስፋ፣ የኃላፊነትና የሀገር ግንባታ ምልክት ነው። ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ብትሆንም፣ በረጅም ዓመታት ሂደት ውስጥ የደን ሽፋኗ በእጅጉ ተመናምኗል። የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ የእርሻ መሬት መስፋፋት፣ ሕገ-ወጥ የደን ጭፍጨፋና ያልተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ችግሩን አባብሰውታል። የአፈር ጥበቃ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፣ ኢትዮጵያ በየዓመቱ በመቶ ሚሊዮን ቶን የሚቆጠር አፈር በዝናብ ተሸርሽሮ ይወሰድባታል። ይህ ደግሞ የግብርና ምርታማነትን ይቀንሳል፣ የውሃ ምንጮችን ያደርቃል፣ የድርቅና የጎርፍ አደጋዎችንም ያባብሳል። ይህ እውነታ ዛሬ የምንተክለው አንድ ችግኝ ነገ ሚሊዮኖችን ሊጠቅም የሚችል መሆኑን ያስገነዝባል።

በዚህ አውድ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በሀገራችን የአካባቢ ጥበቃ ታሪክ ውስጥ ልዩ ምዕራፍ ከፍቷል። ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በየዓመቱ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞች ተተክለዋል፤ አጠቃላይ የተተከሉትም ከ48 ቢሊዮን በላይ መድረሳቸው ተገልጿል። በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር "ተስፋን እንትከል" በሚል መሪ ሃሳብ ከ8 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል እቅድ ተይዞ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ በየአመቱም በአንድ ጀንበር የተከላ መርሃ ግብር በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግኞች ሲተከሉ ቆይተዋል። የዚህ ፕሮግራም ውጤት በቁጥር ብቻ አይለካም፤ የተራቆቱ መሬቶች እየለመለሙ፣ የውሃ ምንጮች እያገገሙ፣ የደን ሽፋን እየተሻሻለ መሆኑ የተጨባጭ ውጤቱ ማሳያዎች ናቸው።

ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች የአረንጓዴ አሻራ ከሌሎች አካባቢዎች የበለጠ ትርጉም አለው። በፍጥነት እያደገች ያለች ዋና ከተማ እንደመሆኗ የአየር ብክለት፣ የሙቀት መጨመር፣ የጎርፍ አደጋና የአረንጓዴ ስፍራዎች እጥረት እየፈተኗት ያሉ ችግሮች ናቸው። በዚህ ረገድ በከተማዋ እየተካሄዱ ያሉ የኮሪደር እና የወንዝ ዳር ልማት፣ የመናፈሻ ፓርኮች ግንባታና የችግኝ ተከላ ሥራዎች የከተማዋን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ የነዋሪዎችን ጤናና የኑሮ ጥራት እያሻሻሉ ናቸው። ዛፎች የካርቦን ልቀትን ይወስዳሉ፣ የአየር ብክለትን ይቀንሳሉ፣ የከተማውን ሙቀት ያረጋጋሉ፣ ለዜጎችም ጤናማ የመዝናኛ ስፍራዎችን ይፈጥራሉ።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ታላላቅ ድሎችን ያሳካችው በሕዝቧ የጋራ ተሳትፎ ነው። የአረንጓዴ አሻራም የዚህ መንፈስ ዘመናዊ መገለጫ ነው። ዛሬ የምንተክለው ችግኝ ነገ ንጹህ አየር፣ የተሻለ ጤና፣ ውብ ከተማና ዘላቂ ኢኮኖሚ ይፈጥራል። ይህ የትውልድ አደራ ነው፤ ከእኛ የሚፈለገውም በቃል ሳይሆን በተግባር መመለስ ነው። ስለዚህ የከተማዋ ነዋሪዎች፣ የመንግሥት ተቋማት፣ የግል ድርጅቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የሃይማኖት ተቋማትና የማህበረሰብ ድርጅቶች የፊታችን ሰኞ፣ ሐምሌ 27 ቀን 2018 ዓ.ም በሚካሄደው የአንድ ጀንበር መርሃ ግብር በንቃት መሳተፍ ይኖርባቸዋል። በተለይም በአዲስ አበባ እያንዳንዱ ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤትና ተቋም ቢያንስ ጥቂት ችግኞች በመትከልና በመንከባከብ ለከተማዋ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እጅግ ትልቅ ነው።

ስለዚህ ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች የአረንጓዴ አሻራ የራሳችን የኑሮ ዋስትና፣ የልጆቻችን የወደፊት ተስፋና የኢትዮጵያ ዘላቂ ብልጽግና መሠረት አድርገን እንውሰደው። በየአካባቢያችን አንድ ችግኝ መትከል፣ የተተከለውን መንከባከብ፣ አረንጓዴነትን የዕለት ተዕለት ባህላችን ማድረግ የምንችለው ትንሹ አስተዋጽኦ ቢመስልም፣ ለሀገራችን የሚያስገኘው ፋይዳ ግን እጅግ ትልቅ ነው። የዛሬ አረንጓዴ አሻራችን በእርግጥ የነገ ተስፋችን፣ የትውልድ አደራችንና የዘላቂ ብልጽግናችን መሠረት ነው።

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ስክነት የሚፈልገው የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችን

**በሰናይ ምግባሩ**

ማህበራዊ ሚዲያ አንድም እውቀት ለመቅሰም፣ የእይታ አድማስን ለማስፋት፣ ለራስ የሚበጁ ስራዎችን ለመከወን... አቅም እየሆነ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝብን ከሕዝብ፣ ሀገርን ከሀገር... የሚያጋጩ አጀንዳዎች የሚነዙበት መድረክም ነው፡፡ ትርፍ እና ኪሳራው እንደ ተቀባዩ እና ተጠቃሚው ይወሰናል፡፡

ይህ ሚዲያ በባህሪው በግለሰቦች እጅ ያለ እንደመሆኑ መጠን መረጃ ስናስተላልፍም ሆነ የሌሎችን መረጃ ስናነብ፣ ስናይ እና ስናዳምጥ በኃላፊነት ስሜት መሆን አለበት፡፡ አተያያችን በዚህ መንገድ ሲሆን ነው ጥፋቱን ሳይሆን ትርፉን የምንቋደሰው፤ መከፋፈል ሳይሆን አንድነትን የምናጠናክረው፤ ወደ ኋላ የሚጎትቱ ሳይሆን ወደ ፊት የሚያስፈነጥሩ ሃሳቦችን መገብየት የምንችለው፡፡

ይኼን ያልኩት አሁን ላይ በተደጋጋሚ እየተገለጠ እንዳለው ኢትዮጵያ እየመከረች ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ስብራት ሆነው የቆዩ ችግሮችን ለይተው በወኪሎቻቸው ተመካካሪዎች አማካኝነት ጠረጴዛ ስበውና የቀደመውን አኩሪ እሴት ዘመኑ ከሚጠይቀው ስልጡንነት ጋር አወዳጅተው ሀሳባቸውን እየተለዋወጡ ነው፡፡

በእነዚህ ተመካካሪዎች የሚነሱት ሀሳቦችም ሆነ የመፍትሔ አማራጮች ሁላችንም የሚጠቅም፣ ለሀገር መጻኢ እድል ብሩህ ተስፋን ይዞ የሚመጣ ነው የሚል እምነት በብዙዎች ዘንድ አለ፡፡

ሆኖም ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ተጠባቂው ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያመጡ ሀሳቦች ሲንሸራሸሩ ይታያል። በተመካካሪዎች የሚንሸራሸሩ ሀሳቦች እንደ መጨረሻ ውሳኔ በመውሰድ “እንዲህ ተብሏል፤ እንዲህ ተደርጓል...” የሚሉ መረጃዎች እየተጋሩ ነው፡፡ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑም በዚህ ረገድ ከተረጋገጠ ምንጭ ብቻ መረጃን ውሰዱ እስከማለት የደረሰ መግለጫ የመስጠቱ ምክንያትም ይኸው ነው፡፡

ይህ ወርቃማ እድል እንዳይባክን መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ በማህበራዊ ሚዲያ የሚዘዋወሩ መረጃዎችን በጥልቀት መመርመር፣ ሊያስከትሉ የሚችሉትን መዘዝ አስቀድሞ መገንዘብ ይገባል፡፡ ይህ ሲሆን ምክክሩ ግቡን እንዲመታ የበኩላችንን አሻራ ተወጣን ማለት ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

በጥቅሉ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችን ሚዛናዊ፣ ገንቢ እና አሰባሳቢ ለሆኑ ጉዳዮች ቦታ የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡ በፍጥነት ያለምክንያታዊነት የሚደረጉ ነገሮች ህዝብን ብሎም ሀገርን ሊጎዱ ይችላሉ።

ለዚህ ደግሞ ስክነት ወሳኝነት አለው። የምናጋራውን መረጃ መልዕክት አስቀድመን መመርመር፣ ትርፍና ኪሳራውን ማስላት ያስፈልጋል። ሌሎች የሚያደርሱን መረጃ ደግሞ ከጀርባው ምን ይዟል? በሚል ግራ ቀኙን ባየ መንገድ ከፈተሽን በኋላ ጠቃሚ ሆኖ ካገኘነው ብቻ ሀሳቡን ብንገዛው እንዲሁም ለሌሎች እንዲደርስ ብናደርግ ጥሩ ነው፡፡

በየትኛውም የእድሜ እርከን ያለን የሚዲያው ተጠቃሚ በዚህ መንገድ ራሳችንን ብንቃኝ ለራሳችን፣ ለማህበረሰባችን ብሎም ለሀገራችን ገንቢ ሚና መጫወት እንችላለን የሚል እምነት አለኝ፤ እናንተስ ምን ትላላችሁ?

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
እዮብ ተፈራ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ
ፋንታነሽ ተፈራ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ
ቶሎሳ መብራቴ

# ከተፈጥሮ የተወዳጀች ከተማ

## • የፊታችን ሰኞ እንደ ሀገር 800 ሚሊዮን ፤ በአዲስ አበባ አንድ ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል

**በቶለሳ መብራቴ**

አረንጓዴነት የከተማዎች ውበት ብቻ አይደለም፤ የአካባቢ ዘላቂነት፣ የሕዝብ ጤና፣ የኢኮኖሚ ዕድገትና የትውልድ ደኅንነት መሠረት ነው። ዛሬ ዓለም በአየር ንብረት ለውጥ፣ በሙቀት መጨመር፣ በደን መራቆት እና በብዝሃ ሕይወት መቀነስ የተነሳ የአካባቢ ችግሮችን ለመቅረፍ በርካታ ሀገራት የአረንጓዴ ልማትን በብሔራዊ ፖሊሲያቸው ማዕከል አድርገው እየሰሩ ይገኛሉ።

አዲስ አበባ ደግሞ በፍጥነት ከሚያድጉ የአፍሪካ ከተሞች መካከል አንዷ ናት። የሕዝብ ብዛት መጨመር፣ የግንባታ መስፋፋት፣ የአየር ብክለትና የአረንጓዴ ስፍራዎች መቀነስ በከተማዋ ላይ ጫና እየፈጠሩ እንደነበረ የሚታወስ ሐቅ ነው።

ኢትዮጵያም በ2011 ዓ.ም. የተጀመረውን "አረንጓዴ አሻራ" መርሐ ግብር በመተግበር የደን ሽፋንን ለማሳደግ፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋምና ለትውልድ ዘላቂ አካባቢ ለመፍጠር ታላቅ እንቅስቃሴ አድርጋለች። በዚህ ሀገራዊ ጥረት ውስጥ አዲስ አበባ ልዩ ሚና ተጫውታለች። በከተማዋ የተካሄደው የችግኝ ተከላ፣ የመንገድ ዳር አረንጓዴ ልማት የከተማዋን ገጽታ በሚታይ ሁኔታ ቀይረውታል።

በከተማዋ በየዓመቱ በሚካሄዱ የችግኝ ተከላ ዘመቻዎች በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግኞች ተተክለዋል። በዚህ ሂደት የመንግሥት ተቋማት፣ የግል ድርጅቶች፣ ተማሪዎች፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ የሃይማኖት ተቋማትና መላው ነዋሪ በአንድነት ተሳትፈዋል። ይህ ተሳትፎ የችግኝ ተከላን ከመንግሥት ፕሮጀክትነት ወደ ሕዝብ ንቅናቄ ከፍ እንዳደረገው የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂና ቢዩልት ኢንቫይሮንመንት ኮሌጅ የከተማ ፕላን እና ዲዛይን መምህርና ተመራማሪ የሆኑት ብርሃኑ ግርማ (ዶ/ር) ከዚህ ቀደም ከተማዋ የነበረችበትን እና አሁን ያለችበትን ሁኔታ በማነፃፀር በሰጡት አስተያየት፤ ከተማዋ ከዚህ ቀደም የነበሩባትን የመዋቅርና የፕላን ጉድለቶች በመቅረፍ ላይ ትገኛለች።

አንድ ከተማን ዘመናዊና ደረጃዋን የጠበቀች ለማድረግ ከሚተገበሩት መመሪያዎች መካከል የ30-30-40 የከተማ ስታንዳርድ ተጠቃሽ ነው። በዚህም መሠረት፡- 40 በመቶ ለግንባታዎች፣ 30 በመቶ ለሕዝብ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች፣ ለአረንጓዴ መሠረተ ልማቶች፣ ለማህበረሰብ ተቋማት እና ክፍት ቦታዎች እና የተቀረው 30 በመቶ ደግሞ ለተለያዩ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች እንዲውል ይደረጋል።

ከተማ ማለት የሕንፃዎች ጥርቅም ብቻ አይደለችም። እውነተኛ የከተማ ዘመናዊነትና ሥልጣኔ የሚለካው ሕንፃዎችን ከተፈጥሮ፣ ልማትን ደግሞ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ማጣመር ሲቻል ብቻ ነው። ብርሃኑ (ዶ/ር) እንደሚያስረዱት፤ የከተማ ውበትና ለኑሮ ምቹነት መሠረቱ የህንጻዎች ቁመት ሳይሆን፣ ነዋሪዎችና እንግዶች የሚተነፍሱባቸው፣ የሚያርፉባቸው፣ ባህላዊና ዘመናዊ እሴቶች ተዋሕደው የሚታዩባቸው ክፍትና አረንጓዴ ስፍራዎች ሲኖሩ ነው።



ግራፊክስ - በእዮብ ተፈራ
አዲስ አበባን ከተፈጥሮ የተስማማች ዛሬንና ነገንም ታሳቢ ያደረገች ከተማ ለማድረግ የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል

ብርሃኑ (ዶ/ር)፤ አዲስ አበባ ለዓመታት የከተማ ፕላን ክፍተት በመቅረፍ፣ በአሁኑ ወቅት የ30 በመቶ የአረንጓዴ ሽፋን ስታንዳርድን በበቂ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ እየተጋች ትገኛለች። ይኸውም ሀገራዊው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር ከከተማ ኮሪደር ልማት ጋር በጠበቀ ሁኔታ ተሳስሮ በመተግበሩ፣ ከተማዋን ከግንባታ ጫና አውጥቶ ሕይወትና ንጹሕ አየር ወደሚሰጥ አረንጓዴ ምህዳር እየቀየራት ነው።

ይህ በጠንካራ መርሐ-ግብርና ሕዝባዊ መሠረት የያዘው የአረንጓዴ አሻራ ልማት ያለምንም መሸራረፍ በቀጣይነት ከተከናወነ፣ አዲስ አበባ የፈጣን ዕድገትና የምቹ የከተማ ሕይወት ማሳያ በመሆን ከአፍሪካ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ተመራጭ ሜትሮፖሊስ የመሆን ራእይዋን በተግባር የምታረጋግጥበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ብርሃኑ (ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ የተፋሰስና አረንጓዴ ልማት ዳይሬክተር ወይዘሮ ስንታየሁ መንግስቱ እንደገለጹት፣ ከተማዋ በአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ባለፉት ስምንት ተከታታይ ዓመታት በርካታ ተግባራትን ስታከናውን ቆይታለች። በዚህም ቢሮው ዘንድሮን ሳይጨምር ከ90 ሚሊዮን በላይ የጥላ፣ የውበትና የፍራፍሬ ችግኞችን መትከሉን ተናግረዋል። በመዲናዋ ዘንድሮ 6 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ፣ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ብቻ ከአራት ሚሊዮን በላይ ችግኞች ተተክለዋል።

አዲስ አበባ እንደ ስሟ አበባ እንድትሆንና በለምለም ዕፅዋቶች እንድትታጀብ ለማድረግ የተከናወኑ የተቀናጁ ሥራዎች ውጤት አስገኝተዋል። በ2010 ዓ.ም 2 ነጥብ 8 በመቶ ብቻ የነበረው የመዲናዋ አረንጓዴ ሽፋን አሁን ላይ 24 በመቶ መድረሱን የከተማ አስተዳደሩ የ2018 በጀት ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት ያመላክታል። የአረንጓዴ ሽፋንን በማስፋት የተገኘው ውጤት አዲስ አበባን በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተቀመጠው የአንድ ከተማ የ30 በመቶ አረንጓዴ ሽፋን መደበኛ መስፈርት ጋር እጅግ ያቀራርባታል።

ወ/ሮ ስንታየሁ፤ አዲስ አበባ በተፈጥሮ መልከዓ-ምድሯ ተዳፋትና ዳገት ያላት ከተማ በመሆኗ የክረምት ወቅት የጎርፍ አደጋ ዋነኛ ሥጋቷ ነበር፡፡ በመሆኑም በእንጦጦ እና በከፍታ ቦታዎች የተተከሉ ችግኞች የዝናብ ውሃ በቀጥታ አፈርን አጥቦ እንዳይሄድ ከማገድ ባለፈ የችግኞቹ ሥሮች የዝናብ ውሃ ወደ መሬት ውስጥ እንዲሰርግ በማድረግ የጎርፍ ፍሰት መጠንን እና ፍጥነትን በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሰውታል።

እንዲሁም የከተማዋን የወንዝ ዳርቻዎች በአረንጓዴ ዕፅዋት በመሸፈን የጎርፍ ሙላት እና የወንዝ ዳርቻዎች መሸርሸርን እንዲቀንስ አድርጓል። በከተማዋ የተተከሉት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግኞች የካርበን ልቀትን በመምጠጥ የአየር ብክለትን ለመቀነስ እና ንጹሕ አየር ለመፍጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ እንደሚገኙ ዳይሬክተሯ ተናግረዋል።

በተለይም ከኮሪደር እና ከወንዝ ዳርቻ ማልማት ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ አረንጓዴ መናፈሻዎች የከተማዋን ገጽታ በእጅጉ ለውጠውታል። ቀድሞ በቆሻሻ የተሞሉ፣ ለሕዝብ ዝግ የነበሩ የወንዝ ዳርቻዎች ዛሬ በእግረኛ መንገዶች፣ በብስክሌት መስመሮች፣ በአረንጓዴ መናፈሻዎችና በመዝናኛ ስፍራዎች ተተክተዋል። ይህም ከተማዋን ለነዋሪዎች ብቻ ሳይሆን ለጎብኚዎችም የሚስብ መዳረሻ አድርጓታል ሲሉ ወ/ሮ ስንታየሁ ተናግረዋል።

አረንጓዴ አሻራ ያመጣው ለውጥ በአካባቢ ጥበቃ ብቻ የሚለካ አይደለም ያሉት ዳይሬክተሯ፤ በከተሞች ውስጥ የዛፎች መጨመር የአየር ጥራትን አሻሽሏል፣ የካርቦን ልቀት ቀንሷል፣ አቧራ ቀንሷል፣ የሙቀት መጠንን አረጋግቷል።

ከዚህ ባለፈ የአረንጓዴ ልማት የሕዝብ ጤናንም አጎልብቷል። በመናፈሻዎች ውስጥ የእግር ጉዞ፣ የአካል ብቃት ሥልጠናና የቤተሰብ መዝናኛ ዕድሎች መፈጠራቸው የሰዎችን የአካልና የአእምሮ ጤና አሻሽሏል።

በኢኮኖሚውም በኩል አረንጓዴ አሻራ የጎላ ፋይዳ እንዳለው ያነሱት ወ/ሮ ስንታየሁ፤ የከተማዋ ውበት መጨመር ቱሪዝምን ያበረታታል፤ የመዝናኛ ቦታዎች መስፋፋት ለአነስተኛ ንግዶች አዲስ የሥራ ዕድል ይፈጥራል፤ የመኖሪያ ጥራትንም ይጨምራል። በአረንጓዴ መናፈሻዎች ዙሪያ የሚፈጠሩ የቡና መጠጫ ቤቶች፣ የምግብ ቤቶች እና ሌሎች አገልግሎቶች የከተማዋን ኢኮኖሚ አነቃቅተዋል።

በማኅበራዊ ዘርፍም የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር የጋራ ኃላፊነትን አጠናክሯል። ችግኝ መትከል ብቻ ሳይሆን ዛፍ ሆኖ እስኪያድግ ድረስ መንከባከብ የዜግነት ባህልን እያጎለበተው ነው። በብዙ አካባቢዎች ነዋሪዎች የጋራ አረንጓዴ ስፍራዎችን በመንከባከብ የአካባቢ ባለቤትነት ስሜት አዳብረዋል።

የትምህርት ተቋማትም በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። ተማሪዎች በተግባር የአካባቢ ጥበቃን በመማር ለወደፊቱ አካባቢን የሚጠብቅ ትውልድ እንዲፈጠር መሠረት ተጥሏል። ይህ የረጅም ጊዜ ትሩፋት ከተተከሉት ዛፎች ያልተናነሰ ዋጋ እንዳለው ዳይሬክተሯ ተናግረዋል።

ከዚህም በላይ አረንጓዴ አሻራ ለወደፊቱ የካርቦን ልቀትን የሚቀንስ፣ የአየር ጥራትን የሚያሻሽልና የከተማዋን የአየር ንብረት መቋቋም አቅም የሚያሳድግ ስትራቴጂካዊ ኢንቨስትመንት ነው። ዛሬ የተተከለው ችግኝ ለነገ ትውልድ ጭምር የሚጠቀምበት ሀብት ነው።

አዲስ አበባ በአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ያስመዘገበችው ለውጥ በተተከሉ ችግኞች ብዛት ብቻ የሚለካ አይደለም። በከተማዋ የተፈጠረው አዲስ አረንጓዴ ገጽታ፣ የአየር ጥራት መሻሻል፣ የሕዝብ ተሳትፎ መጠናከር፣ የመዝናኛ ስፍራዎች መጨመር፣ የኢኮኖሚ ዕድሎች መፈጠርና ለወደፊት ትውልድ የሚተላለፍ የአካባቢ ጥበቃ ባህል መገንባቱ የፕሮግራሙ እውነተኛ ውጤቶች ናቸው።

ከተማዋ ይህንን ጉዞ በቁርጠኝነት ከቀጠለች፣ አዲስ አበባ በአፍሪካ ከአረንጓዴ፣ ከንጹሕና ለሰው ምቹ ከተሞች መካከል ቀዳሚ ስፍራ የምትይዝበት ዕድል ሰፊ ነው። አረንጓዴ አሻራ የዛሬን ከተማ ውብ ከማድረግ በላይ የነገን ትውልድ የሚጠብቅ ታሪካዊ ቅርስ እየሆነ መጥቷል።

ወ/ሮ ስንታየሁ እንደገለጹት፣ የተተከሉት ችግኞች በጥሩ ጽድቀት ላይ የሚገኙ ሲሆን በአማካኝ እስከ 86 በመቶ የሚደርስ የጽድቀት መጠን ማስመዝገብ ተችሏል። ይህም አየርን ከካርቦን ዳይኦክሳይድ ልቀት በመጠበቅ፣ ንጹሕ አክስጅን በመስጠትና የሙቀት መጠንን በመቀነስ ረገድ ለአካባቢ ጥበቃ ከፍተኛ ድርሻ እያበረከተ ይገኛል።

የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ከአካባቢ ጥበቃ ባሻገር የኅብረተሰቡን ማኅበራዊ መስተጋብር ማጠናከሩን የገለጹት ወ/ሮ ስንታየሁ፣ ኅብረተሰቡ በጾታ፣ በዘርና በዕድሜ ሳይለያይ በአንድነት እንዲሳተፍ ማድረጉን ጠቁመዋል። እንዲሁም በፓርኮች፣ በወንዞችና በኮሪደሮች አካባቢ የተተከሉ ችግኞች ነዋሪዎች በነጻነት ተሰብስበው የሚወያዩበትና የሚያርፉበትን ምቹ ሁኔታ ፈጥረዋል።

መንግስት እንደ ሀገር የፊታችን ሐምሌ 27/2018 ዓ.ም የሚካሄደው ሀገር አቀፍ የ1 ጀምበር 800 ሚሊዮን የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር ዝግጅት መጠናቀቁንና በዚህም እንደ አዲስ አበባ አንድ ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል፡፡ ችግኞቹንም ወደ ተከላ ቦታዎች ማጓጓዝ ተጀምሯል ብለዋል ወይዘሮ ስንታየሁ፡፡

## ለጋራ... ከገጽ 1 የዞረ

አሜሪካዊ የሰላም ተመራማሪው ጆን ፖል ሌደራች እንደሚያስረዱትም፤ አገራዊ ምክክር ማለት ተቃራኒ እይታ ያላቸው አካላት የሚከራከሩበት መድረክ ሳይሆን፣ የጋራ እጣ ፈንታቸውን የሚወያዩበት "የማህበራዊ ውል ማደሻ" ሆኖ አገልግሏል።

ኢትዮጵያ እንደሀገር እንዲሁም እንደህዝብ አትራፊ የሆነውንና የወደፊት የአብሮ መኖርን እጣፈንታ የሚወስነውን ሀገራዊ ምክክር እያካሄደች ትገኛለች። ኢትዮጵያ የሺህ ዓመታት የታሪክ ባለቤት፣ የበርካታ ቋንቋዎች፣ ባሕሎች፣ እምነቶችና ማንነቶች መኖሪያ ሀገር ናት። ይህ ሀቅ እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ለዓመታት የቆዩ አለመግባባቶችና ችግሮች ብዙ ናቸው። እነዚህ አለመግባባቶች የሀገር ሰላም፤ አንድነት፤ ልማት እድገትና የዜጎችን የወደፊት ተስፋ የሚፈታተኑ ሆነው መቆየታቸው ሳያንስ ለዘመናት የዘለቁ ውስብስብ የፖለቲካ እና የማህበራዊ አለመግባባቶቿን በጠረጴዛ ዙሪያ ለመፍታት ታደርግ የነበረው ጥረትም ስኬታማ ነበር ማለት አይቻልም።

ለመሆኑ የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር አዲስ ምዕራፍ ያበስራል ሲበል ምን ማለት ነው? ይህ ምክክር ውጤታማ ሆኖ መጠናቀቁስ ስር የሰደዱ ችግሮቻችንን ፈትቶ የመጪውን ዘመን ብሩህ ለማድረግ ያለው ድርሻ ምን ያህል ነው? የሚሉትንና መሰል ጉዳዮች መፈተሽ ተገቢ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደሚገልፁት ኢትዮጵያ እያከናወነች ያለው ምክክር ለዘመናት የተከማቹ ስር የሰደዱ ሀገራዊ ችግሮችን በጋራ ፈትቶ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የሚበጅ አዲስ ማህበራዊ ውል ለመፈረም የተዘጋጀ መድረክ ነው። ምክክሩ ዜጎች ልዩነቶቻቸውን በኃይልና በግጭት ፈንታ በማዳመጥና በሰለጠነ የሃሳብ ፍልሚያ እንዲፈቱ በር ከፋች ነው።

ኢትዮጵያ እያካሄደች ያለው ምክክሩ በሀገሪቱ በግጭት ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ እና ወደፊት ተመሳሳይ ግጭቶች እንዳይደገሙ መሠረት በመጣል ዘላቂ ሰላም ያስገኛል፡፡ የተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎች፣ ሃይማኖቶች እና ፖለቲካዊ አመለካከቶች ያላቸው ዜጎች በጋራ የሚኖሩበትን መሰረት ለማጠናከርም ይረዳል፡፡ ሀገራዊ ጉዳዮችን በጦርነት ወይም በኃይል ሳይሆን በውይይትና በስምምነት የመፍታት ባህልንም ያጠናክራል፡፡ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁሩ አቶ ደያሞ ዳሌ እንደሚገልፁት፣ ኢትዮጵያ የምታደርገው ይሄ ሀገር አቀፍ የምክክር ጉባኤ ትልቅ ትርጉምና ሀገራዊ ፋይዳ አለው፡፡

የሽግግር ወቅት ፍትህ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ሌናርድ ካፕላን በበኩላቸው "አገራዊ ምክክር በስኬት የፈፀሙ አገራት ታሪካዊ ቁስሎቻቸውን እውቅና በመስጠትና በይቅርታ በመፈወስ ረገድ ከፍተኛ ውጤት ያሳያሉ፤ ይህም ለቀጣይ ትውልድ የተረጋጋ አገር የማስረከብ መሰረት ነው።" ይላሉ፡፡ በግጭት አፈታት እና በአገር ግንባታ ዙሪያ የሚሰሩ ታዋቂ ምሁራን እንደሚስማሙበት፤ አገራዊ ምክክር ተራ የፖለቲካ ድርድር ሳይሆን የመዋቅራዊ ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ነው።



ፎቶ፦ ገፀ ድር
ኢትዮጵያ ለቆዩ ችግሮቿ ዘላቂ መፍትሔ ለማፈላለግ እየመከረች ነው

> **በሀገር ደረጃ የሚነሱ ውስብስብ ጉዳዮች የሚፈቱት በአንድ ወገን አሸናፊነት ሳይሆን፣ በጋራ መግባባትና በሁሉም ወገኖች ተሳትፎ መሆኑን ዓለማቀፍ ልምዶች ያሳያሉ። በመሆኑም የሀገራዊ ምክክር ሂደት የዛሬን ችግሮች ብቻ ሳይሆን የነገውን ትውልድ የሚጠቅም የመግባባት ባሕል ለመፍጠር ያግዛል**

በርሊን የሚገኘው የበርጎፍ ፋውንዴሽን ጥናትና ምርምር ተቋም አማካሪው ቬሮኒክ ዱዶኝ (ዶ/ር) የሚያብራሩት ኃይልና ጠመንጃ ጊዜያዊ ጸጥታን እንጂ ዘላቂ ሰላምን ማምጣት እንደማይችሉ እና የምሁራንና የማህበረሰብ ክፍሎችን ድምፅ ያካተተ አገራዊ ምክክር ብቻ የመጪውን ዘመን ብሩህ ለማድረግ አሰተማማኝ መንገድ መሆኑን ነው። ሰላም ሲኖር የጸና መንግሥትና የተረጋጋ ማህበረሰብ ይፈጠራል፣ ኢንቨስትመንት ይጨምራል፣ ንግድ ይስፋፋል፣ የቱሪዝም ዘርፍ ያድጋል እንዲሁም የስራ ዕድሎች ይፈጠራሉ። የፍትህ፣ የምርጫ፣ የጸጥታ እና ሌሎች የመንግሥት ተቋማት በተሻለ መልኩ እንዲሰሩ ያግዛሉ፡፡ መረጋጋት ሲኖር ደግሞ የውጭ ኢንቨስተሮች፣ አጋር ሀገራት እና ዓለም አቀፍ ተቋማት በኢትዮጵያ ላይ የሚኖራቸውን እምነት ይጨምራል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ ሀገራዊ ምክክሩ በውይይትና መግባባት ለኢትዮጵያ ዘላቂ መፍትሔ የማምጣት አዋጭ መንገድ ስለመሆኑ ይገልጻሉ። የሀገራዊ ምክክር ጉባኤው በሰላማዊ፣ በነፃ እና በመተማመን መንፈስ እየተካሄደ ስለመሆኑ ፕሮፌሰር መስፍን ይገልጻሉ። ከ4 ሺህ በላይ ተመካካሪዎች ከ10 እስከ 50 አባላት ባሉት ንዑሳን የውይይት ቡድኖች ተከፋፍለው ሀሳባቸውን በነፃነት እየተለዋወጡም ይገኛሉ፡፡ ዋና ኮሚሽነሩ እንደሚገልፁት ሀገራዊ ምክክሩ የተለያዩ ሐሳቦችን አንድ ላይ በማምጣት የጋራ ራዕይን ለመገንባት የሚረዳ ሂደት ነው። በሀገር ደረጃ የሚነሱ ውስብስብ ጉዳዮች የሚፈቱት በአንድ ወገን አሸናፊነት ሳይሆን፣ በጋራ መግባባትና በሁሉም ወገኖች ተሳትፎ መሆኑን ዓለማቀፍ ልምዶችም ያሳያሉ። በመሆኑም የሀገራዊ ምክክር ሂደት የዛሬን ችግሮች ብቻ ሳይሆን የነገውን ትውልድ የሚጠቅም የመግባባት ባሕል ለመፍጠር ያግዛል። ዘላቂ ሰላም እና ዴሞክራሲ እውን እንዲሆንም ሚናው ቀላል አይደለም፡፡

አገራዊ ምክክሩ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የሀሳብ መሪዎች እንዲሁም የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሀሳብ ልዩነቶችን በውይይት የመፍታት ልምምድ እንዲኖር ሚናው ከፍተኛ ስለመሆኑም የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁሩ አቶ ደያሞ ዳሌ ይገልጻሉ፡፡ አያይዘውም ለዘመናት ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የሚያስችል የፖለቲካ ባህል ለማዳበር እና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ምቹ መደላድል ለመፍጠር ያግዛል።

የሰላም ተመራማሪዎች እንደ ሚገልፁት፣ አገራዊ ምክክር ጊዜያዊ የማረጋጋት ስራ ሳይሆን ዘላቂ መፍትሔ የሚያመጣ መሆኑንም ይገልጻሉ። አብዛኛውን ጊዜ በፖለቲካ ሊቃውንት ደረጃ ብቻ የሚደረጉ ድርድሮች የችግሩን ወለል ብቻ ይዳስሳሉ። አገራዊ ምክክር ግን የዜጎችን ስር የሰደዱ ቅሬታዎች ወደ አደባባይ በማውጣት እውነተኛውን የችግር መንስኤ ያመጣሉ። የተገለሉ ወገኖችን፣ ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ የኃይማኖት አባቶችን እና ተቃዋሚዎችን ያሳተፈ ምክክር የውሳኔዎች ባለቤት ህዝቡ ራሱ እንዲሆን ያደርጋል። ይህም ውሳኔዎቹ የረጅም ጊዜ ህሊናዊ እና ህጋዊ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ያስችላል።

አገራዊ ምክክር የፖለቲካ ውጥረቶችን በማርገብ ረገድ ያለውን ሚና በተመለከተ በዘርፉ ሰፊ ጥናት ያደረጉት ካትሪን ግሮተንሁይስ (ዶ/ር) እንደሚገልፁት፣- የምክክር መድረኮች "የዜጎችን የተቃረኑ ትረካዎች ወደ አንድ አገራዊ እይታ የመቀየር አቅም አላቸው"። የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎች እንደሚያስረዱት፤ አገራዊ ምክክር በውይይት ደረጃ ብቻ ሳይቀር በህግ እና በተቋማዊ ማሻሻያ ሲደገፍ የፖለቲካ ስብራቶችን ከመጠገንም በላይ የኢኮኖሚ መረጋጋትን ያረጋግጣል።

መንግሥት የምክክር ኮሚሽኑን ከማዋቀር ጀምሮ ሂደቱ ፍጹም ነጻ፣ ገለልተኛ እና ዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን ብቻ የቀመረ ሙያዊ አሰራርን የተከተለ እንዲሆን በማድረግ ጣልቃ ገብነት ሙሉ በሙሉ አስቀርቷል። በዚህም የምክክሩ ውጤቶች የዴሞክራሲ፣ የፍትህ እና የደህንነት ተቋማት ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ ሆነው እንዲገነቡ መንገድ ይጠርጋሉ። በምክክር የሚፈጠረው መግባባት፣ ለመጪው ትውልድ የተረጋጋች፣ የተባበረች፣ ሰላማዊና የበለፀገች ኢትዮጵያን የሚያስረክብ መሠረት ይሆናል። ይህ ሀገራዊ ምክክር የጋራ መግባባት ባህልን ለማጠናከር፣ ለፀናችና ለተሻለች ኢትዮጵያ የተከፈተ ትልቅ በር ነው ማለት ይቻላል።

ያለፉትን ቁስሎች በይቅርታና በእውነት ታጥቦ ማለፍ፣ ልዩነቶችን እንደ ሀብት ቆጥሮ በጠረጴዛ ዙሪያ መወያየት ለመጪው ትውልድ የተሻለችና የጸናች አገርን ለማውረስ የማይተካ ዕድል ይሰጣል። በመሆኑም ዛሬ በኢትዮጵያ የተከፈተው ይህ የውይይት በር፤ የነገዋን የበለጸገች፣ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊት አገር እውን ለማድረግ የተጣለ ጽኑ መሠረት በመሆኑ ሁሉም ህብረተሰብ በባለቤትነት ሊደግፈው ይገባል።

# የኑሮን ጫና ያቀለሉ የሰንበት ገበያዎች

- **በአዲስ አበባ በሚገኙ 264 የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች የተለያዩ ምርቶች በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ እየቀረቡ ስለመሆኑ ተመላክቷል**

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

በአዲስ አበባ መሠረታዊ የፍጆታ ምርቶች ላይ የሚስተዋለውን የተጋነነ የዋጋ ጭማሪ ለማስቀረት የተለያዩ ሥራዎች መሠራት ከጀመሩ ዋል አደር ብለዋል ።

ከተሰሩ ሥራዎችም በከተማዋ በሁሉም አቅጣጫዎች በሚባል ደረጃ ቅዳሜና እሑድ ገበያዎች እንዲሁም በአምስቱም የመግቢያ በሮች ትልልቅ የግብይት ማዕከላት ተገንብተው አገልግሎት መስጠት መጀመራቸው በጉልህ ይነሳል፡፡

የእነዚህ ገበያዎች ተጠናክሮ መቀጠል በተለይም በአትክልትና ፍራፍሬ፣ ጥራጥሬና እህል ነክ ምርቶች እንዲሁም ዘይት፣ ማካሮኒ፣ ፓስታና ሌሎች የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች ላይም በተጨባጭ ለውጥ መኖሩን ነው ቅዳሜና እሑድ ገበያዎች ተገኝተን አረጋግጠናል፡፡



ፎቶ፦ ከገፀ ድር
የመዲናዋ ነዋሪዎች በቅዳሜና እሑድ ገበያዎች የተለያዩ ምርቶችን ሲሸምቱ

ወይዘሮ የሺ አርጎ በአዲስ አበባ ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ በተለምዶ 72 ተብሎ በሚጠራው አካባቢ መኖር ከጀመሩ ወደ ስድስት ዓመት እንደሆናቸው ይናገራሉ። በቆይታቸውም እንደ ሽንኩርት ቲማቲም፣ ቃሪያና ሌሎችም በየእለቱ በሚጠቀሟቸው የፍጆታ ዕቃዎች ላይ የዋጋ ጭማሪና የኑሮ ውድነት ከአመት አመት እየተባባሰ መሄዱን ያነሳሉ፡፡

ምንም እንኳን በከተማዋ የምርት እጥረት ጎልቶ ሲከሰት ባይታይም አምና በተሸጠበት ዋጋ ዘንድሮ የሚገኝ የሸቀጥ ምርትም ሆነ የግብርና ውጤቶች አልነበሩም የሚሉት አስተያየት ሰጪዋ በቅርቡ በአቅራቢያቸው በተከፈተው ለሚ ሁለገብ የግብይት ማዕከልና ቅዳሜና እሑድ ገበያዎች የሚፈልጉትን የግብርናም ሆነ የኢንዱስትሪ ምርቶች በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት መቻላቸው ትልቅ እፎይታ እንደሰጣቸው ተናግረዋል፡፡

በተለይ በአቅራቢያቸው ከሚገኘው ቅዳሜና እሑድ ገበያ ያለምንም ደላላ ከአምራቾችና ጅምላ ነጋዴዎች በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ጥራት ያላቸው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ አስችሏቸዋል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህም በከተማም ሆነ በገጠር የጓሮ አትክልቶችና ልዩልዩ የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶች መመረት መጀመራቸው እንዲሁም መንግስት በቅዳሜና እሑድ ገበያና ትልልቅ የገበያ ማዕከላት በተመጣጣኝ ዋጋ ቀጥታ ከአምራች አካላት የተገኘ ምርት ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ተደራሽ ማድረጉ የኑሮ ውድነቱን ለመከላከል አስተዋጽኦ አድርጓል ባይ ናቸው፡፡

ከአትክልትና ፍራፍሬ በተጨማሪም የምግብ እህል ለምሳሌ እንደ ጤፍ፣ ስንዴና በቆሎ በመሰሉት የግብርና ምርቶች ላይ የታየው የዋጋ መረጋጋት በተለይ በክረምት ወራት በከፍተኛ ደረጃ ዋጋቸው ሊጨምር የሚችሉት የምግብ እህሎች ባሉበት መቆማቸው ይበል የሚያሰኝ ለዚህም መንግስትና የሰንበት ገበያዎች የምርት አይነቶችን ጨምረው በማስፋት የጀመሩትን ሥራ አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው የሚያሳዩ እንደሆኑም ሳይገልፁ አላለፉም፡፡

ስድስት ኪሎ አካባቢ ቅዳሜና እሁድ ገበያ ለቤት ፍጆታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ሲሸምቱ ያገኘናቸው አቶ ዳዊት በርሄም ሌላው አስተያየት ሰጭ ናቸው፡፡ አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ ሌሎች ምርቶችን ለመሸመት በመንደር ውስጥ ካሉ ሱቆች ይልቅ የቅዳሜና እሑድ ገበያዎችን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ ገልፀው በገበያዎቹ በእያንዳንዱ ምርት ላይ መንደር ውስጥ ከሚገዙት በኪሎ ከ10 እስከ 20 ብር ቅናሽ እንዳላቸው ነው ያመላከቱት፡፡ እንደ እሳቸው አባባል የእነዚህ ገበያዎች መስፋፋት በሸማችና አምራች መካከል ያለውን አላስፈላጊ ተዋናይ ወይም ደላላ በማስቀረት የሚፈልጉትን ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሸምቱ በማድረግ ረገድ ጉልህ አበርክቶ አላቸው።

ይህንን ቃለ መጠይቅ ባደረግንበት ወቅት በመገናኛ አካባቢ ጥሩ የሚባል ነጭ ሽንኩርት በኪሎ 80 ብር፣ ቀይ ሽንኩርት 90 ብር እንዲሁም አምስት ሊትር ዘይት በ1ሺህ 800 ብር መግዛታቸውን በደስታ የነገሩን ወይዘሮ ብርቱካን ጫላ በዚህ ዋጋ ያውም ከሚኖሩበት አካባቢ በቅርብ ርቀት ባለ ገበያ በማግኘታቸው ትልቅ እርካታ እንደተሰማቸው ያስረዳሉ፡፡

እነዚህን ምርቶች በመንደር ውስጥ ካሉ ሱቆች ልግዛ ቢሉ ነጭ ሽንኩርት በኪሎ 250 ብር ቀይ ሽንኩርት 140 ብር እንዲሁም ዘይት 2 ሺህ 200 እንደሚገዙ ጠቁመው የቅዳሜና እሑድ ገበያን የመሰሉ በመንግስት ድጋፍ የተጀመሩ የግብይት ሥርዓቶች ሊጠናከሩ ይገባል ብለዋል፡፡

በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ሃያት አደባባይ በሚገኘው በቅዳሜ እና እሑድ ገበያ የተለያዩ ፍጆታና አስቤዛዎችን ሲሸምቱ ያገኘናቸው ወይዘሮ ሰላም ታደሰ የተባሉ አስተያየት ሰጪም በገበያው በአንድ ቦታ ብዙ አይነት የግብርና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ማግኘታቸው ብቻ ሳይሆን ትኩስና ጥራት ያላቸው ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በመሸመት ተጠቃሚ መሆናቸውን ነው የነገሩን፡፡

የቅዳሜና እሑድ ገበያዎች ድንች፣ ሽንኩርት፣ ጎመን፣ ቲማቲምና መሰል አትክልትና ፍራፍሬዎችን እንደሚሸምቱ የተናገሩት አስተያየት ሰጪዋ በእነዚህ ገበያዎች መንደር ውስጥ ካሉ ሱቆች በተሻለ ዋጋና ጥራት መገበየት ችለናል ባይ ናቸው፡፡

አቶ ወርቅነህ ንብረት ከአምራች ገበሬዎች አትክልትና ፍራፍሬዎችን ተረክበው ለቅዳሜና እሑድ ገበያ ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ከሚሸጡ ነጋዴዎች መካከል አንዱ ናቸው፡፡ እነዚህ ገበያዎች የፍጆታ ዕቃዎችን ለህብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የኑሮ ውድነቱን በመከላከል ረገድ የጎላ አስተዋጽኦ አላቸው ያሉት ነጋዴው እነዚህ ገበያዎች በአቅርቦት፣ በዋጋ እና ጥራት ተደራሽ መሆናቸውን ነው ያረጋገጡት፡፡

ገበያዎቹ የተቋቋሙበት ዋና አላማ ትኩስ፣ ጥራት ያላቸውና ለጤና ተስማሚ የሆኑ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለሸማቹ በማቅረብ የኑሮ ውድነትን ማቃለል እንደሆነ ጠቅሰው፤ ምርቶቹን ከሚረከቡበት ዋጋ በተወሰነ መልኩ የትራንስፖርትና የጫኚ አውራጅ ታሳቢ በማድረግ ለተጠቃሚው እንሚደርስም ተናግረዋል፡፡

ለአብነትም አንደኛ ደረጃ ሽንኩርት ከገበሬ ወይም ከአከፋፋይ ነጋዴ ከ75 እስከ 80 ብር ተረክበው የትራንስፖርትና የሰራተኛ ወጪን ታሳቢ በማድረግ ለተጠቃሚው በ90 ብር እንደሚሸጡ የገለፁት ነጋዴው ከምንም በላይ ደግሞ ወቅትን ታሳቢ ያደረገ ጭማሪ ባለመኖሩ በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡ ለዚህም ለሸማቹ በግልፅ በሚታይ ቦታ የመሸጫ የዋጋ ዝርዝር ለጥፈው እንዲሠሩ ጠቁመው ከሚያመጡት ምርት ላይም በኪሎ ከ5 እስከ 10 ብር ብቻ ጭማሪ እንደሚያደርጉ አስረድተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አሸናፊ ብርሃኑ እንዳሉት በከተማዋ የተረጋጋ የግብይት ሥርዓት እንዲኖር ብሎም የሚያጋጥመውን የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት ለመከላከል የተለያዩ ሥራዎች እየተሰሩ ነው፡፡

በተለይም እለት በእለት ተፈላጊ የሆኑ ምርቶች ለህብረተሰቡ ተደራሽ ይሆኑ ዘንድ በቅዳሜና እሁድ ገበያዎች፣ በከተማዋ መግቢያ በሮች በተገነቡ የግብርና ምርቶች መሸጫ ማዕከል እንዲሁም በሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበራት እና ዩኒየኖች ጭምር የኢንዱስትሪና የግብርና ምርቶች በስፋት እየቀረቡ ነው፡፡

እንደ ከተማ ከግብይት ሰንሰለት ጋር በተያያዘ እያጋጠመ ያለውን ችግር ለማቃለል የአምራችና ሸማቾችን ቀጥታ ግንኙነት ለማጠናከር የተሰራው ሥራ ተጠቃሽ ነው ያሉት አቶ አሸናፊ ከነዚህም ዋንኛው የቅዳሜና እሑድ ገበያዎችን ማጠናከር እና ትልልቅ የገበያ ማዕከል ማስገንባት ሥራ ማስጀመር መቻሉ ዋንኛው ነው ብለዋል፡፡

አሁን ላይ መላው የከተማዋ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ በአሥራ አንዱም ክፍለ ከተማ በሚገኙ 119 ወረዳዎች የተቋቋሙ 264 የቅዳሜና እሑድ ገበያዎች አሉ፡፡ በእነዚህም አስፈላጊ የሆኑ የግብርናና የፋብሪካ ምርቶች በጥራት እየቀረቡ ነው ብለው፤ ቢሮው ባስቀመጠው ደረጃ መሠረት ግብይት እየተከናወነ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ በከተማዋ በስፋት እየተከናወነ ያለው የከተማ ግብርና ስራም የኑሮ ውድነትን ለመከላከልና የመዲናዋን የገበያ ዋጋ በማረጋጋት ረገድ አይነተኛ ድርሻ እንዳለው አረጋግጠዋል፡፡

የአዲስ አበባ የቅዳሜና እሑድ ገበያዎች ከምርት እጥረትና አቅርቦት ብቻ ሳይሆን ከነፃ ገበያ አንፃር 20 በመቶ ቅናሽ ተደርጎ የግብይት ሥርዓት እንዲከናወን የሚደረግባቸው ናቸው፡፡ ለዚህም ቢሮው በየሳምንቱ የገበያ ጥናት እያደረገ የምርቶችን የዋጋ ዝርዝር ሸማቹ ሊመለከት በሚችል ቦታ እንዲለጠፍ ያደርጋል፡፡

የቅዳሜና እሑድ ገበያዎች፣ እስከ አሁን ባለው ሂደትም የህብረተሰቡን ማህበራዊ ደህንነት የሚጠብቁ፣ የኢኮኖሚ ሸክም የሚያቀልሉ እና የንግድ ፍትሃዊነትን የሚያረጋግጡ ጠቃሚ የገበያ አማራጮች መሆናቸውን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ የከተማዋ ነዋሪዎችም የዚህ ዕድል ተጠቃሚ በመሆን ጤናማ ግብይት እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

## ፅዳትን ... ከገጽ 1 የዞረ

በአሁኑ ወቅት ግን ቱቦዎች በመሸፈናቸው እና ህብረተሰቡም ያለአግባብ ቆሻሻ ከመጣል በመቆጠቡ እንዲህ አይነት ችግር በአብዛኛው እንደማይስተዋል ይገልጻሉ።

እንደ ወይዘሮዋ ገለጻ፣ ለዚህ ትልቅ ለውጥ መምጣት ቀዳሚው ምክንያት የኮሪደር ልማት ነው፡፡ ልማቱ ከምንም በላይ የዕለት ተዕለት የፅዳት ስራውን ቀላል አድርጎታል፡፡ ለውጡም በመሠረተ ልማት ብቻ የተገደበ ሳይሆን በህብረተሰቡ ዘንድም በአስተሳሰብ ጭምር የሚታይ ነው፡፡ ቆሻሻን በአግባቡ በማስወገድ ረገድ ያለው ግንዛቤ እያደገ መጥቷል።

ቀደም ሲል ብዙጊዜ ሰዎች የውሃ መያዣ ፕላስቲኮችን፣ ፌስታሎችንና የተለያዩ ቆሻሻዎችን በዘፈቀደ ጥለው ይሄዱ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን በየመንገዱ ዳር በተቀመጡት የቆሻሻ መጣያዎች (ደስት ቢን) በአግባቡ እንደሚያስቀምጡ በመጥቀስ፣ የታየው ለውጥ እጅግ ደስ የሚል መሆኑንም አስረድተዋል፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 የፅዳት ስራ የሚያከናውኑት ወይዘሮ እጅጋየሁ ቡልቡላ፣ ማህበረሰቡ ቆሻሻን በአግባቡ ለይቶ የመያዝና የማስወገድ ልምዱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን ይመሰክራሉ። የፅዳት ሰራተኞችም ከህብረተሰቡ ጋር በመቀናጀት የሚሰሩባቸውን አካባቢዎች ንጹህና ማራኪ ለማድረግ በትጋት እየሠሩ ይገኛሉ፤ ውጤቱም በጣም አበረታች እንደሆነ ተናግረዋል።

አብዛኛው ህብረተሰብ ለፅዳት ትኩረት እየሰጠ ቢሆንም፣ አሁንም አንዳንድ ችግሮች መኖራቸውን ወይዘሮዋ አልሸሸጉም፡፡ አንዳንድ በሌሊት ቆሻሻን በፌስታል አድርገው በዘፈቀደ የሚጥሉ ሰዎች አሉ፡፡ ህብረተሰቡ ቆሻሻን በዘፈቀደ ከመጣል በመቆጠብ ለከተማዋ ፅዳትና ውበት የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 በተለምዶ እምቢልታ ሆቴል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚኖሩት ወይዘሮ ዘያዳ ኑረዲን በበኩላቸው፣ አዲስ አበባ አሁን ላይ ንጹህና ውብ ገጽታን እየተላበሰች ነው። አካባቢያቸውም በፅዳት ሰራተኞችና በህብረተሰቡ የጋራ ተሳትፎ ንጹህ እየሆነ መጥቷል። በየሳምንቱ ቅዳሜ ቅዳሜ ነዋሪዎች እየወጡ በሚያደርጉት አካባቢ ጽዳት ላይ በንቃት በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ።

"እኔ አካባቢዬ ጽዱ እንዲሆን ወደኋላ ብዬ አላውቅም፤ በዚህም በጣም ደስተኛ ነኝ። ከቤቴ ፊት ለፊት የነበረውን የቆሻሻ መከማቻ አጽድቼ አትክልቶችን በመትከሌ አሁን ቦታው አረንጓዴ ሆኗል። አካባቢዬ ጽዱና አረንጓዴ ሆኖ ሳይ ከፍተኛ ደስታና እርካታ ይሰማኛል" ይላሉ፡፡

ከዚህ ባሻገር አሁንም በውሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች እንዲሁም በመንገዶች ላይ እንደ የሙዝ ልጣጭ ያሉ ቆሻሻዎችን በዘፈቀደ የሚጥሉ እንዳሉ ትዝብታቸውን ያጋሩት ወይዘሮ ዚያዳ፣ ፅዳት የስልጣኔ ምልክትና ጥቅሙ ለሁላችንም መሆኑን በመገንዘብ በአግባቡ መያዝና ማስወገድ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡



ፎቶ ፦ ከፋይል

በተለያዩ የአዲስ አበባ አካባቢዎች የፅዳት ሰራተኞች እና ህብረተሰቡ የጽዳት ስራ ሲያከናውኑ

**ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ራሱን የቻለ መዋቅርና መመሪያ ተዘጋጅቶለት፣ ስራውን የሚሰሩ ማህበራት ተደራጅተው፣ የድጎማ ስርዓት ተዘርግቶ ወደ ስራ በመገባቱ በየወንዙና በውሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች ሲጣሉ የነበሩ የፕላስቲክ፣ ወረቀት፣ ካርቱንና ሌሎች መልሰው ጥቅም ላይ ሊወሉ የሚችሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን በአግባቡ መሰብሰብ ተችሏል**

### እንደ ከተማ ምን እየተሰራ ነው?

የአዲስ አበባ ከተማ ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በ2022 ዓ.ም አዲስ አበባን ፅዱ እና ለነዋሪዎቿ ምቹ የማድረግ ርዕይ ሰንቆ እየሰራ ይገኛል። ለዚህም በርካታ ስራዎች እያከናወነ እንደሚገኝ የኤጀንሲው ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሙላት ተገኝ ለዝግጅት ክፍላችን አብራርተዋል፡፡

ከአምስት ዓመት በፊት ከተማዋ አሁን በምትታየው መልኩ አልነበረችም። ከፍተኛ የፅዳት መጓደል ይታይባት ነበር። በተጨማሪም ህብረተሰቡ በፅዳት ስራው የነበረው ተሳትፎ ዝቅተኛ፣ ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ለመልሶ መጠቀም የሚውለው እዚህ ግባ የማይባል እንደነበር አቶ ሙላት ያነሳሉ፡፡

እነዚህ ችግሮች እያሉ ከተማዋን ፅዱ ማድረግ ስለማይቻልም፤ የህብረተሰቡን ተሳትፎ እና ለመልሶ መጠቀም የሚውለውን ደረቅ ቆሻሻ ለማሳደግ ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ፅዳትን ባህል ማድረግ ግንዛቤ ከመፍጠር እንደሚጀምር የሚያነሱት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አቶ ሙላት፣ ከዚህ አኳያ ተቋሙ ከማዕከል እስከ ወረዳ ባለው መዋቅር "የግንዛቤና የህብረተሰብ ተሳትፎ" በሚል መዋቅርና አደረጃጀት በመፍጠርና ተገቢውን ባለሙያ በመመደብ ወደ ስራ ገብቷል፡፡

በከተማዋ በሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች ከ2 ሺህ በላይ የግንዛቤ ፈጠራ ባለሙያዎች እንዲኖሩ ተደርጓል። ባለሙያዎቹ ቤት ለቤት በመዞር ማህበረሰቡ ቆሻሻን በአግባቡ እንዲይዝና እንዲለይ የማስተማር ስራ እየሰሩ ይገኛል፡፡ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክን ጨምሮ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም፣ በቡና ጠጡ መድረኮች፣ ሰዎች በብዛት በሚንቀሳቀሱባቸው በዋና ዋና አደባባዮችና መንገዶች ፊት ለፊት፣ በየሳምንቱ ብሎክን መሰረት አድርጎ በሚደረጉ የንቅናቄ ስራዎች፣ በየሳምንቱ አርብ በትምህርት ቤቶች የፅዳት ንቅናቄ እና በሌሎች መንገዶች ህብረተሰቡ ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አስተዳደር ጋር በተያያዘ ግንዛቤ እንዲኖረው እየተሰራ እንደሚገኝ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አቶ ሙላት ያስረዳሉ፡፡

ከባለፈው ዓመት ጀምሮ ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የጋራ መግባቢያ ስምምነት በማድረግ፣ የአካባቢ ጥበቃና ንጽህና ክበባት ተቋቁመው በትምህርት ቤት ፅዳትን ባህል የማድረግ አስተሳሰብ ለመፍጠር እየተሰራ ነው፡፡ ልጆች ከታች ጀምሮ ንጽህናን እያወቁ እየተገበሩ ሲሄዱ ውጤቱም በሂደት እየታየ ይመጣል ይላሉ፤ አቶ ሙላት፡፡

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚገልጹት፣ እስከአሁን የከተማዋን ፅዳት በማስጠበቅ፣ የሚመነጨውን ቆሻሻ በአግባቡ ለይተው እንዲይዙና እንዲያስወግዱ ለነዋሪዎች በተሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ የአገልግሎት ለውጥ መጥቷል፡፡ ለዚህም በአሁኑ ወቅት የኮሪደር ልማት የተከናወነባቸውና ዋና ዋና መንገዶች ያሉባቸው አካባቢዎች እንደ ከዚህ ቀደሙ ቆሻሻ አይደሉም፤ የንፅህና ጉድለት የሚታይባቸው አይደሉም፡፡ የፍሳሽ መተላለፊያ መስመሮች፣ የወንዝ ዳርቻዎች፣ ከማኑኾሎች (የፍሳሽ ማስወገጃ፣ የውሃ ቧንቧ፣ የኤሌክትሪክ ወይም የቴሌኮም መስመሮችን ለመፈተሽ፣ ለመጠገን እና ለማፅዳት የሚያስችል የመሬት ውስጥ መተላለፊያ በር) እንደ ድሮው ቆሻሻና የሚሰነፍጥ ሽታ አያመነጩም። ማህበረሰቡም በጉልበትና በገንዘብ ተሳትፎ በማድረግ በየአካባቢው ያሉ ብሎኮችን ሞዴል አድርጓል፡፡

ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ውስጥ ለመልሶ መጠቀም የሚውለውን መጠን በማሳደግ የሚሰራው ስራ የፅዳት ባህል ለውጥ ማሳያ እንደሆነ አቶ ሙላት ያነሳሉ፡፡ በከተማዋ ከሚመነጨው ቆሻሻ ውስጥ 70 በመቶ የሚሆነው የሚበሰብስ እና ለመልሶ መጠቀም መዋል የሚችል ነው፡፡ ነገር ግን ከሀገራዊ ለውጡ በፊት ይህንን ቆሻሻ ወደ መልሶ መጠቀም በመቀየር ረገድ የተሰራው ስራ እዚህ ግባ የማይባል ነበር፡፡ ኤጀንሲው ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ስራውን የሚከታተል ራሱን የቻለ መዋቅርና መመሪያ ተዘጋጅቶለት፣ ስራውን የሚሰሩ ማህበራት ተደራጅተው፣ የድጎማ ስርዓት ተዘርግቶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በዚህም በየወንዙና የውሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች ሲጣል የነበረ የፕላስቲክ፣ ወረቀት፣ ካርቱንና ሌሎች መልሰው ጥቅም ላይ ሊወሉ የሚችሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን በአግባቡ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ወደ 15 በመቶ የሚሆነው ለመልሶ መጠቀም እየዋለ ይገኛል፡፡ በ2018 በጀት ዓመት ብቻ በመልሶ መጠቀም የተደራጁ ማህበራት 3 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ አግኝተዋል፡፡ የሚጣል፣ የሚቃጠልና የሚቀበር የነበረውን ቆሻሻ ወደ ሀብት መቀየር መቻሉ ትልቅ የባህል ለውጥ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ፅዳትን ባህል ለማድረግ በማህበረሰቡ ዘንድ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ለምሳሌ የሃይማኖት አባቶችንና እድሮችን በማሳተፍ ትልቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ ቆሻሻ በዘፈቀደ መጣል ወንጀል እንደሆነ፤ ከሃይማኖት አኳያም ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የእምነት አባቶች ምዕመኑን እንዲያስገነዝቡ ተደርጓል፡፡ በጥቅሉ ከ629 ሺህ 800 በላይ አባወራዎችና እማወራዎችን በፅዳት ስራው በማሳተፍ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ከመፍጠር አኳያ ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ የከተማው ነዋሪ በፅዳት ዙሪያ ግንዛቤ አለው። የሚያውቀውን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ግን ጉድለቶች እንዳሉ ያነሱት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፣ ለዚህም በህገ-ወጥ መንገድ ቆሻሻ በማስወገድ የከተማዋን ፅዳት የሚያጓድሉ አካላት ተጠያቂ የሚያደርግ ደንብ ቁጥር 167/2016 እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም

# ለዘመናት ችግሮች የመፍትሔ ትልም

## (ክፍል ሁለት)



በአሌክስ ብርሀኑ (የሰላምና ደህንነት መምህር እና ተመራማሪ)

ኢሜል፡- alexbirhanu81@gmail .com

ውድ አንባቢዎቻችን፤ ባለፈው ዕትማችን በዋናው ርዕስ ስር የንጉሣዊው ዘመን፣ የሥርዓቱ የረጅም ጊዜ ተፅዕኖ እንዲሁም የደርግ ሥርዓት ፖሊሲዎች፣ ተፅዕኖዎችና ውጤቱ በሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች የጸሐፊውን ሰፊ ማብራሪያ ማቅረባችን ይታወሳል። የጽሁፉን ሁለተኛ ክፍል በሚከተለው መልኩ አቅርበንላችኋል፤ መልካም ንባብ፡፡

### የኢሕአዴግ ዘመን አስተዳደር ለውጦች እና ያልተፈቱ መለያየቶች

የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) ከግንቦት 1983 ዓ.ም. እስከ ሕዳር 2012 ዓ.ም. ድረስ ኢትዮጵያን ያስተዳደረ የፖለቲካ ጥምረት ነበር። ይህ ጥምረት የደርግ መንግሥትን ድል ባደረጉ የትጥቅ ትግል ቡድኖች የተመሠረተ ሲሆን፣ እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ ዋና መሪው መለስ ዜናዊ ነበሩ። ሥልጣን ሲይዙ አገሪቱ ከፍተኛ የመፍረስ አደጋ ውስጥ ነበረች፤ የረጅም ጊዜ ጦርነት፣ የሕዝብ መፈናቀል፣ አስከፊ ረሃብ እና በክልሎችና በማዕከላዊ መንግሥት መካከል የተከማቸ አለመተማመን ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ከንጉሣዊው እና ከወታደራዊው ዘመን የተሸጋገሩ የመሬት ፍትሕ፣ የማንነት እውቅና እና አካታች የአስተዳደር ጥያቄዎች አልተፈቱም ነበር።

እነዚህን መሠረታዊ ችግሮች ለመፍታት ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን የመጀመሪያ ፌዴራላዊ ሥርዓት አቋቋመ። ይህ ሥርዓት በ"ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች" መብቶች ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ የብሔር ማንነትን የክልል አስተዳደር መሠረት አድርጎ በሕግ እውቅና ሰጠ። ክልሎች ራሳቸውን የማስተዳደር መብት አገኙ፣ በአማርኛ ቋንቋ ብቻ የተመሠረተውን የቀድሞ አቀራረብ በማስፋት በርካታ የአካባቢ ቋንቋዎች የሥራ እና የትምህርት ቋንቋ እንዲሆኑ ፈቀደ። እያንዳንዱ ማህበረሰብ ቋንቋውን እንዲጠቀም፣ ባህሉን እና የአካባቢውን ጉዳይ እንዲያስተዳድር መብት ተሰጠው። ይህም ለብዙ ዓመታት የትጥቅ ትግል ምክንያት የነበሩ ቅሬታዎችን ለመመለስ የተደረገ እርምጃ ነበር።

በኢኮኖሚ ዘርፍም መንግሥቱ በመንግሥት የሚመራ ልማት ላይ የተመሠረተ ሰፊ ፕሮግራም አስጀመረ። በመንገድ፣ በባቡር፣ በዩኒቨርሲቲዎች፣ በጤና ተቋማት እና በመሠረተ ልማት ላይ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ተደረገ። በገጠር አካባቢዎች የመሠረታዊ አገልግሎት ሽፋን ተስፋፋ፡፡ በዚህም ለብዙ ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተመዝግቧል። ሆኖም መሬት በመንግሥት ባለቤትነት እንዲቆይ ተደረገ፣ የግል ኢንቨስትመንትም በተወሰኑ ዘርፎች ብቻ ተፈቀደ።

ነገር ግን ከእነዚህ ለውጦች ጎን ለጎን ኢሕአዴግ በፖለቲካ ሕይወት ላይ ጠንካራ ቁጥጥር አድርጎ ቀጠለ። በብዙ ክልሎች የተቃዋሚ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ ተገደበ፣ የምርጫ ሂደቱን ገዢው ጥምረት ተቆጣጠረ፣ ከፍተኛ የደህንነት፣ የሀብት አጠቃቀም እና የሹመት ውሳኔዎች በማዕከላዊ አመራር እጅ ቀጠለ።

ተቺዎች ፌዴራሊዝሙ በሰነድ ላይ ብቻ የተገደበ እንደነበር ይገልጻሉ፤ የክልል መሪዎች ከሕዝብ ይልቅ ለማዕከላዊ ፓርቲ አመራር ተጠያቂ ነበሩ ብለው ይከራከራሉ። የተቃዋሚ ፖለቲከኞች፣ ጋዜጠኞች እና አክቲቪስቶች እስር፣ ገደብ እና ማስፈራራት እንደገጠማቸው ይጠቅሳሉ። በተጨማሪም የመሬት ኪራይ ፕሮጀክቶች ሕዝቦችን ማፈናቀላቸው፣ የልማት ጥቅሞች በእኩል አለመከፋፈላቸው እና የወሰን ጉዳዮች አለመፈታታቸው እየጨመረ የመጣ ቅሬታ ፈጠረ።

በመጨረሻው የአስተዳደር ዘመኑ ኢሕአዴግ ተጨባጭ ውጤቶችን አስመዝግቧል፡፡ በአብዛኛው አገሪቱ የነበረውን የጦርነት ሁኔታ አስቆመ፤ የማንነት ጉዳይን በሕገ መንግሥት ደረጃ እውቅና ሰጠ እንዲሁም ቀደምት መንግሥታት ያልደረሱባቸው አካባቢዎች ድረስ መሠረተ ልማት አስፋፋ።

ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ ጥልቅ ያልተፈቱ ችግሮችን ትቶ ሄደ፤ በራስ አስተዳደር ቃል ኪዳንና በማዕከላዊ ቁጥጥር እውነታ መካከል ያለው ልዩነት፣ የመሬትና የወሰን ቅሬታዎች፣ የፖለቲካ ውድድር እጥረት እና ነፃነትና ፍትሕ ላይ የተፈጠሩ ጥያቄዎች ቀጠሉ። እነዚህ ችግሮች ወደ ሰፊ ሕዝባዊ ተቃውሞ ተቀይረው የጥምረቱን መፍረስና አዲስ የብሔራዊ ውይይት ጥረቶች መጀመር አስከተሉ።

### በሦስቱ ዘመናት የተደጋገሙ አዝማሚያዎች፤ የኢትዮጵያ መንግሥታት የቆዩ ቅሬታዎችን እንዴት እንደተመለከቱ

በንጉሣዊው፣ በደርግ እና በኢሕአዴግ መንግሥት ዘመናት ውስጥ በተደጋጋሚ የተነሱ መሠረታዊ ጉዳዮች ተመሳሳይ ነበሩ። እነሱም የመሬት ፍትሃዊ አጠቃቀም፣ የተለያዩ ማንነቶች እኩል እውቅና ማግኘት፣ የሥልጣንና ሀብት ፍትሃዊ ክፍፍል፣ የድንበር ጉዳዮችን በሰላም መፍታት እና በመንግሥትና በሕዝቦች መካከል እምነት መገንባት ናቸው።

እያንዳንዱ መንግሥት ከቀድሞው ሥርዓት የተለያዩ ፖሊሲዎችን አምጥቶ አንዳንዴ አሠራሮችን ቢቀይርም፣ እነዚህን

> "መደመር" ከግጭት ይልቅ ትብብርን፣ ከማግለል ይልቅ ማካተትን፣ ከመከፋፈል ይልቅ ውይይትን የሚያስቀድም አስተሳሰብ ነው

ጥልቅ ችግሮች በሚመለከት ተመሳሳይ አዝማሚያዎች ቀጥለዋል። እነዚህ የተደጋገሙ ቅርጾች ዛሬም ብዙ ቅሬታዎች ለምን እንደቀጠሉ ለመረዳት ወሳኝ ናቸው።

### 1ኛ. መሬትን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ማድረግ

ሦስቱም መንግሥታት የመሬት ዋና ቁጥጥርን በመንግሥት እጅ አቆይተዋል፤ ለሕዝብ ወይም ለግለሰቦች የተረጋጋና ዘላቂ የባለቤትነት መብት ሙሉ በሙሉ አልሰጡም።

በንጉሣዊው ዘመን መሬትን እንደ የንጉሥ ንብረት በመቁጠር ለታማኝ መኳንንትና ሹማምንት ይሰጥ ነበር። ደርግ የፊውዳል የመሬት ሥርዓትን ቢያስወግድም፣ መሬትን "የሕዝብ የጋራ ንብረት" በማለት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር አደረገ። ኢሕአዴግም የመሬት ባለቤትነትን ለመንግሥት አስቀምጦ ለገበሬዎች የመጠቀም መብት ብቻ ሰጠ። በሦስቱም ዘመናት መሬት የሕዝብ ተፈጥሯዊ መብት ከመሆን ይልቅ የመንግሥት የሥልጣን መሣሪያ ሆኖ ቆይቷል። ይህም የመሬት መፈናቀልና የመሬት ዋስትና እጥረት ለረጅም ጊዜ የቁጣና የመከፋፈል ምንጭ እንዲሆን አድርጓል።

### 2ኛ. የብሔራዊ ማንነት ጉዳይን በአንድ አቅጣጫ መወሰን

ሦስቱም መንግሥታት የአገራዊ ማንነት ግንባታን በራሳቸው እይታ ለመወሰን ሞክረዋል፤ ሕዝቦች በጋራ እንዲወስኑ ሙሉ ዕድል አልሰጡም። የንጉሣዊው ሥርዓት አንድ ባህል፣ አንድ ቋንቋ እና አንድ የሃይማኖት ትርክትን እንደ ብቸኛ የኢትዮጵያ ማንነት ለማቅረብ ሞክሯል። ደርግ የብዝሃነትን እውነታ ቢቀበልም፣ በአንድ ወጥ የሶሻሊስት ሀገራዊ ሀሳብ ሥር አስገባው። ኢሕአዴግ የብሔር ማንነትን በሕገ መንግሥት ቢያውቅም፣ የቡድን ጥያቄዎችን አንዳንድ ጊዜ ከገዢው ሥርዓት ጋር በሚኖረው ግንኙነት መሠረት ይመለከት ነበር። ሦስቱም ሥርዓቶች "መዋሃድ ወይም መለያየት" ከሚለው አማራጭ በላይ ሁሉንም ማንነቶች በእኩል ዋጋ የሚያከብር የጋራ አገራዊ ስሜት ለመገንባት ሙሉ በሙሉ አልቻሉም።

### 3ኛ. የማዕከላዊ ቁጥጥር ባህል

ሦስቱም መንግሥታት የሥልጣን ማዕከላዊነትን በተለያየ መልኩ ቀጥለዋል። ንጉሠ ነገሥታቱ ከመዲናዋ በተሾሙ መኳንንትና ባለሥልጣናት አማካይነት ያስተዳድሩ ነበር። ደርግ ሁሉንም ውሳኔዎች በወታደራዊ ምክር ቤቱ እጅ አስገባ። ኢሕአዴግ ፌደራል ሥርዓት ቢያቋቁምም፣ ብዙ ጊዜ የክልል መሪዎች ለማዕከላዊ ፓርቲ አመራር ተጠያቂ ሆነው ቆዩ። በሁሉም ዘመናት የአካባቢ ጥያቄዎች ለማዕከላዊ ሥልጣን ታማኝነት በሚኖረው መጠን ይፈቱ ነበር። ይህም ቃል ከተገባው የሥልጣን መጋራት እና በተጨባጭ ሁኔታ መካከል ክፍተት ፈጠረ።

### 4ኛ. ለተቃውሞ እና ለልዩነት የኃይል ምላሽ መስጠት የተደጋገመ አዝማሚያ መሆን

በሦስቱም የኢትዮጵያ የመንግሥት ዘመናት የተለያዩ የሕዝብ ጥያቄዎችን፣ ተቃውሞዎችን እና የፖለቲካ ልዩነቶችን በውይይት ከመፍታት ይልቅ በኃይል ለመቆጣጠር የመሞከር አዝማሚያ ተደጋግሟል። በንጉሣዊው ዘመን ለመሬት መውረስ፣ ለፖለቲካዊ መገለል እና ለኢፍትሃዊ ግብር የተነሱ ሕዝቦች በወታደራዊ ኃይል ይጨፈለቁ ነበር። የአመፅ እንቅስቃሴዎች በጦር ዘመቻ፣ በቅጣት እና በግዳጅ አገዛዝ ይቆጣጠሩ ነበር። ደርግም በተቃዋሚዎች ላይ ከፍተኛ የጭቆና እርምጃ ወስዷል። የፖለቲካ ተቃውሞዎችን በእስር፣ በግድያ እና በከባድ የደህንነት እርምጃዎች ለመቆጣጠር ሞክሯል። ኢሕአዴግም በተለይ በአንዳንድ የፖለቲካ ቀውሶች ወቅት የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን በገደብ፣ በእስር እና በደህንነት እርምጃዎች ለመቆጣጠር ሞክሯል። ሦስቱም ሥርዓቶች ከፍተኛ ተቃውሞ ከተነሳ በኋላ አንዳንድ ማሻሻያዎችን ቢያደርጉም፣ ተቃውሞን እንደ ሕጋዊ የሕዝብ ድምፅ ለመቀበል በቂ ባህል አልገነቡም። በዚህም የተነሱ ቅሬታዎች በውስጥ ተከማችተው በኋላ በትልቅ ቀውስ መልክ እንዲመለሱ አድርጓል።

### 5ኛ. የግጭት መንስኤዎችን ሳይሆን ውጤቶችን መቆጣጠር

በሦስቱም ዘመናት መንግሥታት ብዙ ጊዜ የግጭት መሠረታዊ ምክንያቶችን ከመፍታት ይልቅ የታዩ ችግሮችን በጊዜያዊ መፍትሄዎች ለመቆጣጠር ተጠቅመዋል። እያንዳንዱ አዲስ መንግሥት ከቀድሞው ያልተፈቱ ችግሮችን ተረክቦ፣ አንዳንድ ለውጦችን በማድረግ አዲስ መዋቅር ገንብቷል፤ ነገር ግን የሥልጣን፣ የመሬት እና የማንነት ጥያቄዎችን በጥልቀት ለመፍታት የሚያስችል ሁሉን አቀፍ ሂደት አላስጀመረም። በተለይም ከታሪካዊ ጉዳቶች፣ መገለሎች እና ግጭቶች በኋላ ሁሉንም ማህበረሰብ የሚያሳትፍ ብሔራዊ ውይይት፣ እውነት መፈለግ እና እርቅ ማድረግ በስፋት አልተካሄደም። ይህም እያንዳንዱ አዲስ መንግሥት የቀድሞ ችግሮችን በአዲስ መልክ እንዲያስተላልፍ አድርጓል።

### ተደጋጋሚ አዝማሚያዎች የሚያሳዩት ትልቁ ትምህርት

እነዚህ ተደጋጋሚ ሁኔታዎች ኢትዮጵያ ዛሬ ያለችበት ችግር በቀላሉ የመሪ ወይም የፖሊሲ ለውጥ ጉዳይ ብቻ እንዳልሆነ ያሳያሉ። ችግሩ ከመቶ ዓመት በላይ የቆየ የሥልጣን፣ የመሬት እና የማንነት አስተዳደር ችግር ነው። በታችኛው ደረጃ ያሉ ሕዝቦች በተሟላ ስምምነት እና ተሳትፎ ውሳኔ እንዲያደርጉ እድል ሳይሰጥ ከላይ በሚመጣ ውሳኔ ብቻ የሚመራ ሥርዓት ሲቀጥል፣ ተመሳሳይ ቅሬታዎች እንደገና ይነሳሉ። ስለዚህ የወደፊቱ የኢትዮጵያ ሰላም የሚወሰነው በማን ሥልጣን ላይ እንዳለ ብቻ ሳይሆን፣ ሥልጣን፣ ማንነት፣ ሀብት እና የጋራ ዕጣ ፈንታ በምን መልኩ እንደሚደራጁ ነው።

### የብልጽግና ፓርቲ የሰላም ርዕይ በብዝሃነት ውስጥ ስምምነትን መገንባት

የብልጽግና ፓርቲ ወደ ሥልጣን የመጣው በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ እጅግ ወሳኝ በሆነ ወቅት ነበር። ፓርቲው የተረከበው ከፍተኛ ብዝሃነትና ሰፊ አቅም ያላት፣ ነገር ግን ለረጅም ጊዜ በተከማቹ የፖለቲካ ቅሬታዎች፣ ባልተፈቱ ታሪካዊ አለመግባባቶች፣ ተደጋጋሚ ግጭቶችና ጥልቅ ማህበራዊ መከፋፈል የተጫነች አገር ነበር። ለብዙ ዓመታት የተካሄዱ የፖለቲካ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# አደጋን ለመከላከል የተዘረጉት የበጎነት እጆች

**• በአዲስ አበባ 650 በጎ ፍቃደኞች በክረምትና በበጋ የትራፊክ ማስተናበር ስራ እየሰሩ እንደሚገኙ ተጠቁሟል**

**በለይላ መሀመድ**

“ለእኛ ለአይነስውራን ከፍተኛ እገዛ እያደረጉልን ነው፡፡ በተለይም የትራፊክ ፍሰት በሚበዛባቸው የእግረኛ ማቋረጫ መንገዶች ላይ መኪናዎችን ያስቆሙልናል፤ እጃችንን ይዘው ያሻግሩናል፡፡ ከማሻገርም ባለፈ በራሳችን መንቀሳቀስ እስከንችልበት የእግረኛ መንገድ ድረስ ይሸኙናል። የሚሰጡን ክብር እና ርህራሄ ደግሞ የበለጠ ያስደስተናል። በዚህም በጎ ፍቃደኞቹ ባሉበት መንገድ በነፃነት እና ያለስጋት እንድንቀሳቀስ ያደርገናል”፡፡ ሲሉ በ6 ኪሎ አካባቢ አግኝተን ያነጋገርናቸው የእይታ ችግር ያለባቸው አቶ ደጀኔ መኩሪያ የበጎ ፍቃድ ትራፊክ አስተናባሪዎች ስለሚሰጧቸው አገልግሎቶች ይገልፃሉ፡፡

አቶ አደም መሀመድኑር የተባሉት አሽከርካሪም የበጎ ፍቃድ ትራፊክ አስተናባሪዎች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ነው የገለጹልን፡፡ በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች በተለይም የሰዎች እንቅስቃሴ በሚበዛባቸው ሰፈሮች እና የስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት የትራፊክ ፍሰቱ በጣም ይጨናነቃል። የበጎ ፍቃድ ትራፊክ አስተናባሪዎች በሚሰማሩባቸው መስመሮች ሁሉ የተሽከርካሪዎች ፍሰት ይቀላጠፋል፡፡ የትራፊክ ፍሰቱ እንዳይስተጓጎል እግረኞች ሰብሰብ ብለው እንዲሻገሩ በማድረግ ረገድ በጎ ፍቃደኞች የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ የሚደነቅና የሚበረታታ እንደሆነ ይገልጻሉ። እግረኞች በሚሻገሩበት ወቅት ገና ከሩቅ ምልክት እየሰጡ አሽከርካሪዎች ፍጥነታቸውን እንዲቀንሱ የሚያደርጉት ጥረት አደጋ እንዳይከሰት አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው። በዋናነት ደግሞ ድጋፍ የሚፈልጉ አረጋውያን፣ ህፃናት እና ሌሎች አካል ጉዳተኞችን ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ መንገድ እንዲያቋርጡ ከማገዛቸውም ባለፈ ለአሽከርካሪዎችም እፎይታ እንደሚሰጡ ነው ሀሳባቸውን ያጋሩን፡፡

ወይዘሮ አልማዝ ገብረየስ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በጉለሌ ክፍለ ከተማ በተለያዩ አካባቢዎች በትራፊክ ማስተናበር ስራ እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ በተጠቀሰው ዓመተ ምህረት ሽሮ ሜዳ ላይ በተከሰተ የትራፊክ አደጋ ምክንያት ብዙ ሰዎች ላይ ጉዳት ደርሶ ማየታቸው ወደ አገልግሎቱ እንዲገቡ ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡

እሳቸው ይህን የማስተናበር ስራ በሰሩባቸው አካባቢዎች ምንም አይነት የትፊክ አደጋ ተከስቶ እንደማያውቅ የሚገልጹት ወይዘሮ አልማዝ፣ “አንድ አሽከርካሪ ምንም አይነት ችግር ሳያደርስ በሰዓቱ ወደ መድረሻው ሲደርስ እንዲሁም አንድ እግረኛ መንገዱን በደህና ሲያቋርጥ የማየው ደስታ ለምሰራው ስራ ትልቅ ምላሽ ነው። በተለይ ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ እግረኞች እንዳይጨነቁና የትራፊክ ፍሰቱ እንዳይቋረጥ ከማስተባብራቸው 60 በጎ ፈቃደኞች ጋር በመሆን የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ። ይህም በትራፊክ መዘጋጋት



ፎቶ፡- ለይላ መሀመድ

የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎች በትራፊክ ማስተናበር ስራ ላይ

ምክንያት የሚባክነውን የሰዎች ጊዜ፣ ጉልበት እና የነዳጅ ወጪ በትንሹም ቢሆን የሚያቃልል በመሆኑ መሳተፌ ደስታ ይፈጥርልኛል” ብለዋል።

ሌላኛው አስተያየት ሰጪ አለሙ ሀይሌ ይባላል፡፡ እግረኞች ደህንነት ተሰምቷቸው እንዲሻገሩ በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ትራፊክ ማስተናበር ላይ የበኩሉን ሚና እየተወጣ ነበር ያገኘነው፡፡ በእንዲህ አይነቱ የበጎነት ተግባር በቋሚነት ማገልገል ከጀመረ ዘንድሮ ሁለተኛ ዓመቱ ቢሆንም አቅመ ደካሞችን መንገድ የማሻገር አልፎ ተርፎም እቃቸውን ተሸክሞ ማገዝና መሸኘት የመሳሰሉት የአገልጋይነት ስሜት ልምዱ የቆየ የልጅነት ባህሉ መሆኑን ያስታውሳል፡፡

ይህን አገልግሎት በመከወን አሽከርካሪዎችና እግረኞች በሰላም እንዲጓዙ የበኩሏን ሚና በመጫወት ላይ የምትገኘው ሌላዋ በጎ ፍቃደኛ መስከረም ከበደ ትባላለች፡፡ ለዚህ ስራ ምክንያት የሚደርሱ የመኪና አደጋዎችና የሚያስከትሉት መዘዝ እንዲሁም ዓይነ ስውራን መንገድ ለመሻገር ሲቸገሩ ማየቷ ነው፡፡ ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ ሰዎች በፍጥነት ወደየቤታቸው ለመድረስ ይፈልጋሉ። በተመሳሳይ ተሽከርካሪዎችም ወደየመዳረሻቸው ለመሄድ ይጣደፋሉ። ይህም የትራፊክ ፍሰቱን የበለጠ እንዲጨናነቅ ያደርገዋል። እንዲህ አይነቱን ክስተት በትዕግስት በመቆም የትራፊክ ፍሰቱ እንዲስተካከል ከሌሎች ጓደኞቿ ጋር ሆና የበኩሏን አስተዋጽኦ እያደረገች መሆኗን አብራርታለች፡፡

“በጎ ፍቃደኛ ሆኜ በትራፊክ ማስተናበር ላይ መሳተፌ ለእኔ ትልቅ ኃላፊነትና ኩራት ይሰማኛል” የምትለው መስከረም፣ ህግ ጥሰው የሚሄዱ አንዳንድ ሰዎች አሉ፡፡ ይህን በማድረጋቸው

> **“እግረኞች በሚሻገሩበት ወቅት ገና ከሩቅ ምልክት እየሰጡ አሽከርካሪዎች ፍጥነታቸውን እንዲቀንሱ የሚያደርጉት ጥረት አደጋ እንዳይከሰት አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው”**

ራሳቸውን ለአደጋ ስለሚያጋልጡ ከዚህ ድርጊት ቢቆጠቡ ጥሩ መሆኑን ገልጻለች።

በጎ ፍቃደኛ የትራፊክ አስተናባሪዎች ለትራፊክ መሳለጥ እያበረከቱት ያለው አበርክቶ ምን እንደሚመስል የዝግጅት ክፍሉ ላነሳው ጥያቄ የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር ወይዘሮ ገነት ዲባባ ምላሽ ሲሰጡ፤ የክረምት በጎ ፍቃድ ትራፊክ አስተናባሪዎች ከፍተኛ እገዛ እያደረጉ እንደሆነና ተቋሙ በክረምት እና በበጋ የትራፊክ ማስተናበር ስራ የሚሰሩ 650 በጎ ፍቃደኛ መኖራቸውን ጠቁመዋል፡፡

እነዚህን በጎ ፍቃደኞች ወደዚህ ስራ እንዲገቡ የተደረገበት ምክንያት የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር መስመር መዘርጋትን መነሻ ተደርጎ ነው፡፡ መንገደኞች ወደ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት ለመሳፈር ሲሻገሩ ያጋጥም የነበረውን ችግር ለመፍታ በወቅቱ 100 አስተናባሪዎችን ከለገሀር እስከ እስጢፋኖስ ድረስ ወደ ሳሪስና አያት በሚወስደው የእግረኛ ማቋረጫዎች ላይ እንዲሰማሩ በሙከራ ደረጃ ተጀመረ፡፡ እነዚህ የበጎ ፍቃድ አስተናባሪዎች በተሰማሩበት አካባቢ አደጋ የመከሰቱ ችግር እየቀነሰ በመምጣቱ በሂደት ህዝብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች፣ በገበያ ስፍራዎች እንዲሁም ሀይማኖታዊ ተቋማት ባለባቸው አካባቢዎች በጎ ፍቃደኞች እንዲሰማሩ ተደረገ፡፡ አሁን ላይ ቁጥራቸውም አድጎ ወደ 650 ሊደርስ ችሏል ብለዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፣ በበጋው መርሃ ግብር እነዚህ በጎ ፈቃደኞች በተለያዩ ቦታዎች በስራ መግቢያ እና መውጫ ሰዓት ባስተናበሩበት ወቅት የትራፊክ እንቅስቃሴው ሰላማዊ ከመሆኑም በላይ ምንም አይነት የትራፊክ አደጋ አይደርስም። ይህ የበጋ የትራፊክ ማስተናበር የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ልምድና ተሞክሮ እያደገ በመምጣቱ የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ተጀምሯል፡፡ ከክረምቱ የአየር ፀባይ ጋር በተያያዘ የሚደርስ የትራፊክ አደጋን መከላከልና የሰውን ልጅ ህይወት እንዲሁም የንብረት ውድመት የማዳን ስራ ተጠናክሮ እንዲሰራ ያለመው ይኸው አገልግሎት የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን ከአዲስ አበባ ህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ጋር በመተባበር እየተሰራ ይገኛል፡፡

በየዓመቱ በክረምት ወቅት በበጎ ፍቃድ የሚከናወነው የትራፊክ ማስተናበር ስራ በኮሚሽኑ እየተመራ ያለ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን በኮሚሽኑ በኩል ለሚመጡት በጎ ፍቃደኞች እግረኛንና ተሽከርካሪን እንዴት ማስቆም እንዳለባቸው የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና ይሰጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ልምድ ካላቸው የበጋ በጎ ፍቃደኞች ጋር እንዲሰሩ በማድረግ በስልጠና ያገኙትን ክህሎት እንዲያዳብሩ ይደረጋል፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ በቀጥታ የበጋ በጎ ፍቃደኞች መሸፈን በማይችሉባቸው አካባቢዎች በማሰማራት የማስተናበር ስራ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

ዳይሬክተሯ አክለው እንደገለጹት፤ እነዚህ በጎ ፍቃደኞች በዚህ መልኩ በየቦታው መሰማራታቸው ለህብረተሰቡም ሆነ ለተቋሙ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ ስራው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይፈልጋል፡፡ የባለስልጣኑ ሰራተኞች በቦታው ላይ ሄደው ምን ያህል እገዛ እንዳደረጉ ያያሉ፡፡ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በተለይም ከክረምት ወቅት ጋር በተያያዘ በአስፋልት መርጠብ ሳቢያ ጎማ ሊንሸራተት ስለሚችልና አንዳንድ እግረኞች በኮፍያና በጃንጥላ ተከልለው ስለሚሄዱ አደጋ የመከሰት እድሉ ሰፊ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በጎ ፈቃደኞቹ የሚጫወቱት አዎንታዊ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

የበጎ ፍቃደኞች ተሳትፎ ብቻውን የትራፊክ ችግርን ሊፈታ አይችልም። አሽከርካሪዎች በዝናብ ወቅት ፍጥነታቸውን መቀነስ፣ የትራፊክ ህጎችን ማክበርና የበጎ ፍቃደኞችን መመሪያ መከተል ይጠበቅባቸዋል። እግረኞችም በተመረጡ መሻገሪያዎች መጠቀምና ከመኪና ጋር ከሚያጋጭ እንቅስቃሴ መቆጠብ አለባቸው። ትንሽ ትዕግስት፣ ትብብርና የህግ አክብሮት በክረምት ወቅት ትራፊክን የበለጠ ለማሳለጥ ያስችላል ሲሉ ዳይሬክተሯ መልእክት አስተላልፈዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ቡድን መሪ አቶ ቢኒያም ጊቻ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየወሩ የሚቀርብ

# ከማስመረቅ የተሻገረው የኮሌጁ ተግባር



ፎቶ፦ ከፋይል
የ2018 ዓ.ም ተመራቂዎች ከቀጣሪ ድርጅቶች ጋር የስራ ትስስር ባደረጉበት ወቅት



ፎቶ ፦ ከፋይል
የተለያዩ ድርጅቶች ከኮሌጁ ጋር ምሩቃንን ለመቅጠር የሚያስችል ትስስር ፈጥረዋል

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ወጣት ፋሲካ ጋሻው በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በሆቴልና ቱሪዝም ትምህርት ክፍል ከሁለት ዓመት ስልጠና በኋላ በቅርቡ ተመርቃለች፡፡ ተመራቂዋ ስራን በመፈለግ ያባከነችው ጊዜ እንደሌለ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጻለች፡፡ በኮሌጁ በተፈጠረው የሥራ ዕድል ፈጠራና ትስስር ቀጥታ ወደ ስራ ገብታለች፡፡

ፋሲካ በአሁኑ ወቅት በሸራተን ሆቴል ተቀጥራ እየሰራች ትገኛለች፡፡ "በኮሌጁ የተደረገልን ትስስር ተመርቄ ስራ አገኝ ይሆን? የሚለውን ስጋት አስቀርቶልኛል። ይህም የቀሰምኩትን እውቀት በተግባር ለማዋል እና ሙያዊ ብቃቴንም ይበልጥ ለማዳበር እድል ሰጥቶኛል፡፡ ቀጣይ ለምደርስበት ህይወትም መነሻዬ ነው" ስትል ስለተመቻቸላት ዕድል ምስጋና አቅርባለች፡፡

ሌላኛው የኮሌጁ የ2018 ተመራቂ ወጣት ወንድማገኝ አለሽኝ፣ "በኮሌጁ በዌብ ማበልፀግና የዳታ ቤዝ አስተዳደር ዘርፍ ለሶስት ዓመት ሰልጥኛለሁ፡፡ እንደተመረቅኩም ኮሌጁ ባመቻቸልኝ የስራ ዕድል በሰለጠንኩበት ሙያ 'ሞቲ ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር' ተቀጠርኩ፡፡ ይህ ለእኔ ትልቅ እድል ነው፡፡ ወደፊትም ከድርጅቱ ጋር ያለኝን የስራ ትስስር በማጠናከርና የቻልኩትን ሁሉ በመስራት ህይወቴን ለመለወጥ እጥራለሁ" ሲል ኮሌጁ ባደረገው ነገር ደስተኛ መሆኑን ነግሮናል።

አቶ ሙሉጌታ ጋሻው በኮሌጁ የስራ ትስስርና ጋይዳንስ ካውንስሊንግ አስተባባሪ ናቸው፡፡ ኮሌጁ በቅርቡ የመቶኛ ዓመት የምሥረታ በዓሉን ያከበረ ሲሆን በ2018 ዓ.ም ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ሰልጣኞችን በቀጥታ ከሥራ ገበያው ጋር የሚያስተሳስር የሥራ አውደ ርዕይ ማካሄዱን አስታውሰዋል፡፡

ኮሌጁ ሰልጣኞችን አሰልጥኖ ከማስመረቅ ባለፈ የስራ እድል ፈጠራ እና ትስስር መፍጠር መቻሉ፣ ቀጣሪው ሰራተኛ፣ ተቀጣሪው ስራ አጥቶ ከመንገላታት ለመታደግ አስችሏል፡፡ ይህም ሰልጣኞቹ በሰለጠኑበት የሙያ መስክ ስራ እንዲያገኙ፣ ቀጣሪውም የሚፈልገውን ባለሙያ እንዲያገኝ ማድረግን ያለመ መሆኑን አብራርተዋል።

እንደ አስተባባሪው ገለጻ፣ ኮሌጁ በቴክስታይል ጋርመንት፣ ሆቴል መስተንግዶ፣ አውቶሞቲቭ፣ ኮንስትራክሽን፣ ኤሌክትሪካል፣ ኤስቴቲክስ፣ በኮምፒዩተር ቴክኖሎጂ (ICT)፣ በፋይናንስ፣ በከተማ ግብርና እና በመሳሰሉት የትምህርት ክፍሎች ለሰልጣኞች ስልጠና እየሰጠ ይገኛል። 11 በሚደርሱት ዲፓርትመንቶች ስር 42 የሚጠጉ የሙያ ዘርፎችም አሉ። በእነዚህ የሙያ ዘርፎች 967 ሰልጣኞችን አሰልጥኖ በዚህ ዓመት አስመርቋል፡፡

እነዚህን ሰልጣኞች ከሆቴሎች ለምሳሌ ኃይሌ ግራንድ ሞል፣ ሸራተን፣ ኢሊሌ፣ ሂልተን፣ ከሮያል ቢዝነስ ግሩፕ፣ ከሞቲ ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ የኢትዮጵያ ሞተርና ኢንጂነሪንግ ኩባንያ (ሞኤንኮ) ጋር የማስተሳሰር ስራ ተሰርቷል፡፡ በትስስሩ መሰረት የተቀጠሩ፣ እየተቀጠሩ

> በቴክኒክና ሙያው ዘርፍ ትልቁን ሚና ሊጫወቱ የሚገባቸው ኢንዱስትሪዎች ናቸው። የሚፈለገውን ባለሙያ የብቃት ደረጃ ማውጣት እንዲሁም የብቃት ምዘና መመዘን ይጠበቅባቸዋል። እነዚህን ነገሮች ለማምጣት ደግሞ ኮሌጁ የስራ እድል ፈጠራና የትስስር ስራዎችን እየሰራ ነው

ያሉ እና ወደፊትም የሚቀጠሩ አሉ። በኮሌጁ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀውና ከአንድ ሺህ በላይ ዜጎችን የስራ ዕድል ተጠቃሚ ያደርጋል ተብሎ የሚጠበቅ የትስስር መድረክ ሐምሌ 9 ቀን 2018 ዓ.ም ተደርጓል፡፡ በመድረኩም በዋናነት ቀጣሪና ተቀጣሪን በአንድ ጣሪያ ስር በማገናኘት ሰልጣኞች ሥራ ፍለጋ የሚንከራተቱበትን እንዲሁም አሠሪዎች ለቅጥር ማስታወቂያ የሚያወጡትን ጊዜና ወጪ ለመቀነስ ያለመ ስራ ለመስራት መግባባት ተደርሷል።

በመድረኩ ላይም 35 ድርጅቶች የተገኙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ከ16 በላይ ድርጅቶች ሰልጣኞችን መቅጠር ጀምረዋል፡፡ ይህ አሰራር ለቀጣሪውም ሆነ ለተቀጣሪው ፋይዳው የጎላ ነው። ይህም ሲባል ተቀጣሪዎች ከተመረቁ በኋላ ረጅም ጊዜያቸውን ስራ በመፈለግ እንዳያጠፉ ያደርጋቸዋል፡፡ በሰለጠኑበት የሙያ ዘርፍ ስለሚቀጠሩም ደስተኛና ውጤታማ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል። በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ ያግዛቸዋል፡፡ "ምን ልስራ? ወይም እንዴት ልኑር?" የሚል ጭንቀታቸው ስለሚወገድ በስነ ልቦና የተረጋጋ ህይወትን እንዲመሩም ያስችላቸዋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣሪ ድርጅቶች የሰለጠኑ ሰራተኞችን በቀላሉ ያገኛሉ። በስራ ላይ ያሉት ሰልጣኞችም ክፍተት ሲኖርባቸው ኮሌጁ ድጋሚ የማሰልጠን ኃላፊነት ስላለበት በእውቀት በበቂ ሰራተኞች ስራቸውን እንዲያሰሩ ያደርጋቸዋል፡፡ የቅጥር ማስታወቂያ ለማውጣት የሚያባክኑት ጊዜና ገንዘብ ይቀንሳል፡፡ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራትም ምርታማነትን ያሳድጋል።

በአጠቃላይ፣ ኮሌጁ ለተመራቂዎች የስራ ዕድል ፈጠራና ትስስር ማመቻቸቱ ከኢንዱስትሪዎች ጋር ያለውን ትስስር ያጠናክራል፣ የትምህርት ፕሮግራሞች ከገበያ ፍላጎት ጋር እንዲጣጣሙ ያግዛል። የትምህርትን ውጤት ወደ ተግባራዊ ሥራ በመቀየር ለግለሰብ፣ ለተቋምና ለሀገር ልማት ለማዋል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

የቴክኒክና ሙያው ዘርፍ ትልቁን ሚና ሊጫወቱ የሚገባቸው ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡ የሚፈለገውን ባለሙያ የብቃት ደረጃ ማውጣት እንዲሁም የብቃት ምዘና መመዘን ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህን ነገሮች ለማምጣት ደግሞ ኮሌጁ የስራ እድል ፈጠራና የትስስር ስራዎችን እየሰራ መሆኑን አቶ ሙሉጌታ ተናግረዋል፡፡

ኮሌጁ ሰራተኛና አሰሪን የማገናኘት ስራን ዋና ተልዕኮው አድርጎ እየሰራና ወደፊትም አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የሚያሳስቡት አስተባባሪው፤ ቴክኒክና ሙያ ያለ ኢንዱስትሪ ምንም ነው። ስለዚህ ኮሌጁ ከኢንዱስትሪዎች ጋር እየሰራ ይገኛል፡፡ ይህም በኮሌጅ እና በኢንዱስትሪዎች ስልጠና ይሰጣል። ኮሌጁ 70 በመቶውን የሚያሰለጥንና የሚመዝን ሲሆን ኢንዱስትሪው ደግሞ 30 በመቶውን እንደሚመዝኑ ተናግረዋል፡፡

# ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የመጽሐፍት ምረቃ፣ የኪነ ጥበብ አውደ ርእይ እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጽሐፍት

በመምሕር ገላውዴዎስ አለልኝ ተፅፈው የተሰናዱት ሦስት የህጻናት መፅሀፍት በዛሬው እለት ተመርቀው ለንባብ ይበቃሉ፡፡ “የጎበዝ ልጆች ቤተ መጻሕፍት”፣ “የምጡቅ አዕምሮ ልጆች ፈተና” እና “የልጆች የእውቀት ገበታ” የተሰኙት መፅሐፍት ልጆች አሳቢ እና አሠላሳይ እንዲሆኑ የሚያስችሉ በርካታ ጠቅላላ ዕውቀቶችን በውስጣቸው የያዙ መሆናቸው ተገልጿል፡፡ የመጽሐፎቹ የምርቃት ስነ ስርዓት ከ8:00 ሰዓት ጀምሮ ፒያሳ በሚገኘው በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ይከናወናል፡፡

በሌላ መረጃ የኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት አገልግሎት እና ንባብ ለህይወት ኢትዮጵያ ፕሮጀክት በጋር ያዘጋጁት የንባብ ሳምንት እና ዓመታዊ የመጻሕፍት አውደ ርዕይ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በሳለፍነው ሃሙስ የተጀመረውና በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል እየተካሄደ የሚገኘው ይህ መርሃ ግብር ነገ ይጠናቀቃል፡፡ አውደ ርዕዩ ላይ በርካታ ደራሲያን፣ የመጻሕፍት አታሚዎች፣ አሳታሚዎችና አከፋፋዮች እየተሳተፉበት ነው፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር
በመዲናዋ ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## የንባብ መርሃ ግብር

“በቆሎ እና ንባብ በክረምት” በሚል በዛሬው እለት የንባብ ልምድ ልውውጥና ውይይት ይደረጋል፡፡ መርሃ ግብሩ ከ8፡00 ጀምሮ ጎተራ ማሳለጫ በሚገኘው ልህቀት የንባብ ባህል ማጎልበቻ ማእከል ይደረጋል፡፡ በውይይቱ ላይ ደራሲ ሃይለመለኮት መዋዕል እና ደራሲ ጸሃይ መላኩን ጨምሮ ሌሎች አንጋፋና ወጣት ደራሲያን እንደሚገኙ ተገልጿል፡፡

## ሙዚቃ

“ቁንጅና” የተሰኘው አዲስ የሙዚቃ ቪዲዮ ተለቀቀ፡፡ ይህ የድምጻዊ ፍቃዱ ትዛዙ አዲስ ስራ ትናንት ምሽት በናሆም ሪከርድስ አማካኝነት ለአድማጭ ተመልካች ደርሷል፡፡ ግጥምና ዜማው በራሱ በፍቃዱ ትዛዙ የተሰራ ሲሆን አቤል ጳውሎስ በቅንብር ተሳትፎበታል።

## የኪነ ጥበብ አውደ ርእይ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አለ የሥነ ጥበብና ዲዛይን ትምህርት ቤት የተዘጋጀው አመታዊ የኪነ ጥበብ አውደ ርእይ በእይታ ላይ ይገኛል፡፡ አውደ ርእዩ ፈጠራን፣ ልምድና እውቀትን ለመለዋወጥ የሚያግዝ ሲሆን ረዘም ላለ ጊዜ ማለትም እስከ ፈረንጆች ጥቅምት 16 ድረስ እንደሚቆይ ተገልጿል፡፡

## የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። በብሄራዊ ቴአትር ቤት ቅዳሜ 8፡00 ሰዓት “12ቱ እንግዶች” እንዲሁም በ12:00 ሰዓት በቅርቡ ወደ መድረክ የመጣው “በር የሌለው ቤት” ይታያሉ፡፡ እሁድ በ8፡00 ሰዓት “ንጉስ አርማሕ” እንዲሁም በ12፡00 “እምዩ ብረቷ” ይታያሉ፡፡ ተመልካቾችም ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የ“ሁሉ በጄ” መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ ደግሞ “እሳት ወይ አበባ” ዘወትር ቅዳሜ በ11፡00 እንዲሁም “ባልቻ አባነፍሶ” ቴአትር እሁድ በ8:00 ሰዓት የሚታዩ ሲሆን ትኬቱን በኦንላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

ቦሌ ፍላሚንጎ በህፃናትና ወጣቶች የቴአትርና ሲኒማ ኮምፕሌክስ ቅዳሜ ጠዋት 4፡00 ሰዓት “አዮ ቦራ” የተሰኘው የአፋን ኦሮሞ ቴአትር ይታያል፡፡ እሁድ ጠዋት 4፡00 ሰዓት ደግሞ “የንባብ ከተማ” የተሰኘው አዲስ ቴአትር ለእይታ ይበቃል፡፡ እሁድ በ8፡00 ሰዓት በቅርቡ ወደ መድረክ የመጣው “ወህኒ አምባ” እንዲሁም 11፡30 ሰዓት “አትጥሪኝ” የተሰኙ ቴአትሮች ለተመልካች ይደርሳሉ።

እንዲሁም በሀገር ፍቅር ቴአትር ረቡእ በ11፡00 “አሉ” የተሰኘው አዲስ ቴአትር፣ ሐሙስ 11፡30 ሰዓት “ነገሩ አይቆምም፣ እሑድ በ8፡00 ሰዓት “ሰዴታ” (በአፋን ኦሮሞ) እና በ12፡00 ሰዓት “የመጨረሻው ፍርድ” ለቴአትር አፍቃሪያን ይቀርባሉ።

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው ክብ $6 \times 6 - 7 \times 5 = 1$ ይሆናል፡፡ ሁለተኛው ማለትም ከላይ በኩል በስተቀኝ $6 \times 3 - 4 \times 3 = 6$ ነው፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት የመጨረሻው $7 \times 3 - 9 \times 2 =$ **3** ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ የሚገቡ ትክክለኛ ቁጥር 3 ነው፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# መጽሐፍት በሲኒማ ስክሪን

**በአብርሃም ገብሬ**

አንድን መጽሐፍ ገጽ በገጽ ገልጦ ማንበብ ማለት ኩነቶችን በገዛ አእምሮ መዳኘትና በምናብ ሰፊ ሰማይ ሥር አዲስ ዓለምን መፍጠር ማለት ነው። ደራሲው በቃላት የገነባቸው ገጸ-ባህሪያት፣ የሳላቸው መልክዓ-ምድሮች እና ያሰፈራቸው ረቂቅ ስሜቶች በአንባቢው ሥነ-ልቦና ውስጥ የየራሳቸውን ሕያው ቅርጽ ይይዛሉ። ሆኖም ይህ በግለሰቡ ምናብ የተሳለ ዓለም ከወረቀት ገጾች ወጥቶ በትልቁ የሲኒማ ስክሪን ላይ በምስልና በድምፅ ሲገለጥ በተደራሲው ልብ ውስጥ ልዩ የስሜት መለወጥን ሊያመጣ ይችላል። ቀድሞ የተነበበ መጽሐፍ ወደ ፊልም ሲቀየር፣ በተመልካቹ ዘንድ "እኔ በምናቤ የሳልኩትና የዳይሬክተሩ የፊልም ሥራ ገጠሙ ወይ?" የሚል ጉጉት ይጭራል፡፡ በዚህም በምስል ጥበብ የመደመም ወይም ታሪኮች ሲቀነሱ የመቆጨት አዎንታዊና ተቃራኒ ስሜቶች የሚፋለሙበትን ድንቅ ኪነ ጥበባዊ ሙግት ይፈጥራል።




ፎቶ ከገፀ ድር

ወደ ፊልም ከተቀየሩ መጽሐፍት መካከል ጥቂቶቹ

ይህ ከመጽሐፍ ገጽ ወደ ሲኒማ አዳራሽ የመሻገር ጥበብ፣ በዓለም የኪነ-ጥበብ ታሪክ ውስጥ እንደ ማሪዮ ፑዞ "The Godfather" ወይም እንደ ቺኑዋ አቼቤ "Things Fall Apart" ያሉ ድንቅ ሥራዎችን በብዙዎች ዘንድ እንዲወደዱ ያደረገ ኪነ-ጥበባዊ መንገድ ነው፡፡ ታሪክ የቋንቋና የባህል ድንበር ተሻግሮ ዓለም አቀፋዊ ዝና እንዲቀዳጅ እና የንባብ ልምድ ባልዳበረበት ማህበረሰብ ውስጥ ጭምር የጥበብ ባለቤትነት ስሜትን እንዲፈጥር አድርጓል። ይህ የጥበብ መስተጋብር በሀገራችንም ታይቷል። የደራሲ አዳም ረታ "እቴ ሜቴ የሎሚ ሽታ" ረቂቅ የሕጽናዊነት (ከተለያዩ ብጥስጣሽ ታሪኮች አንድ ወጥ ውበት መፍጠር) ፍልስፍና ወደ ምስል ተቀይሮ በፊልም ተመልክተናል፡፡ ለመሆኑ አንድ መጽሐፍ ወደ ፊልም ሲቀየር በተመልካች ሥነ-ልቦና እና ምናብ ላይ የሚፈጥረው እውነተኛ ስሜት ምንድን ነው? የዛሬው የጥበብ ዓምዳችን ይህንን ይዳስሳል።

## መጻሕፍትን ወደ ሲኒማ የማሻገር ጥበብ በጨረፍታ

የአውሮፓ ሥነ-ጽሑፍ እና የሲኒማ ጥበብ ለዘመናት እጅግ የጠበቀ ትስስር አላቸው። በተለይም የአውሮፓን ክላሲክ እና ዘመናዊ ድርሰቶችን መነሻ በማድረግ የተሰሩት "The Godfather"፣ "The Lord of the Rings"፣ "The Shawshank Redemption" የመሰሉ የሲኒማ ሥራዎች መጀመሪያ መጻሕፍት ነበሩ፡፡ በሲኒማው ስክሪን ላይ ከታዩ በኋላ ደግሞ ይበልጥ ተወዳጅና ዓለም አቀፋዊ የሆነ ተደራሽነት አግኝተዋል። ይሄ የሆነው ግን በመጻሕፍት መልክ ታትመው የነበሩ ድርሰቶች ሁለት ሰዓት ገደማ ወደሚፈጅ የሲኒማ ጥበብ መቀየራቸውን ተከትሎ ነው፡፡

ታዋቂዋ የአዳፕቴሽን ተመራማሪ ሊንዳ ኸቺዮን በፈረንጆቹ 2013 ለንባብ ባበቃችው 'A Theory of Adaptation' በተሰኘው መጽሐፏ እንደምትገልጸው፣ ከመጽሐፍ ወደ ፊልም የመቀየር ሂደት (Adaptation) ማለት ቃላትን በቀጥታ ወደ ምስል መተርጎም ሳይሆን፣ የአንድን ጥበብ ቅርፅ ወደ ሌላ የጥበብ ቋንቋ መቀየር ማለት ነው። በመጽሐፍ ውስጥ ደራሲው የገጸ-ባህሪያትን ውስጣዊ ስሜት፣ ሃሳብና የሥነ-ልቦና ውዝግብ በሰፊ ትረካና በቃላት ፍሰት ይገልጸዋል። በሲኒማው ዓለም ግን ይህ የውስጥ ስሜት በተዋንያን የፊት ገጽታ፣ በዓይን እንቅስቃሴ፣ በብርሃንና ጥላ ውህደት እንዲሁም በምስል ቅንብር መተካት አለበት። ስለዚህ አዳፕቴሽን ስኬታማ የሚሆነው የፊልም ሰሪው ከመጽሐፉ ገጾች ጀርባ ያለውን ማዕከላዊ ጭብጥ ሳያጠፋ፣ በምስል ጥበብ ሕግጋት መሰረት አዲስ ሕይወት ዘርቶ ሲቀርጸው ብቻ ነው ትላለች፤ ተመራማሪዋ።

በአውሮፓ ሥነ-ጽሑፋዊ መነሻነት የተቀረጹት ከላይ የተጠቀሱት ተወዳጅ የፊልም ሥራዎች እንደሚያሳዩት፣ አዳፕቴሽን ታሪኮችን ከባህልና ከጊዜ ገደብ አሻግሮ ዓለም አቀፋዊ የማድረግ ታላቅ ኃይል አለው። መጻሕፍቱ በተጻፉበት ዘመንና ማህበረሰብ ውስጥ ብቻ ተወስነው ሊቀሩ ይችሉ የነበሩ እንደ ክህደት፣ ፍርሃት፣ ተስፋ እና ወዳጅነት ያሉ ሰብአዊ ባህሪያትን የፊልም ጥበብ ወደ ዓለም አቀፍ መድረክ ያወጣቸዋል። ሲኒማው የቋንቋና የባህል ድንበሮችን በመሻገር፣ የታሪኮቹን ፍልስፍናዊ ጥልቀት ለተለያዩ ሀገራት ተመልካቾች በእኩል ደረጃ ተደራሽ ያደርገዋል። በዚህም ምክንያት አዳፕቴሽን የአንድን ማህበረሰብ ሥነ-ጽሑፋዊ ሀብት ወደ መላው ዓለም የጋራ የጥበብ ቅርስነት የሚያሸጋግር ዋነኛ ኪነ ጥበባዊ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል።

ደራሲና የፊልም ሐያሲ ዋለልኝ አየለ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጠው አስተያየት፣ ንባብ አብዛኛውን ጊዜ የግለሰቡ ብቸኛ ተግባር ሲሆን፣ ፊልም ግን ብዙሃን በአንድ ላይ የሚታደሙበት የጋራ ጥበብ ነው። አንድን መጽሐፍ አንብበው የተለያዩ ሰዎች በፊልም መልክ ሲያዩት፣ ታሪኩን ከግል ምናብ ወደ ጋራ ማህበራዊ አጀንዳነት ያሸጋግሩታል። ይህ ሂደት በተመልካቹ ዘንድ "እኔ የወደድኩትን ታሪክ አሁን ሌላውም እያየው ነው" የሚል የእኔነት ስሜት ይፈጥራል፡፡

> **አንድ መጽሐፍ ከወረቀት ገጾች ተነስቶ ወደ ሲኒማ አዳራሽ የሚያደርገው ጉዞ ቀላል የሆነ ወይም ቃል በቃል የመተርጎም ሂደት ሳይሆን፣ የኪነ-ጥበብ ዳግም ውልደት ነው**

ከሲኒማ እይታ በኋላም በታሪኩ ዙሪያ ሰፊ ክርክሮችንና የሀሳብ ልውውጦችን በመፍጠር ማህበራዊ መነቃቃትን ይፈጥራል በማለት አጫውቶናል።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ የመጽሐፍ ገጾችን ጨምቆ በሁለት ሰዓት ፊልም ውስጥ ለማቅረብ ሲባል፣ ዳይሬክተሩ በርካታ ንዑስ ታሪኮችንና ተወዳጅ ገጸ-ባህሪያትን ለመቁረጥ ይገደዳል። ተመልካቹ በመጽሐፉ ውስጥ ልቡን የሰረቁት ወሳኝ ሁነቶች በፊልሙ ላይ ተለቅመው ሲቀነሱ ወይም ሲዘለሉ ሲመለከት፣ "ዋናው የታሪኩ ነፍስ ተሰረቀ" የሚል የቅሬታ ስሜት ሊያድርበት እንደሚችል ደራሲና ሐያሲ ዋለልኝ አጫውቶናል፡፡

አንባቢ በመጽሐፉ መሪ ገጸ-ባህሪ ላይ የራሱን ምናባዊ ምስል ይስላል፤ መልኩን፣ ድምፁን፣ አካሄዱን... በገዛ ምናቡ ይፈጥራል። ነገር ግን በፊልሙ ላይ ያንን ገጸ-ባህሪ የሚወክለው ተዋናይ ከተደራሲው የምናብ ምስል ጋር ፈጽሞ የማይጣጣም ሆኖ ሲገኝ በትልቅ ስክሪኑ እና በተመልካቹ አእምሮ መካከል ኪናዊ ውዝግብ ይፈጠራል። ይህ ሁኔታ ተመልካቹ በንባብ የገነባውን ነጻ የምናብ ምስል በዳይሬክተሩ እይታ እንደተነጠቀ ሆኖ ሊሰማውና የተመለከተው ፊልም ቅር ሊያሰኘው ይችላል ብሏል፡፡

## ሁለት መጻሕፍት በሲኒማ ስክሪን

በአፍሪካዊ ደራሲ ተጽፎ ዓለም አቀፍ ተወዳጅነትና ዕውቅና ካገኙ ድርሰቶች መካከል አንዱ የናይጄሪያዊው ደራሲ የቺኑዋ አቼቤ "Things Fall Apart" ድርሰት ነው፡፡ የመጽሐፉ ዋነኛ ጭብጥ የአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት እሳቤ ወደ ናይጄሪያ መምጣት፣ ለዘመናት ጸንቶ በኖረው ኢግቦ ማህበረሰብ ባህል፣ እሴትና የአኗኗር ዘይቤ ላይ ያስከተለውን አስደንጋጭ መናጋት ያስነብባል። አቼቤ፣ የቅኝ ገዢዎች እሳቤዎች እንዴት የማህበረሰቡን አንድነት እንዳፈረሱትና የጋራ ዕሴቶቻቸው እንደበታተኑት በመጽሐፉ ውስጥ ያሳያል። ይህ ጭብጥ አፍሪካውያን የገዛ ማንነታቸውን፣ ሥርዓታቸውንና ክብራቸውን በባዕዳን ወረራ ምክንያት እንዴት እንዳጡ የሚያሳይ አሳዛኝ ሁኔታ ይተርካል፡፡

አቼቤ ይህንን መጽሐፍ የጻፈበት ዋናው ፍልስፍናዊ ጭብጥ፣ ነጮች አፍሪካን ጨለማና ሥልጣኔ የራቃት አድርገው የሚስሉበትን የተዛባ የታሪክ አተራረክ ለመቀልበስ ነው። መጽሐፉ ነጮች ከመምጣታቸው በፊት የነበረው የአፍሪካ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ የዳኝነት ሥርዓት፣ የዳበረ ባህል፣ ጥልቅ ጥበብ እና ውስብስብ ማህበራዊ ውቅር የነበረው መሆኑን ያሳያል። ጭብጡ አፍሪካውያን የራሳቸውን ታሪክ በራሳቸው ብዕር መጻፍና የገዛ ታሪካቸው ባለቤት መሆን እንዳለባቸው የሚያሳይ መልእክትም ይዟል።

ዓለም አቀፍ ተወዳጅነትን ያተረፈው መጽሐፍ ወደ ቴሌቪዥን ተከታታይነት ድራማ ከተቀየረ በኋላ የፈጠረው አዎንታዊ መነቃቃት ብዙዎችን አስገርሟል፡፡ መጽሐፉ በ1987 ዓ.ም ወደ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ መለወጡ፣ በናይጄሪያ ማህበረሰብ ውስጥ እንደገና ነፍስ የዘራ ሆኗል። ኦጉንሌዬ ፎሉኬ የተባለ ተመራማሪ በ2003 ለንባብ ባበቃው "African Video Film Today" በተሰኘ ጥናታዊ ጽሑፉ ላይ እንዳሰፈረው፣ የደራሲ ቺኑዋ አቼቤ መጽሐፍ ወደ ቴሌቪዥን ድራማ መቀየሩ፣ የንባብ ባህል ባልዳበረበትና ማንበብ በማይችለው ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ ቁጭትና መነሳሳትን መፍጠሩን ጽፏል፡፡ ንባብ ከፍተኛ ትኩረትን፣ ጊዜን እና የቋንቋ እውቀትን (በተለይ መጽሐፉ በእንግሊዝኛ መጻፉን ተከትሎ) የሚጠይቅ በመሆኑ፣ ለብዙ ሕዝብ ተደራሽ አልነበረም። ነገር ግን ታሪኩ በምስልና በድምፅ ወደ ሕዝቡ ሲመጣ፣ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ፣ የንባብ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ኢኮኖሚ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ከማዕድ የተረፈ ጥሪት

**በይግለጡ ጓዴ**

ማለዳ 12 ሰዓት ላይ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 አንድ ግቢ ውስጥ ተገኝተናል፡፡ ወይዘሮ ተዋበች ባዩ ከማዕዳቸው ተርፎ የገቢ ምንጭ የሆናቸውን ታሪክ ከቃል በላይ የሆነ ልምዳቸውን ሊያካፍሉን ፈገግ እያሉ የዶሮ ጎጆውን በቀስታ ከፈቱ፡፡

በጎጇቸው ውስጥ ያሉት ዶሮዎች በአንድ ጊዜ ጩኸታቸውን አሰሙ። ይህ ጩኸት ግን ለወይዘሮ ተዋበች ጣፋጭ ዜማ ነው፡፡ የጠዋት ፀሐይ በዶሮዎቹ ጎጆ ጣሪያ ላይ ስትወድቅ በውስጡ ያሉት እንቁላሎች እንደ ወርቅ ያበራሉ።

ወይዘሮ ተዋበች እንቁላሎቹን አንድ በአንድ በጥንቃቄ በማንሳት በቅርጫት ውስጥ እያስቀመጡ ከጥቂት ዓመታት በፊት ባዶ የነበረው ጓሯቸው ዛሬ የቤተሰባቸው የገቢ ምንጭ እንደሆነ አጫወቱን። በሰዓታት ውስጥ ይህ ቅርጫት ወደ አካባቢው ገበያ ይሄዳል፤ ከዚያም የተገኘው ገቢ የልጆቻቸውን የትምህርት ወጪ፣ የቤት ፍጆታና ሌሎች የዕለት ፍላጎቶችን ይሸፍናል። "የዶሮ እርባታውን ስጀምር እንደነገሩ ነበር፤ ዛሬ ግን የቤተሰባችንን ገቢ እየደገፈ ነው" በማለት ወጋቸውን ቀጠሉ፡፡

ከራስ ማዕድ ተርፎ የገቢ ምንጭ እንደሆናቸውም ሲያጫውቱን በልበ ሙሉነት ነው፡፡ በሦስት የዶሮ ጫጩቶች የተጀመረው የሌማት ትሩፋት ዛሬ 50 ዶሮዎች ደርሶ በርካታ እንቁላሎችን እያስገኘ እንደ ስሙ ከማዕድ ተርፎ ለገበያ በቅቷል፡፡ በርግጥም የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ኮሚሽን የ2018 በጀት ዓመት ሪፖርት እንደሚያሳየው በርካቶች በዚህ ዘርፍ ተሰማርተው ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

ኮሚሽኑ ልክ እንደ ወይዘሮ ተዋበች ሁሉ በዛ ያሉ የመዲናዋ ነዋሪዎች ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ በበጀት ዓመቱ ብቻ 46 ሺህ ዶሮዎች፣ 1 ሺህ 324 የዶሮ ጎጆዎች እና 980 ኩንታል መኖ ለተጠቃሚዎች አሰራጭቷል። ይህም ብዙ ቤተሰቦች በትንሽ ቦታ ትልቅ ገቢ እንዲያገኙ መንገድ ከፍቷል።

ከአዲስ ከተማ ወደ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ስናመራ ደግሞ ሌላ የሕይወት ለውጥ አለ፡፡ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የሚኖሩት አርሶ አደር በለጠ ፍቅሬ የወተት ምርት ላይ ተሰማርተዋል። ከሁለት የወተት ላሞቻቸው የሚያገኙት ምርት ሁሌም ጠዋት ጠዋት በአካባቢው ለሚገኙ ቤተሰቦች በተመጣጣኝ ዋጋና በጥራት ይደርሳል።

በአዲስ አበባ ከተማ ልክ እንደ አርሶ አደር በለጠ ሁሉ በርካቶች በእንስሳት እርባታ ዘርፍ ተሰማርተው የኑሮን ፈተና በማሸነፍ ለሌሎች መትረፍ ስለመቻላቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ። የዝግጅት ክፍላችን በተለያዩ ጊዜያት ወደ እናንተ ያደረሳቸው ተጨባጭ ዘገባዎች የዚህ ምስክር ናቸው፡፡ የኮሚሽኑ የ2018 በጀት ዓመት ሪፖርትም ይህንኑ ያመለክታል። በሪፖርቱ መሠረት 156 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሊትር ወተት



ፎቶ፡-ከፋይል
በአዲስ አበባ እየተከናወኑ ካሉ የከተማ ግብርና ስራዎች በከፊል

በበጀት ዓመቱ ተመርቷል፤ 157 ሺህ 907 ቶን የእንስሳት ሥጋም ለገበያ ቀርቧል። እነዚህ ቁጥሮች የምግብ አቅርቦትን ብቻ ሳይሆን የከተማ ኢኮኖሚንም እያጠናከሩ መሆናቸውን ያሳያሉ።

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ነዋሪ አቶ በርጋ ሸኩሪ በግቢያቸው ባለችው ጥቂት ቦታ የጓሮ አትክልት ያመርታሉ። ጎመን፣ ሰላጣ፣ ቲማቲምና ቃሪያ በትንሽ መሬት ላይ እያመረቱ ለጎረቤቶቻቸው ይሸጣሉ። በዚህም ለቤተሰባቸው የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጡ ባሻገር ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንደሆናቸውም አጫውተውናል።

ለዚህ ደግሞ በ2018 በከተማው የተመዘገበው 123 ሺህ 811 ቶን የአትክልት ምርት፣ 52 ሺህ 117 ቶን የግቢና ጓሮ ምርት እንዲሁም 20 ሺህ 200 ቶን የመኸር ሰብል እንደ አቶ በርጋ ያሉ በሺዎች የሚቆጠሩ አምራቾች የጋራ ጥረት ውጤት መሆኑን ያሳያል።

ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ነዋሪ አቶ ህርኮ ሰይፉ የንብ ማነብን ምርጫቸው አድርገው በትጋት በመስራታቸው ከራስ ያለፈ ለውጥ ማስመዝገባቸውን ይናገራሉ። በትንሽ ቦታ የጀመሩት ሥራ ዛሬ የቤተሰባቸውን ወጪ የሚሸፍን ሆኗል።

በርግጥም ዛሬ በተለያዩ ክፍለ ከተሞች ጣፋጭ የአዲስ አበባ ማር እየተቆረጠ ነው። የኮሚሽኑ የ2018 በጀት ዓመት ሪፖርቱም ይህንኑ እውነት ይመሰክራል። ለአብነትም በበጀት ዓመቱ 709 ሺህ 209 ኪሎ ግራም ማር በአዲስ አበባ ተመርቷል። ይህ የንብ ማነብ በከተማ ውስጥም የሚቻልና በርግጥም የተቻለ መሆኑንም ያረጋግጣል፡፡

በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ደግሞ ወጣት አይናለም ሙሉጌታ በዓሣ እርባታ ተሰማርቷል። በትንሽ የውኃ ገንዳ የጀመረው ሥራ ዛሬ ለምግብ ቤቶችና ለግለሰቦች ዓሣ ወደ ማቅረብ ደረጃ ተሸጋግሯል። “ብዙ ሰዎች ‘በከተማ ውስጥ ዓሣ ማምረት አይቻልም’ ይሉኝ ነበር፤ ዛሬ ግን እነሱ ራሳቸው ደንበኞቼ ሆነዋል” ይላል ወጣት አይናለም በፈገግታ። በኮሚሽኑ የ2018 የስራ አፈፃፀም ሪፖርት እንደተመለከተው ወጣት አይናለምን በመሳሰሉ ብርቱዎች 23 ሺህ 752 ኪሎ ግራም የዓሣ ምርት ተገኝቷል፡፡

ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ያደረጉት የግብርና ሳይንስ ባለሙያው አጥናፉ አበራ (ዶ/ር) እንደሚሉት በአዲስ አበባ ከተማ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ የከተማ ግብርና ፍሬ እያፈራ እና ጉልህ ለውጥ እያስመዘገበ ነው፡፡ እነዚህ ለውጦች ደግሞ የሚያሳዩት አንድ የጋራ መልእክት አላቸው፤ ይሄውም የከተማ ግብርና ከጓሮ በላይ መሆኑን ነው፡፡

በትክክል ከሰራንበት የከተማ ግብርና የቤተሰብ ገቢን ያሳድጋል፣ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ያስችላል፣ የሥራ ዕድልን ይፈጥራል፤ ይህ ሁሉ ሲደመር የከተማውንም ኢኮኖሚ በአስተማማኝ መልኩ ለመገንባት ያስችላል ይላሉ የከተማ ግብርና ባለሙያው አጥናፉ አበራ(ዶ/ር)፡፡

የአርሶ አደርና ከተማ ልማት ኮሚሽን የ2018 በጀት ዓመት ሪፖርት እንደሚያሳየው በአዲስ አበባ፣ 615 ሺህ 16 ቶን ጠቅላላ የግብርና ምርት ተገኝቷል። በዚህ ውስጥ በርካቶች ራሳቸውን ለውጠው ለሌሎች ተርፈዋል፣ በኑሮ ውድነት መረጋጋት ላይ አሻራቸውን አስቀምጠተዋል፣ ጥራት ያላቸውን ምርቶች ለገበያው አቅርበዋል፣ ሰርቶ መለወጥ ይቻላል ለሚለው እውነትም ተምሳሌት ሆነዋል፤ በከተማዋ ሁለንተናዊ ዕድገትም ጉልህ አበርክቶ አድርገዋል፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 የሚኖሩት ወይዘሮ ወይንሸት ሰብስቤ ሁሌ ጠዋት ጠዋት በአግባቡ ከሚመግቧቸው ላሞች እያለቡ ያከማቹትን ወተት በአካባቢው ላሉ ሆቴሎች፣ ካፌዎችና ቤተሰቦችም በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባሉ፡፡ “ወተት ለእኛ ምግብ ብቻ አይደለም፤ ገቢያችንም ነው” ይላሉ።

እንደ ወይዘሮ ወይንሸት ሰብስቤ ያሉ ታታሪ ሰዎች በሚያደርጉት ጥረት እና የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ኮሚሽን ተከታታይ ድጋፍ በከተማው የወተት ምርትን በእጅጉ ማሳደግ ተችሏል፡፡

ይህም የከተማ ግብርና በቤተሰብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በከተማው የምግብ አቅርቦት ሥርዓት ውስጥ ያለውን ሚና በጉልህ ያሳያል።

በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 የሚገኘው የጋራ መኖሪያ መንደር ከሩቅ ሲታይ እንደ አትክልት መናፈሻ ይመስላል። በጠዋት የተረጨው ውኃ ከጎመኑ ቅጠል ጋር ተደምሮ አረንጓዴውን ቀለም የሚያበራ ጌጥ አስመስሎታል፡፡ የዚህ ጓሮ ባለቤት እና ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ያደረጉት አባ ኤልያስ የምሩ ናቸው።

ከዚህ በፊት በቤታቸው ዙሪያ የነበረው ክፍት ቦታ ዛሬ የቤተሰባቸው ማዕድ አድማቂ ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ የገቢ ምንጭም ሆኗል። በየሳምንቱ ጎመን፣ ሰላጣ፣ ቲማቲምና ቃሪያ ለአካባቢው ነዋሪዎች ያቀርባሉ። “ከገበያ የምንገዛው ቀንሷል፤ ከምናመርተው የምንሸጠውም ጨምሯል” ይላሉ፤ አባ ኤልያስ፡፡

ከለሚ ኩራ ወደ ጉለሌ ሲያቀኑ የአየሩ ሽታ ይቀየራል። በእንጦጦ ተራራ ደኖች እና በጉለሌ እጸዋት ማዕከል አረንጓዴ ልምላሜ የታጀበው ክፍለ ከተማው በርካቶች በንብ ማነብ ተሰማርተው ማር እየቆረጡበት ነው፡፡ ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት አቶ ጥጋቡ ሽታነህ አንዱ ናቸው። አቶ ጥጋቡ ሽታነህ፣ “ንብ ትዕግሥት ታስተምራለች፤ እያንዳንዱ ጠብታ ማር የብዙ ቀናት ጥረት ውጤት ነው” ይላሉ።

በከተማ ውስጥ ንብ ማነብ የማይቻል የሚመስለው ብዙ ሰው ቢኖርም እሳቸው እና መሰሎቻቸው ጣፋጭ ማር እያመረቱ እንደሆነም ነግረውናል። በስፍራው በነበርንበት ወቅትም ይህንኑ ማረጋገጥ ችለናል፡፡

በ2018 በጀት ዓመት በከተማ ግብርና ዘርፍ 1ሚሊዮን 283 ሺህ 537 የመዲናዋ ነዋሪዎች ተሳታፊ ሆነዋል። በርግጥ በከተማ ግብርና የተመዘገቡትን ውጤቶች ወደ እያንዳንዱ ጓሮ ገብቶ ላስተዋላቸው የልጆች ትምህርት ክፍያ፣ የአንድ ቤተሰብ የዕለት ምግብ እና የአንድ ማህበረሰብ የወደፊት ተስፋን የሚያመላክቱ በመሆናቸው የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና እያስመዘገባቸው ያሉ ስኬቶች ዋጋቸው ከቁጥር በላይ ከፍ ያለ ነው፡፡

# ልጆች፤ የክረምት ጊዜያችሁን ምን በማድረግ እያሳለፋችሁ ነው?

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች እንዴት ናችሁ? ወቅቱ ክረምት እንደመሆኑ ትምህርት ቤት ተዘግቶ እረፍት ላይ ናችሁ፡፡ በዚህ ወቅት ደግሞ የተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ በማድረግ፣ ከጓደኞቻችሁ ጋር በመጫወት፣ የልጆች ፊልም በማየት፣ ስዕል በመሳል፣ መፃህፍትን በማንበብ፣ ቤተ ዘመድ በመጠየቅ... ታሳልፉላችሁ ብለን እናስባለን፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገርናቸው ልጆች ያሉንን ደግሞ እንደሚከተለው ወደ እናንተ ለማድረስ ወደድን፤ መልካም ንባብ ይሁንላችሁ፡፡

ብሩክ እሸቱ እባላለሁ፡፡ 12 ዓመቴ ነው። የክረምት እረፍቴን የተለያዩ ነገሮችን በማከናወን አሳልፋለሁ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ መንፈሳዊ ትምህርት መማር ዋነኛው ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም ዛሬ እንዳገኘሽኝ ወደ መዝናኛ ቦታዎች በመሄድ እጫወታለሁ፡፡ ይህም አዳዲስ ጓደኞች ጋር አስተዋውቆኛል፡፡

ሌላው የማደርገው ሰዓቴን አመቻችቼ ከቤተሰቦቼ ጋር በመሆን አያቶቼን መጠየቅ ነው፡፡ በትምህርት ምክንያት ሳላያቸው የቆዩኋቸውን ዘመዶቼን አገኝበታለሁ፡፡ ተነፋፍቆ መገናኘት ደስ ይላል፡፡ ዘመዶቼን ከማየት ባለፈም አዳዲስ ቦታዎችን አያለሁ። እነዚህንና መሰል ነገሮች በማድረግ የእረፍት ጊዜዬን በአግባቡ እጠቀማለሁ፡፡

ሚኪያስ አዲሱ እባላለሁ፡፡ 13 ዓመቴ ነው፡፡ በክረምት የተለያዩ ነገሮችን አደርጋለሁ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ጠቃሚ ነው ብዬ የማስበውና የማስቀድመው ማንበብን ነው፡፡ ማንበብ ደስተኛ ያደርገኛል፡፡ በየቀኑ ሳላነብ አልውልም፡፡ በትምህርት ጊዜ ስማር የዋልኩትን ለፈተና እንደማነበው ሁሉ በአሁኑ ወቅትም በሚቀጥለው ዓመት ለምማራቸው የትምህርት አይነቶች የሚረዱኝን የተለያዩ አጋዥ መፃህፍትን እና አጫጭር ልቦለዶችን አነብባለሁ፡፡

በማንበቤም የማላውቃቸውን ነገሮች እንዳውቅ አስችሎኛል፡፡ እነዚህ ጥቅሞችን የሚያስገኘውን ንባብ ሁልጊዜም ቦታ እሰጠዋለሁ፡፡ ለዚህም እረፍቴን በአግባቡ እየተጠቀምኩ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ ከጎኔ ሆነው መፃህፍት በመግዛትና እንዳነብ በማበረታታት የሚያግዙኝ ቤተሰቦቼን አመሰግናለሁ፡፡ ሌሎች ልጆችም እረፍት ስለሆኑ ብቻ ሙሉ ትኩረታቸውን ጨዋታ ላይ ከሚያደርጉ ይልቅ ለነገ የሚያግዙ ነገሮች ላይ ቢያሳልፉ እላለሁ፡፡

ነብያት ፍስሃ እባላለሁ፡፡ 15 ዓመቴ ነው፡፡ ክረምት ሲመጣ ከትምህርት ቤት ከጓደኞቼ ብለይም እረፍት ስለምሆን ደስ ይለኛል፡፡ ጊዜ ስላለኝ የተለያዩ ተግባራትን አከናውናለሁ፡፡ ኳስ እጫወታለሁ። ወደፊት መሆን የምፈልገውን ሰዓሊ በመሆኑ ስዕል መሳልን ትኩረት ሰጥቼ እሰራበታለሁ፡፡ የተለያዩ ስዕል አሳሳሎችን በስልክ ከዩቱዩብ እያየሁ እስላለሁ፡፡


ፎቶ፡- ኤ አይ ቻት ጂፒቲ
ልጆች በክረምት ጊዜያቸው የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ

እንስሳትና ሰው ከስዕሎቼ መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህን ስዕሎች በክረምት ብቻ ሳይሆን በትምህርት ወቅትም እንዲሁ እስላለሁ፡፡ ይህንን ፍላጎቴን ለማሳካት ወላጆቼ ከጎኔ ሆነው አስፈላጊውን ግብዓት ያሟሉልኛል፡፡ ያበረታቱኛል፡፡ የዕረፍት ጊዜዬን በአግባቡ መጠቀሜም ጊዜዬን እዳላባክን ያደርገኛል። ልደርስ ያሰብኩበትን የስዕል ስራ እንዳሳካም ይረዳኛል ብዬ አስባለሁ፡፡

ፍቅሩ መለሰ እባላለሁ፡፡ 13 ዓመቴ ሲሆን ከስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እግር ኳስ መጫወት ያስደስተኛል። በሳምንት ሶስት ቀናትን ልምምድ አደርጋለሁ፡፡ በቤት ውስጥ ደግሞ ፑሽ አፕ እና ሲት አፕ አንዳንድ ጊዜ እሰራለሁ፡፡ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ በማድረጌ የአመጋገብ ስርዓቴን በማስተካከል ጤናማ ክብደት እንዲኖረኝ፣ በራሴ እንድተማመን እና ጡንቻዬ እንዲጠነክር አግዞኛል፡፡

የክረምት እረፍቴንም እነዚህን በማድረግና በመዝናኛ ቦታዎች በመዝናናት በአግባቡ እየተጠቀምኩት እገኛለሁ። በቀሪዎቹ የእረፍት ቀናቴም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሙዚየም እና ሳይንስ ሙዚየምንም ጨምሮ በከተማችን የሚገኙ የሚጎበኙ ቦታዎች የመመልከት እቅድ አለኝ፡፡

## አረንጓዴው እንጦጦ ፓርክ



ልጆች፣ አሁን ክረምት ስለሆነ አዲስ አበባን የበለጠ አረንጓዴ ለማድረግ ብዙ ችግኞች እየተተከሉ ነው።

ከእነዚህ ውብ አረንጓዴ ቦታዎች መካከል እንጦጦ ፓርክ አንዱ ነው። በፓርኩ ውስጥ ብዙ ዛፎች፣ ውብ አበቦች፣ ንጹህ የመራመጃ መንገዶች፣ የልጆች መጫወቻ ስፍራዎች እና የስፖርት ቦታዎች ይገኛሉ። እንዲሁም የተፈጥሮን ውበት በቅርብ ማየትና ንጹህ አየር መተንፈስ ይቻላል።

ልጆች፣ ዛፎችን መትከልና አረንጓዴ ቦታዎችን መጠበቅ ለአካባቢያችን ትልቅ ጥቅም አለው። ስለዚህ እንጦጦ ፓርክን ስትጎበኙ ንጽህናውን ጠብቁ፣ አበቦችንና ዛፎችን አትጉዱ፣ ተፈጥሮንም በፍቅር ተንከባከቡ። ይህ ከተማችን ሁልጊዜ አረንጓዴና ውብ እንድትሆን ይረዳል።

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ቀን ሙሉ በአየር ላይ የሚውል ሆኖም የትም የማይንቀሳቀስ ምንድን ነው?**

**መልስ፡-** *ሀ. ባንዲራ*

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ምግቧ የሚጣፍጥ ፤ ጦሯ የሚያብጥ ምድናት?**

*ሀ. ጎረቤት*
*ለ. ንብ*
*ሐ. ዘመድ*

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

# ቆሻሻን ከጠንቅነት ወደ ሀብትነት

**በደረጀ ታደሰ**

በፈጣን የከተማ ዕድገትና በሕዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት በአዳጊ አገራት ከተሞች የሚመነጨው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ከጊዜ ወደ ጊዜ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል። የተባበሩት መንግስታት የሰፈራ ፕሮግራም (UN-Habitat) "African Cities Waste Management Report" በሚል ርዕስ በጎርጎሮሳዊያን የዘመን ቀመር 2023 ላይ ይፋ ባደረገው ጥናታዊ ሪፖርት መሰረት፣ በአፍሪካ ከተሞች በቀን ከሚጣለው ቆሻሻ ውስጥ 70 በመቶ የሚሆነው በአግባቡ ሳይወገድ በየሜዳውና በየጎዳናው ላይ ይደፋል። ይህ ሁኔታ በዚሁ ከቀጠለ በአስርት ዓመታት ውስጥ የከተሞችን ለነዋሪዎች መኖሪያነት የመመቸትን መሰረታዊ ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ይከትተዋል፡፡

ከቆሻሻ ቆሻሻን መምረጥ ቢከብድም፤ የፕላስቲክ ቆሻሻዎች ለከተሞች ከፍተኛ አደጋ መሆናቸው አልቀረም። ለብዙ አገልግሎት (የዕቃ መያዣዎች፣ የፈሳሽ ኮዳዎች፣ የምርት ማሸጊያዎች ...) እንዲውሉ ተደርገው የሚመረቱ ፕላስቲኮች፣ በአብዛኛው አንድ ጊዜ ጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላ የሚጣሉ ናቸው፡፡ አንዴ አገልግለው መጣላቸው የቆሻሻ ክምችት እንዲጨምር ተፅዕኗቸው ይጎላል፡፡ ቆሻሻዎቹ በቀላሉ የማይበሰብሱና አካባቢን ለከፍተኛ ብክለት የሚዳርግ ኬሚካል መያዛቸው ደግሞ፣ በዛሬ ቸልተኛነት ነገ የህልውና አደጋ ይዞ እንዲመጣ ያደርጋሉ፡፡ ቱቦዎችን በመድፈን ለአካባቢ ብክለት፣ ለጎርፍ አደጋ ያጋልጣሉ፡፡ ስለዚህ ይህንን ችግር ለማቃለል ብሎም ለመቅረፍ፣ በጥናት ላይ የተመሰረቱ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፉ፣ አዳዲስ እና ውጤታማ አሠራሮችን መተግበር ያስፈልጋል፡፡ አዲስ አበባ ከተማ፣ የፕላስቲክ ምርቶችን (በተለይ በተለምዶ ፌስታል የሚባሉትን የፕላስቲክ ከረጢቶች) ጥቅም ላይ እንዳይውሉ በሕግ የከለከለችበትና ተግባራዊ የተደረገበት በዚህ ረገድ የሚጠቀስ በጎ ጅምር ነው፡፡

በዚህ ጽሑፍ በቀላሉ የማይበሰብሱ፣ የከተማ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎችን በመድፈን ለአካባቢ ብክለት ዋነኛ መንስኤ የሆኑ የፕላስቲክ ቆሻሻዎችን በመሰብሰብ፣ ወደ ዘላቂ የግንባታ ግብዓትነት የመቀየር አዲስ አሠራር እንቃኛለን፡፡ ይህ አሠራር፤ በተለይ በአፍሪካ ከተሞች እየተተገበረ ያለበትን ልምድ በምሳሌዎች አጣቅሰን እናቀርባለን፡፡ ብዙም ርቀን ሳንሄድ በጎረቤታችን ኬንያ ቆይታ እናደርጋለን። ነዋሪነቷን በናይሮቢ ያደረገችውን ሥራ ፈጠሪ እንስት፣ ንዛምቢ ማቴን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ አድናቆት ያስቸራትን በዕውቀትና በቴክኖሎጂ የታገዘ አዲስ ግኝቷንም በማሳያነት እናነሳለን፡፡

ንዛምቢ ማቴ፣ በኬንያ እና በመላው ዓለም ስሟ እየገነነ የመጣ የቁስ ሳይንስ መሐንዲስ (Materials Scientist) ናት። ለመታወቋ ምክንያቱ ደግሞ፣ አሳሳቢ ለሆነው የፕላስቲክ ቆሻሻ



ፎቶ፡- ከገጸ ድር

ከወዳደቀ ፕላስቲክ የግንባታ ግብዓት የሠራችው ኬንያዊቷ ሥራ ፈጣሪ ንዛምቢ ማቴ

> **በአፍሪካ አገራት ከተሞች ያሉ ወጣቶች በተደራጀ መልኩ የፕላስቲክ ቆሻሻዎችን እየሰበሰቡ ለከተማ ውበት የሚሆኑ ንጣፎችን በማምረት ራሳቸውን እየደገፉ አካባቢያቸውንም እያነጹ ይገኛሉ፤ ይህ ተግባር እጅግ የሚያበረታታ እና ድጋፍ ሊደረግለት የሚገባው ነው**

ክምችት የሰጠችው መፍትሄ ነው፡፡ ይህች ወጣት፣ በናይሮቢ ጎዳናዎች ላይ የሚጣለው የፕላስቲክ ቆሻሻ ሁሌም ያሳስባት ነበር፡፡ ማሰብ ብቻውን ውጤት ስለማይሆን፤ ተቀጥራ ትሠራበት የነበረውን አንድ የነዳጅ ኢንደስትሪ በመልቀቅ፣ በጎርጎሮሳዊያን የዘመን ቀመር 2017 ጀምሮ በቤቷ ጀርባ ባለው አነስተኛ የመሥሪያ ክፍል (ቤተ ሙከራ) ውስጥ ምርምር በማድረግ፣ ለዓመታት ቆየች፡፡ ባደረገችው ምርምር፣ የተጣሉ ፕላስቲኮችን በማቅለጥና ከአሸዋ ጋር በማቀናጀት እጅግ ጠንካራ የሆኑ የኮብልስቶን ንጣፎችን ማምረት የሚችል የቴክኖሎጂ ቀመር ማግኘት ቻለች።

በኬንያዊቷ ዕውን የሆነው ቴክኖሎጂ፤ የራሷን ኢንዱስትሪው እንድታቋቁም አስችሏታል፡፡ በዋናነት የግንባታ ግብዓቶች ላይ ያተኮረው በቴክኖሎጂ የታገዘው ኢንደስትሪ የአመራረት ሂደት ያልተወሳሰበ እና በአዳጊ አገራት በቀላሉ ሊተገበር የሚችል መሆኑ ልዩ ያደርገዋል። የአሠራር ሂደቱ በቀላል አገላለጽ ይህንን ይመስላል:- ወጣቶች መጀመሪያ የላስቲክ ቆሻሻዎችን ከያሉበት ይሰበስባሉ። የተሰበሰቡት በዓይነት በዓይነት ይለያሉ። በመቀጠል የተለዩት ፕላስቲኮች በትልልቅ ማቅለጫዎች ውስጥ በሙቀት ወደ ፈሳሽነት ይቀይሩታል። የቀለጠው ፕላስቲክ 30 ከመቶ መጠን ሆኖ፣ 70 ከመቶ መጠን ካለው አሸዋ ጋር ይደባለቃል (ይዋሃዳል)፡፡ በዚህ ጊዜ ቀልጦ በፈሳሽነት የተዘጋጀው ፕላስቲክ እንደ ሲሚንቶ የማጣበቅ (Binder) ሚናን ይጫወታል። አሸዋውን በሚገባ ያጣብቀዋል፡፡ በዚህ መልኩ የተዋሀደው ፕላስቲክና አሸዋ ሳይቀዘቅዝ በሃይድሮሊክ ማተሚያ ማሽኖች (Hydraulic Press) አማካኝነት ወደተለያዩ ማራኪ የንጣፍ ቅርጾች ይቀየራል፡፡ ከዚያም በውሃ እንዲቀዘቅዝ ይደረጋል። ኢንዱስትሪው በአሁኑ ወቅት ከሙከራ ደረጃ አልፎ በቀን ከ1 ሺህ 500 በላይ ንጣፎችን የሚያመርት ሲሆን፣ ከተመሰረተ ጀምሮ ከ100 ቶን በላይ የፕላስቲክ ቆሻሻን ወደ ግንባታ እቃ ቀይሯል።

የዚህ አሠራር የምህንድስና ብቃትና የጥንካሬ አቅም ከመደበኛው የሲሚንቶ ምርት በተሻለ ሁኔታ መረጋገጡ በተለያዩ ሳይንሳዊ ጥናቶች ተመስክሯል። የኬንያ የኢንዱስትሪ ምርምር እና ልማት ተቋም (KIRDI) ባደረገው በላብራቶሪ የተደገፈ የምርት ጥራት ምዘና (Compressive Strength Test) መሰረት፣ ከፕላስቲክና አሸዋ የሚመረቱት እነዚህ ንጣፎች በጥራት ለረጅም ጊዜ ማገልገል እንደሚችሉ አረጋግጧል። ይህ ጥንካሬ ከመደበኛው የኮንክሪት ንጣፍ በሁለት እጥፍ ገደማ የሚበልጥ ነው። ንጣፎቹ የተወሰነ የመለጠጥ ባህሪ ስላላቸው ከባድ መኪና ሲያልፍባቸው አይሰነጠቁም፤ ውሃ ሙሉ በሙሉ የማይመጡ (Waterproof) በመሆናቸው በቅዝቃዜና እርጥበት የመሸርሸር እድላቸው እጅግ አነስተኛ ነው። በተጨማሪም ከመደበኛው ንጣፍ በ15 በመቶ ቀለል ያሉ በመሆናቸው የትራንስፖርት ወጪን ይቀንሳሉ። ይህንንና መሰል ጠቀሜታን የሚሰጥ ኢንደስትሪ ዕውን ላደረገችው ኬንያዊት፣ በጎርጎሮሳዊያኑ የዘመን ቀመር በ2020 በተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም (UNEP) ዘንድ፣ "የምድራችን አሸናፊ ወይም ተጽዕኖ ፈጣሪ ወጣት (Young Champion of the Earth)" የተሰኘ ዓለም አቀፍ እውቅና እና ከፍተኛ ሽልማት አበርክቶላታል።

ከአካባቢ ጥበቃና ከኢኮኖሚ አንጻርም ቴክኖሎጂው የሚያስገኘው ውጤት እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ጥናታዊ መረጃዎች ያሳያሉ። በታዋቂው "Journal of Cleaner Production" ላይ በወጣ ጥናት መሰረት፣ እነዚህን ንጣፎች ለማምረት የሚጠይቀው የሃይል ፍጆታ ከመደበኛው የሲሚንቶ ጡብ በ40 በመቶ ያነሰ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ ቶን የፕላስቲክ ቆሻሻ ግንባታ ላይ በዋለ ቁጥር በአማካይ 1 ነጥብ 5 ቶን የካርቦን ጋዝ ወደ አየር እንዳይለቀቅ ያደርጋል። በሌላ በኩል፣ ዋናው ጥሬ እቃ ከቆሻሻ የሚሰበሰብ በመሆኑ የምርቱ መሸጫ ዋጋ ከመደበኛው የሲሚንቶ ንጣፍ ከ10 እስከ 30 ከመቶ ቅናሽ አለው። የዓለም አቀፉ የሰራተኞች ድርጅት (ILO) መረጃ እንደሚያመለክተው፣ ወደዚህ መሰል የክብ ኢኮኖሚ (Circular Economy) የሚደረግ ሽግግር በአዳጊ አገራት ውስጥ ከመደበኛው የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ይልቅ በ25 እጥፍ የበለጠ ከአረንጓዴ ልማት ጋር የተያያዘ የስራ እድል የመፍጠር አቅም አለው፡፡

ለናይሮቢ ከተማ እና ለኬንያ የፕላስቲክ ቆሻሻ ክምርን ከስጋትነት ወደ ጠቃሚ ምርት ግብዓትነት የሚቀየርበትን መላ በማስተዋወቅ፣ ወደ ታላቅ ስኬት እየገሰገሰች ያለችውን ወጣት ዓይነት ተግባር ውስጥ የገቡ አፍሪካዊያን ወጣቶች ቁጥር ቀላል አይደለም። በእኛው አዲስ አበባ እንኳን፣ እንደ ውሃ ቱቦ፣ የኤሌክትሪክ ኮንዲዩት እና መሰል ምርቶችን ከወዳደቁ ቆሻሻዎች የሚያመርቱ ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ በሌሎች የአፍሪካ አገራት ከተሞች ያሉ ወጣቶችም በተደራጀ መልኩ የፕላስቲክ ቆሻሻዎችን እየሰበሰቡ ለከተማ ውበት የሚሆኑ ንጣፎችን (Paving blocks) በማምረት ራሳቸውን እየደገፉ አካባቢያቸውንም እያነጹ ይገኛሉ። ይህ ተግባር እጅግ የሚያበረታታ እና ድጋፍ ሊደረግለት የሚገባው ነው፡፡ ምክንያቱም፤ "ቆሻሻን ወደ ሀብት" (Waste to Wealth) የመቀየር ሂደት በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንደሚባለው በርካታ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጥቅሞችን በአንድ ላይ ያስገኛል።

በአጠቃላይ እንደ ናይሮቢ (ኬንያ) እና ዳሬሰላም (ታንዛኒያ) ያሉ የምስራቅ አፍሪካ ከተሞች ተሞክሮ እንደሚያሳየው፣ ቆሻሻን ወደ ግንባታ ቁስ መቀየር የወጣቶችን ስራ አጥነት ከመቀነስ ባለፈ ለከተማ መሠረተ-ልማት ግንባታ ተመጣጣኝና ጠንካራ ግብዓት በቅናሽ ዋጋ ለማቅረብ ያስችላል። ይህንን ውጤታማ አሠራር በሌሎችም በማደግ ላይ ባሉ የከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በሰፊው ለማስፋፋት መንግስታት በፖሊሲ ደረጃ ድጋፍ ሊያደርጉላቸውና ወጥ የሆነ የጥራት መለኪያ መስፈርት ሊያወጡላቸው ይገባል።

ከዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# ልዩ ጥንቃቄ የሚሻው የጨቅላነት ወራት

**• የእናት ጡት ወተትን ዘግይቶ መጀመር ጨቅላ ህፃናትን ለደም መርጋት ችግር ሊያጋልጥ እንደሚችል ተመላክቷል**

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

ወላጆች በተለይም እናቶች ጨቅላ ህፃናት ሆስፒታል እያሉም ሆነ ከሆስፒታል ከወጡ በኋላ ልዩ ትኩረትና ክትትል ማድረግ እንዳለባቸው የጤና ባለሙያዎች ይመክራሉ። በጨቅላ ህፃናት የእጅ ወይም የእግር ማበጥ እና ቀለም መለወጥ፣ የሽንት መጠን መቀነስ፣ የአተነፋፈስ ችግር፣ ጡት አለመሳብ እና መሰል አደገኛ ምልክቶችን ሲመለከቱ በአፋጣኝ ወደ ህክምና ተቋማት መሄድ እንዳለባቸውም ይመክራሉ።

ጨቅላ ህፃናት ተጋላጭ ከሚሆኑባቸው ህመሞች አንዱና ዋነኛው ደግሞ የደም መርጋት (የፕላትሌት እጥረት) እንደሆነ በዳግማዊ ምኒልክ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በጨቅላ ህፃናት ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት ዮሐንስ ጎዲ ያስረዳሉ።

መምህሩ በጨቅላ ህፃናት ላይ የሚጋጥመውን የደም መርጋት በተመለከተ በ2017 ዓመተ ምህረት አንድ ጥናት አጥንተው ነበር። የጥናቱ ዋነኛ ትኩረትም ደም እንዲያደርጉ የሚያደርጉ የደም ህዋሳቶች (የፕላትሌት) እጥረት ያለባቸው ጨቅላ ህፃናት የመዳንና የመሞቻ ጊዜን መተንበይ ሲሆን፤ በጥናታቸውም ደም እንዲረጋ የሚያደርግ ህመም ያለባቸው ጨቅላ ህፃናት ችግሩ የሚመጣባቸው መቼ ነው? የችግሩ ተጠቂ የሆኑ ጨቅላ ህፃናት የመዳንና የመሞቻ ጊዜያቸውስ ምን ይመስላል? የሚለውን ተንብየዋል።

ጨቅላ ህፃናት ተጋላጭ ከሚሆኑባቸው በሽታዎች አንዱ የደም መርጋት ነው፤ የሚሉት መምህሩ፣ ይህም በብዙ ምክንያት ሊከሰት እንደሚችል ይናገራሉ። በተለይም ያለቀን መወለድ፣ የኪሎ ማነስ (ሲወለዱ ከ1 ነጥብ 5 ኪሎ ግራም በታች ዝቅተኛ ክብደት ያለባቸው ህፃናት) እንዲሁም በወሊድ ጊዜ ታፍነው የሚወለዱ ህፃናት ለደም መርጋት ሊጋለጡ እንደሚችሉ ጠቅሰዋል። ህፃናት እንደተወለዱ የእናት ጡት ወተትን ዘግይቶ መጀመርም ተጋላጭ ከሚያደርጉ ምክንያቶች የሚመደብ ሲሆን፣ ህፃናት እንደተወለዱ በአንድ ሰዓት ጊዜ ውስጥ የእናት ጡት ወተት ማግኘት እንዳለባቸውም መክረዋል።

ህፃኑ ገና ሲወለድ ያሉበት አንዳንድ የጤና ችግሮች እና በሽታዎች ሳቢያ በሰውነት ውስጥ የፈሳሽ መጠን ሲቀንስ ደም የመወፈርና የመርጋት ባህሪ ከማጣቱም ሌላ፣ ከባድ የባክቴሪያ ኢንፌክሽንም የሰውነትን የደም መርጋት ሂደት ሊያዛባው ይችላል። ከዚህም ሌላ በተፈጥሮ የሚከሰቱ የልብ ችግሮች፣ የደም ማነስ ወይም መብዛት በደምና በኦክስጅን ዝውውር ላይ የሚኖሩ እክሎችም ደም በሰውነት ውስጥ በተገቢው ፍጥነት እንዳይዘዋወር በማድረግ ለረጋ ደም መንስኤ ይሆናሉ።



ፎቶ፦ ከገፀ ድር
ወላጆች፣ ለጨቅላ ህፃናት ሆስፒታል እያሉም ሆነ ከሆስፒታል ከወጡ በኋላ ልዩ ክትትል ሊያደርጉላቸው እንደሚገባ የጤና ባለሙያዎች ይመክራሉ

በዳግማዊ ምኒልክ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በጨቅላ ህፃናት ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት ዮሐንስ ጎዲ እንደሚሉት፣ ህፃናት ከተወለዱ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች ጨቅላ ህፃናት ክፍል ውስጥ ይተኛሉ፤ በዚያም ለአንድ ወርና ከዚያ በላይ ለሚሆን ጊዜ የሚቆዩበት አጋጣሚ አለ።

ጨቅላ ህፃናት ክፍል እንዲገቡ የሚያደርጋቸው ምክንያት ደግሞ ያለቀን መወለድ፣ የኪሎ ማነስ ወይም ከኢንፌክሽን ጋር የተያያዙ በሽታዎች፣ የአተነፋፈስ ችግር ወይም ሳንባ ሳይጠነክር መወለድ የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ። ጨቅላ ህፃናት ክፍል ውስጥ የሚገቡ ህፃናት ብዙ ጊዜ የኢንፌክሽን መድኃኒቶችን እየወሰዱ ወይም የሙቀት መጠናቸው በጣም እየቀነሰ የአተነፋፈስ ችግር ካለባቸው፣ ከሚመጡ የደም ችግሮች መካከል የደም ማነስ፣ የደም መብዛት ወይም ደም እንዲረጋ የሚያደርግ የፕላትሌት መጠን ማነስ ከአጋላጭ ምክንያቶች መካከል ናቸው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ደም እንዲረጋ የሚያደርጉ የደም ህዋሳቶች (የፕላትሌት) እጥረት ያለባቸው ጨቅላ ህፃናት በጣም ብዙ ናቸው የሚሉት አጥኚው፣ የጥናቱ መነሻ ምክንያትም ይህው ነው። በዚህ ረገድ ከሚታዩት በጣም የተለመዱ የደም በሽታዎች ውስጥ ይህ በሽታ በዓለም አቀፍ ደረጃ አንደኛው እንደሆነም ተናግረዋል። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት ችግሩ በጣም ጎላ ያለ ነው፤ ያሉት አጥኚው፣ በጉዳዩ ዙሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረጃ እስከአሁን የተጠናው ጥናት አንድ ብቻ መሆኑንና ያም ቢሆን በበሽታው የተጠቁ ጨቅላ ህፃናት ቁጥር ምን ያህል ነው? የሚለውን ብቻ የሚያሳይ ነው ብለዋል። አሁን የተጠናው ጥናት ደግሞ ደም እንዲረጋ የሚያደርግ ህመም ያለባቸው ጨቅላ ህፃናት ችግሩ የሚመጣባቸው መቼ ነው? የሚለውን የሚተነብይ ነው።

ችግሩ የሚመጣው ህፃናት ክፍል ከገቡ በኋላ በስንተኛው ቀን ነው? በ5ኛው ቀን ነው? በ10ኛው ወይስ በ15ኛው ቀን ነው? የሚለውን ከተወለዱ እስከ 28ኛው ቀን ድረስ ጥናት ተደርጎበታል። ለሁለት ወራት በአዲስ አበባ በተመረጡ ስድስት የመንግስት ሆስፒታሎች በተደረገው ጥናት 350 ጨቅላ ህፃናት ተካተዋል። በጥናቱ ከተካተቱት ጨቅላ ህፃናት መካከልም 14 ነጥ 1 በመቶ የሚሆኑት የፕላትሌት እጥረት እንዳለባቸው ተመላክቷል። የጥናቱ ዋንኛ ትኩረት የችግሩ ተጠቂ የሆኑ ጨቅላ ህፃናት አማካይ የሞት ጊዜ ምን ያህል ነው? የሚለው እንደመሆኑ፣ እስከ 28 ቀን ክትትል እየተደረገባቸው አብዛኛዎቹ ከ23 ቀን በኋላ እንደሚሞቱ ተናግረዋል።

መምህር ዮሐንስ በጥናታቸው ከእናት የሚመጡ ተጽዕኖዎች ለሞት ከሚያደርሱ ዋና ዋና ምክንያቶች ተጠቃሽ እንደሆኑ ጠቁመው፣ እናት በእርግዝና ወቅት የነበሩባት አንዳንድ የጤና ሁኔታዎች በህፃኑ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ባይ ናቸው። እናት ቁጥጥር ያልተደረገበት የስኳር በሽታ ካለባት፣ በእርግዝና ወቅት የሚከሰት ከፍተኛ የደም ግፊትና የጄኔቲክ (የተፈጥሮ) ምክንያቶች ህፃኑ ለደም መርጋት ሊያጋልጡ እንደሚችሉ አንስተዋል።

አቶ ዮሐንስ የቀደሙ የዓለም አቀፍና የኢትዮጵያ ጥናቶችን በመጥቀስ፣ በኢትዮጵያ በኒዮኔታል ጽኑ ሕክምና (NICU) የሚተኙ ጨቅላ ሕፃናት መካከል የፕላትሌት እጥረት 49 ነጥብ 3 በመቶ እስከ 63 (ወይም 66) በመቶ ሊደርስ እንደሚችል ገልጸዋል። የችግሩ መንስኤ በርካታ እንደመሆኑ መጠን ችግሩን ለመከላከል በተለይ ከእናት የሚመጡ ተጽዕኖዎችን ማስቀረት ወሳኝ ነው። ለዚህ ደግሞ ማዋለጃ ክፍል ያሉ ባለሙያዎች ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው ብለው፣ ለነፍሰ ጡር እናቶች አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ ቀዳሚው እንደሆነም አጽንኦት ሰጥተዋል። ለምሳሌ የተለያየ የጤና እክል ያለባትን እናት ጤናዋ ያለበትን ሁኔታ ክትትል በማድረግና አስፈላጊውን መድኃኒት በመስጠት ቀደም ብላ በኦፕራሲዮን እንድትወልድ ማድረግ ተገቢ ነው።

እንደዚሁም ያለቀን መወለድ፣ በወሊድ ጊዜ የሚያጋጥም መታፈን የመሳሰሉ ተጽዕኖዎችን ለመከላከልና የአንጀት ቁስለት ያለባቸው ህፃናትን ደግሞ ህፃናት ክፍል ያሉ ባለሙያዎች ከድህረ ወሊድ ጀምሮ በትኩረት ከመስራት ባለፈ፣ በሆስፒታሎች ደረጃ ችግሮቹን ፈጥኖ የሚለይ ባለሙያ ማብቃትን እንደ መፍትሄ አስቀምጥዋል። በተለይ እናቶች ወደ ቤታቸው ከሄዱ በኋላ ችግሩ እንዳይከሰት ለጤና ጠንቅ የሆኑ አደገኛ ምልክቶችን መለየትና ማወቅ ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ፦ የአተነፋፈስ ችግር፣ የሽንት መጠን መቀነስ፣ ጡት አለመሳብ እና መሰል ችግሮችን ሲመለከቱ በፍጥነት ወደ ጤና ተቋም መሄድና ማሳየት ይኖርባቸዋል።

የጤና ባለሙያዎችም እናቶች በድህረ ወሊድ ወቅት ከሚያጋጥማቸው የጤና እክል ራሳቸውን እና ሕፃኑን መጠበቅ እንዲችሉ በእርግዝና ወቅት የቅድመ ወሊድ ክትትል እንዲያደርጉ ግንዛቤ በመስጠት እና ስለ ህመሙ ምልክቶች መረጃ በመስጠት ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው ብለዋል። ከጤና ባለሙያዎች በተጨማሪ የጤና ተቋማትም በደም ባንክ አገልግሎት አስፈላጊውን ደም ማሟላት፣ መንግሥትም እንደመንግሥት የእናቶችንና የህፃናትን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ የጤና ፖሊሲዎች በሚገባ ማጠናከር፣ የህፃናት አገልግሎትን በጀመረው ልክ ማስፋፋት ብሎም የህክምና መሳሪያዎችና መድኃኒቶችን የበለጠ ማሟላት እንደሚጠበቅበትም መክረዋል።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ልማቱ ለብዝሃ ሕይወት መጠበቅ ያለው አበርክቶ እስከምን?

• ቀበና ላይ የተሰራው የወንዝ ዳርቻ ልማት አካባቢውን ለሰው ልጆች፣ ለእንስሳትና ለእጽዋት ምቹ እንዳደረገው ተጠቁሟል

**በለይላ መሃመድ**

የቀበና ወንዝ የድሮ ተፈጥሯዊ ገጽታ ማራኪ በሚባል የሚገለጽ እንደነበር አካባቢውን በደንብ የሚያውቁ ሰዎች ምስክር ናቸው፡፡ አቶ ገረመው ተፈራ ውልደታቸውም እድገታቸውም በቀድሞው ደጃአዝማች ይልማ መኮንን አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የነበረውና ከ1983 ዓ.ም በኋላ ቀበና መጀመሪያ፣ አንደኛና ቅድመ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የተባለው ት/ቤት አጠገብ ነው፡፡ ከቀበና ወንዝ ጋር የነበራቸውን ቁርኝትና ትዝታ ሲናገሩ በተነቃቃና በጋለ ስሜት ነበር፡፡

"ከልጅነታችን ጀምሮ የቀበና ወንዝ የጊዜ ማሳለፊያችን መዝናኛችን ነበር። ከትምህርት ቤት ስንወጣ ቀበና ወንዝ ሳንዋኝ ወደ ቤታችን አንገባም። ከጓደኞቻችን ጋር በመሆን ጥቃቅን አሳዎችን በማጥመድ እንበላ ነበር። በወንዙ ዙሪያ ሲጠጣ የሚጣፍጥ ትናንሽ ምንጮች ነበሩ፡፡ ቤተሰቦቻችን በወቅቱ መጠጥን ጨምሮ አጠቃላይ ለቤት ውስጥ መገልገያ የሚሆን ውሃ ይቀዱ የነበረው ከዚሁ ከወንዙ ዳርቻ ከሚመነጩ ምንጮች ነበር፡፡" ሲሉ ወንዙ የነበረውን የቀደመ ገጽታ እና ይሰጥ የነበረውን ዘርፈ ብዙ አገልግሎት አስታውሰዋል፡፡

"ከባለፉት ዓመታት ወዲህ ከተማው እየሰፋ ሲሄድ ወንዙ እየቆሸሸ መጣ፡፡ ወዝና ለዛውን አጣ፡፡ እንኳን ለመጠጣትና ለመዋኘት ይቅርና በአካባቢው ለማለፍም ሽታው አይቻልም ነበር፤ በዚህም ማንም አይቀርበውም ነበር፡፡ ድሮ ከነበረበት ይዞታው ጋር እያነጻጸርን ለልጆቻችን ታሪክ ከመንገር ያለፈ ስራ መስራት ባለመቻላችን እያየን እናዝን ነበር፡፡

ዛሬ ደግሞ ታሪክ ተቀይሮ ወንዙ ለማ፡፡ አሁን ላይ ከነበረበት ቆሻሻ ገጽታ ተላቅቆ ለልጅ ልጆቻችን መዝናኛነት በሚውል ደረጃ መልማቱ ከፍተኛ ደስታ ፈጥሮብኛል። እድሜ ሰጥቶኝ ሁሉንም አይነት ለውጦች በማየቴ ፈጣሪዬን ማመስገን እፈልጋሉ፡፡ ጠዋትም ማታም ከልጆቼና ከልጅ ልጆቼ ጋር ወጣ እያልኩ አየር እቀበላለሁ" በማለት የልማቱን ትሩፋት አጫውተውናል፡፡

ግርማ ተስፋዬ የተባሉት የአካባቢው ነዋሪም የአቶ ገረመውን ሀሳብ ይጋራሉ። እሳቸውም በዚሁ ቀበና ወንዝ አካባቢ ተወለደው ማደጋቸውን በመጠቆም፣ ወላጅ እናታቸው በ1963 ዓ.ም በአካባቢው መኖር መጀመራቸውንና አሁንም በዚሁ በእናታቸው መኖሪያ ቤት ውስጥ ወልደው ከብደው እየኖሩ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

"የቀበና ወንዝ ዋና የምንማርበት፣ እናቶች ልብስ የሚያጥቡበትና ወጣቶች የሚገናኙበት የፍቅር ቦታ ነበር" ሲሉ ያለፉበትን ጊዜ የገለጹት በትዝታ ፈረስ እየጋለቡ ነበር። በዛን ወቅት እንደአሁኑ የተለያዩ የመዝናኛ ስፍራዎች ስላልነበሩ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉትና የሚዝናኑት በቀበና ወንዝ ነበር፡፡ የወንዙ ዳርቻ በዛፎች፣




ፎቶ፡- ከገፀ ድር
ተፈጥሯዊ መልኩን እየያዘ የመጣው የቀበና ወንዝ ዳርቻ ከፊል ገፅታ

በቁጥቋጦዎችና በወንዝ ዳር እፅዋት የተከበበ ስለነበር የዛፎቹ ጥላ፣ የወንዙ እና የአእዋፋት ድምጽ አጠቃላይ ተፈጥሯዊ ገጽታው ሰላም ይሰጥ ነበር። በተለይም የወንዙ ውሃ እጅግ ንጹሕና ቀዝቃዛ ስለነበር የሰፈሩ ነዋሪዎች ለአጠቃላይ የቤት ውስጥ አገልግሎት ይጠቀሙበት እንደነበር ጠቁመዋል።

"በከፍተኛ ደረጃ ተበክሎ የነበረውን ወንዝ ወደ የቀደመ ገጽታው እንዲመለስ የታደገውን መንግስት በዚህ አጋጣሚ ሳላመሰግን አላልፍም፡፡ በእኔ እድሜ ይሄንን ማየቴ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ ምክንቱም ያ እንዋኝበት፣ እንዝናናበት እና ልብስ እናጥብበት የነበረው ወንዝ ቆሽሾ ስናይ ይከፋን ነበር፤ እናዝን ነበር፡፡" ይላሉ አቶ ግርማ፡፡

የቀበናን ወንዝ ወደቀደመ ተፈጥሯዊ ይዘቱ በመመለስ የብዝሀ ህይወት እንዲያገግም ስለተሰራው ልማት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የደን ሀብት አጠባበቅ ቡድን መሪ እንዲሁም "የእንጦጦ - ቀበና የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ልማት" እና የቀበና ግድብ ፕሮጀክት አስተባባሪ ኢንጂኒዬር አማኑኤል ሽብሩን አነጋግረናቸዋል። እንደ ኢንጂኒዬር አማኑኤል ገለጻ፤ በአዲስ አበባ ከተማ እምብርት ውስጥ አቋርጠው ከሚያልፉት ወንዞች መካከል አንዱ የሆነው የቀበና ወንዝ በቆሻሻ የተበከለ ጥቁር ውሃ ነበር፡፡ ከወንዙ ይወጣ የነበረው መጥፎ ጠረን ለማለፍ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ይህ ችግር የተፈጠረው ወንዙና የወንዝ ዳርቻው ከመልማቱ በፊት በአካባቢውና በዙሪያው ይኖሩ የነበሩ ነዋሪዎች እና የተለያዩ ተቋማት መጸዳጃ ቤታቸውን ጨምሮ አጠቃላይ ፍሳሻቸውን ወደ ወንዙ ይለቁ ስለነበር ነው፡፡

የፕሮጀክቱ አስተባባሪ አያይዘው እንደገለጹት፤ ቀበናን ጨምሮ ሌሎች በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ወንዞች ለዘመናት ትኩረት በመነፈጋቸውና በቸልታ በመያዛቸው ምክንያት ከልማት ማዕከልነት ይልቅ የቆሻሻና የፍሳሽ መጣያ ቦታ ሆነው ቆይተዋል። ከተማና ወንዝ በታሪክ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ ህይወትና በተፈጥሮ ውስጥ የተሳሰሩ ናቸው። ብዙ የዓለም ከተሞች በወንዝ ዳርቻ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ውሃ ለህይወት መሰረት ነው፤ ወንዝ ደግሞ የውሃ ምንጭ ብቻ ሳይሆን የሰዎች፣ የንግድ፣ የባህልና የከተማ እድገት መስመር ነው። ይሁን እንጂ ከተማ እየተስፋፋና የነዋሪው ህዝብ እየበዛ ሲሄድ የሰው ልጅ በወንዙ ላይ ተጽዕኖ ያደርግበታል። በዚህ የተነሳም ከተማና ወንዝ ያላቸው ቁርኝት እየተፈተነ ይመጣል። ከዚህ በተጨማሪ የወንዞቹን የተፈጥሮ ገጽታ ከማበላሸት ባለፈ በወንዙ ዙሪያ የሚኖሩና የሚንቀሳቀሱ ነዋሪዎችን ጤናና ደህንነት የሚፈታተን ሁኔታ ፈጥሯል።

ብዙ ጊዜ የወንዝ ዳርቻ ልማት ሲባል መንገድ፣ መብራት፣ የእግረኛ መንገድና አረንጓዴ ቦታ መገንባት ብቻ ይመስላል። ይሁንና ዘላቂ የወንዝ ልማት ከዚህ የበለጠ ሰፊ ነው። የወንዙ ውሃ ጥራት መጠበቅ፣ የፍሳሽ ውሃ በቀጥታ ወደ ወንዙ እንዳይገባ ማድረግ፣ የወንዙን የተፈጥሮ ፍሰት መጠበቅ፣ የጎርፍ አደጋን መቀነስ፣ የወንዙን ዳርቻ በአገር በቀል ዕፅዋት ማልማትና ለህዝብ ክፍት የሆኑ የመዝናኛ ቦታዎችን መፍጠር የዘላቂ የወንዝ ልማት አካላት ናቸው። ስለዚህ "የእንጦጦ - ቀበና የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ልማት" እና የቀበና ግድብ አንድ ፕሮጀክት ብቻም ሳይሆን የከተማ አካባቢ ጥበቃ፣ የውሃ ሀብት አስተዳደር፣ የህዝብ ጤናና የከተማ ኑሮ ጥራትን የሚያገናኝ ሰፊ የልማት እቅድ ነው፤ እንደ ኢንጂኒዬር አማኑኤል ገለጻ።

በተፈጥሮ በብዝሀ ህይወት የበለጸገ፤ ነገር ግን በሚፈለገው ደረጃ ጥቅም ላይ ያልዋለውን የቀበና ወንዝ ከነበረበት ችግር እንዴት እንደሚላቀቅና ማልማት እደሚቻል

> ከእንጦጦ እስከ ቀበና ያለው የወንዝና የወንዝ ዳርቻ ልማት እና የቀበና ግድብ አንድ ፕሮጀክት ብቻም ሳይሆን የከተማ አካባቢ ጥበቃ፣ የውሃ ሀብት አስተዳደር፣ የህዝብ ጤናና የከተማ ኑሮ ጥራትን የሚያገናኝ ሰፊ የልማት ሥራ ነው

በመጀመሪያ የተወሰደውን እርምጃ ኢንጂኒዬር አማኑኤል ሲገልጹ፤ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመሆን የማካለል ስራ ነበር የተሰራው። በወንዙ ዳርቻ የነበሩ መኖሪያ ቤቶች እንዲነሱ ተደርጓል፡፡ ፍሳሻቸውን ወደ ወንዙ ያስወግዱ የነበሩ የጋራ መኖሪያ ቤቶችና ተቋማት ማስወገጃቸውን የማስቆም ስራ ተሰርቷል፡፡ በኮንሶ ባህላዊ የእርከን ስራ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ተሰርተዋል። ከታች ከወንዙ ጀምሮ ወንዙና የወንዝ ዳርቻው ላይ ጋቢዎን (ድንጋዩን በጥልፍልፍ ሽቦ የማሰር) እና እርከን በመሰራቱ የጎርፍ አደጋ እንዳይከሰት አድርጓል፡፡ ይህም የተለያዩ እጽዋትን ለመትከል ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡" ብለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የተለያዩ ሀገር በቀል እጽዋት እየተተከሉ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ስራዎች በመሰራታቸው የመጣውን ለውጥ አስተባባሪው፤ "ብዝሀ ህይወት ማለት ውሃ፣ አፈር፣ እጽዋት፣ አእዋፋት፣ የሰው ልጅ እና የመሳሰሉትን የሚይዝ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር እነዚህ ብዝሀ ህይወት እየበዙ መጥተዋል፡፡ አካባቢው አረንጓዴና ለም በመሆኑ ምንጮች ተፈጥረዋል፡፡ የጠፉ አእዋፋት መምጣት ጀምረዋል፡፡ ሰዎችም ለመዝናኛነት እየመጡ ነው፡፡ አሁን ላይ ቀበና ላይ የተሰራው የወንዝ ዳርቻ ልማት አካባቢውን ለሰው ልጆች፣ ለእንስሳትና ለእጽዋት ምቹ እንዲሆን አድርጎታል። ለህጻናት መዝናኛነት፤ ለትልልቅ ሰዎች ማረፊያነትም እየዋለ ይገኛል"፡፡ ሲሉ ገልጸውታል፡፡

በወንዙና በወንዝ ዳርቻው የመጣውን ልማት የመጠበቅና እንክብካቤ የማድረግ ስራ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እና የአካባቢው ነዋሪ ብቻ ሳይሆን የከተማው ነዋሪ ሁሉ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ይህንን ልማት መጠበቅና ማስቀጠል ከግንባታው ያልተናነሰ ትልቅ ስራ ነው። ወንዙ እንደገና በቆሻሻ እንዳይሞላ፣ የፍሳሽ ውሃ እንዳይገባ፣ የወንዙ ዳርቻ በዘፈቀደ እንዳይያዝና የተተከሉ ዛፎች እንዳይወድሙ ቀጣይነት ያለው ክትትልና የህዝብ ተሳትፎ ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ነዋሪዎች ተጠቃሚዎች ብቻ ሳይሆኑ የወንዙ ጠባቂዎችም መሆን አለባቸው። የቀበና ወንዝ የመላው ከተማ የጋራ ሀብት ነው፤ ሁሉም ሊጠብቀውና ሊንከባከበው እንደሚገባ አስተባባሪው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

## ፅዳትን ... ከገጽ 6 የዞረ

በሁለቱም መንገድ (በግንዛቤ ፈጠራና ያጠፉትን ተጠያቂ በማድረግ) በመሰራቱ ለውጦች እየታዩ መጥተዋል፡፡ አሁን ማህበረሰቡ በአካባቢው በዘፈቀደ ቆሻሻ ሲጣል "አንሱ! ትክክል አይደለም፤ ቆሻሻ መጣያ ላይ በአግባቡ ጣሉ" ማለት ጀምሯል። ከዚህ ባለፈም ለህግ አካላት በማሳወቅ አካባቢን ያቆሸሹ እንዲቀጡ እያደረገም ይገኛል፡፡ ከ752 ሺህ በላይ የህብረተሰብ ክፍል በድግግሞሽ በየሳምንቱ ቅዳሜ ከቤቱ እየወጣ በየብሎኩ አካባቢውን እያፀዳ ይገኛል። ይህም በ2018 በጀት ዓመት 750 ሺህ የማህበረሰብ ክፍል ለማሳተፍ ከተያዘው ከፍ ያለ ነው። ህብረተሰቡ የፅዳቱ ባለቤት ተደርጓል። በዚህም በርካታ አካባቢዎች ንጽህና ውብ ሆነዋል፤ የሚታይ ለውጥ መጥቷል ብለዋል፤ አቶ ሙላት፡፡

### ቀጣይ ምን ለመስራት ታቅዷል?

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የ2018 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እና የ2019 በጀት ዓመት ዋና ዋና አቅጣጫዎችን ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ባቀረቡበት ወቅት፣ የከተማዋን ውበትና ፅዳት ማስጠበቅ ትኩረት ከተሰጣቸው ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል አንዱ መሆኑን ገልጸዋል።

በቀጣይም ቆሻሻን የሚጠየፍ ማህበረሰብ እንዲኖር፣ ደረቅ ቆሻሻ ሀብት መሆኑን በመረዳት ባለቤት ሆኖ እንዲሰራ ህብረተሰቡን የማስተማር ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አቶ ሙላት ተናግረዋል፡፡ ኤጀንሲው በ2019 በጀት ዓመት 800 ሺህ የሚጠጋ የህብረተሰብ ክፍል በፅዳት ስራው ለማሳተፍ እቅድ ይዞ እየሰራ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት በክረምት የንቅናቄ ስራ በ90 ቀናት እቅድ የወንዝ ዳርቻዎች፣ የአስፋልት ዳር፣ የኮብልስቶንና ጥርጊያ መንገድ በዮች፣ ማንኖሎች አካባቢ ንጹህ እንዲሆኑ ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በክረምት ወቅት የጎርፍ አደጋን በመከላከል በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ፤ "ደረቅ ቆሻሻ የሀብት ምንጭ እንጂ ለጎርፍ አደጋ ስጋት ሊሆን አይገባም!" በሚል መሪ ሀሳብ በየክፍለ ከተሞች እየተካሄደ ይገኛል፡፡

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አያይዘውም አዲስ አበባ በፍጥነት እያደገች እና እየተለወጠች ትገኛለች፡፡ የፅዳት ባህሉ እየተሻሻለና እያደገ ቢመጣም፤ የከተማዋን ፈጣን ዕድገት የማይመጥንና ኋላ ቀር የሆነ የቆሻሻ አወጋገድ ልማድ አሁንም አለ። ከተሽከርካሪ በመስኮት ወደ ውጪ ቆሻሻ የሚጥሉ፣ በየአካባቢው የቆሻሻ መጣያዎች ቢኖሩም በአግባቡ ቆሻሻ የማያስወግዱ ዜጎች እንዳሉ ያነሳሉ፡፡ በተለይ በቆሎ በልተው ቆረቆንዳውን፣ የሸንኮራ አገዳ ልጣጭ በዘፈቀደ የሚጥሉ፣ ከመኪና ዲኮር ቤቶችም ለምሳሌ ከፒያሳ ወደ ዮሐንስ በሚወስደው መንገድ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ቆሻሻን በግዴለሽነት የመጣል ሁኔታ ይታያል፡፡ እርምጃ በመውሰድ ለማስተካከል እየተሞከረ ቢሆንም አሁንም ችግሩ ይታያል። የምንኖርባትን ከተማ ንፁህና ውብ ማድረግ የሁሉም ኃላፊነት እንደመሆኑ እያንዳንዱ ዜጋ ያመነጨነውን ቆሻሻ በአግባቡ በመያዝና በትክክለኛው የቆሻሻ መጣያ ቦታ በማስወገድ ኃላፊነቱን መወጣት እንዳለበት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

## ለዘመናት ... ከገጽ 7 የዞረ

ሽግግሮች የኢትዮጵያ መሠረታዊ ችግሮች በመንግሥት ለውጥ ብቻ፣ በወታደራዊ ድል ወይም በግዴታ የመንግሥት ኃይል ሊፈቱ እንደማይችሉ አሳይተዋል።

ይህንን እውነታ በመገንዘብ፣ የብልጽግና ፓርቲ "መደመር" (Medemer) የተሰኘ አዲስ የፖለቲካ ፍልስፍና አቀረበ። ይህም ከግጭት ይልቅ ትብብርን፣ ከማግለል ይልቅ ማካተትን፣ ከመከፋፈል ይልቅ ውይይትን የሚያስቀድም አስተሳሰብ ነው። በመሠረቱ መደመር የኢትዮጵያ ብዝሃነት እንደ ድክመት ወይም ለዘላቂ ግጭት ምክንያት ሳይታይ፣ ይልቁንም ጠንካራ፣ አንድነት ያላትና የበለጸገች ሀገር ለመገንባት ሊጠቀምበት የሚችል ስትራቴጂካዊ ሀብት እንደሆነ ያምናል።

የፓርቲው የሰላም ርዕይ ዘላቂ ሰላም በደህንነት እርምጃዎች ወይም በፖለቲካ ልሂቃን መካከል በሚደረጉ ስምምነቶች ብቻ ሊረጋገጥ እንደማይችል በሚለው ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ነው። ዘላቂ ሰላም የሚጠይቀው የግጭት መንስኤዎችን መፍታት፣ በማህበረሰቦች መካከል የጠፋ መተማመንን መመለስ፣ ሀገራዊ አንድነትን ማጠናከር እና ዜጎች በታሪክ የከፋፈሏቸውን ጉዳዮች በነፃነት የሚወያዩበትን አሳታፊ መድረኮች መፍጠር ነው።

ከዚህ በፊት የነበሩ አካሄዶች ብዙ ጊዜ ልዩነቶችን በማዕከላዊነት፣ በአንድ ዓይነት ሀሳብ ማስገደድ ወይም በፖለቲካዊ ፉክክር ለመቆጣጠር ሲሞክሩ፣ የብልጽግና ፓርቲ ግን የውይይትና የመግባባት ባህልን ለማሳደግ እንደሚሰራ ያሳያል። ዓላማው ልዩነቶችን ማጥፋት ሳይሆን፣ በሰላማዊ፣ በዴሞክራሲያዊና ገንቢ መንገድ እንዲተዳደሩ የሚያስችል የፖለቲካ ሁኔታ መፍጠር ነው።

ይህንን ርዕይ በተግባር የሚያሳዩ በርካታ ሀገራዊ ተነሳሽነቶች አሉ። ከእነዚህ መካከል የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን መቋቋም በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆዩ ሀገራዊ ጥያቄዎችን በአሳታፊና በሰፊ ሂደት ለመፍታት ከተደረጉ ትልቅ ሙከራዎች አንዱ ነው። ኮሚሽኑ በታሪክ አለመግባባት የፈጠሩ ጉዳዮችን ለመወያየት ተቋቁሟል። እነዚህም የማንነት ጥያቄዎች፣ የሕገ መንግሥት አወቃቀር፣ የአስተዳደር ሥርዓት፣ የታሪክ ትርክቶች፣ የመሬት አስተዳደርና የሥልጣን ክፍፍልን ያካትታል።

የሀገራዊ ምክክሩ ሂደት ልዩ የሚያደርገው ሰፊ የህዝብ ተሳትፎን በመሠረታዊ መርህነት መውሰዱ ነው። ውይይቱን በፖለቲካ ልሂቃን ብቻ ከመገደብ ይልቅ፣ ወጣቶችን፣ ሴቶችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ የሃይማኖት መሪዎችን፣ የሲቪል ማህበራትን፣ ምሁራንን፣ የማህበረሰብ ተወካዮችንና የፖለቲካ ተዋናዮችን ለማሳተፍ ጥረት አድርጓል። በዚህም የኢትዮጵያ የወደፊት አቅጣጫ ላይ በህዝብ የተደገፈ ስምምነት ለመፍጠር ይታሰባል።

የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ መዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግም ሌላው የመንግሥት የሰላም አጀንዳ ዋና አካል ነው። ዘላቂ ሰላም ያለፉ ግጭቶችንና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በመመልከት ላይ እንደሚመሠረት በመገንዘብ፣ ፖሊሲው እውነትን ማጋለጥ፣ ተጠያቂነት፣ እርቅ፣ ካሳ እና ተቋማዊ ማሻሻያን ለማስፈጸም ያለመ ነው። ዓላማው ያለፉ ቁስሎችን ብቻ ማስታወስ ሳይሆን፣ እነዚህ ግጭቶች እንዳይደገሙ ሁኔታዎችን መፍጠርና ለተጎዱ ማህበረሰቦች ፈውስ ማምጣት ነው።

በተመሳሳይም የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት መፈረም ኢትዮጵያ ግጭቶችን በጦርነት ሳይሆን በድርድር ለመፍታት ያላትን ፍላጎት ያሳየ ታሪካዊ እርምጃ ነበር። ስምምነቱ የመንግሥትን ሰላም፣ ሀገራዊ መረጋጋትና መልሶ ግንባታን ማስቀደም ያሳያል። እንዲሁም ዘላቂ ሰላም በወታደራዊ ውጤት ብቻ ሳይሆን፣ በፖለቲካዊ ውይይት፣ በእርቅና በአካታች አስተዳደር መደገፍ እንዳለበት አስገንዝቧል።

ከእነዚህ የተቋማት እርምጃዎች ባሻገር፣ መንግሥት የህዝብ ውይይቶችን፣ የማህበረሰብ ውይይት መድረኮችንና ዜጎች በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሚሳተፉባቸውን መድረኮች አበረታቷል። እነዚህ ጥረቶች ሰላም የጦርነት አለመኖር ብቻ ሳይሆን፣ መተማመን፣ አካታችነት፣ ፍትሕና ትርጉም ያለው የፖለቲካ ተሳትፎ መኖር እንደሆነ ያሳያል።

ምናልባትም የብልጽግና ፓርቲ የሰላም ርዕይ በጣም የሚለየው የፖለቲካ ባህልን ለመለወጥ የሚሰጠው ትኩረት ነው። ለብዙ ትውልዶች በኢትዮጵያ የፖለቲካ አለመግባባቶች አንዱ ሲያሸንፍ ሌላው የሚሸነፍበት የ"ዜሮ ድምር" ፉክክር ተደርገው ይታዩ ነበር። የመደመር ፍልስፍና ይህንን አስተሳሰብ በትብብር፣ በጋራ ኃላፊነትና በጋራ ሀገር ግንባታ ለመተካት ይፈልጋል።

ስለዚህ የፓርቲው ርዕይ ከግጭት መፍታት በላይ የሚዘልቅ ነው። የኢትዮጵያ ብዝሃነት የመከፋፈል ምክንያት ሳይሆን የአንድነት መሠረት የሚሆንበት አዲስ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስምምነት ለመፍጠር ያለመ ነው። በውይይት፣ በእርቅ፣ በዴሞክራሲያዊ ተሳትፎና በጋራ ሀገራዊ ማንነት ግንባታ ላይ በማተኮር፣ የብልጽግና ፓርቲ ሰላማዊ፣ የተረጋጋና የበለጸገች ኢትዮጵያ ለመገንባት መሠረት ለማስቀመጥ ይጥራል።

ምንም እንኳን ከፍተኛ ተግዳሮቶች ቢኖሩም እና ወደ ዘላቂ ሰላም የሚደረገው ጉዞ ገና ባይጠናቀቅም፣ የመንግሥት አቀራረብ ከግጭት መቆጣጠር ወደ የግጭት መንስኤዎችን መፍታት ላይ የተመሠረተ ስትራቴጂያዊ ለውጥ እየተጓዘ መሆኑን እንደሚያሳይ ይገለጻል። የዚህ ርዕይ ስኬት በመጨረሻ የሚወሰነው የመንግሥት ተቋማት፣ የፖለቲካ ኃይሎች፣ የሲቪል ማህበራት፣ የሃይማኖት መሪዎችና መላው ህዝብ በጋራ መከባበር፣ መግባባትና ሀገራዊ እድገት ላይ በመመስረት የወደፊት ግንባታውን ለመሳተፍ ባላቸው ፍላጎት ነው።

በዚህ ረገድ፣ የሀገራዊ ምክክር ሂደት፣ የሽግግር ፍትሕ ማዕቀፍና የመደመር ሰፊ ፍልስፍና የፖሊሲ እርምጃዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ የታሪክ የግጭት ዑደቶችን ለመስበርና ለቀጣይ ትውልዶች ዘላቂ የሰላምና የብልጽግና መሠረት ለመገንባት የታለመ ሰፊ ሀገራዊ ፕሮጀክት አካል ናቸው።

አሁን በስልጣን ያለዉ መንግስት ሰላም በአጭር ጊዜ ፖለቲካዊ ስልት ሳይሆን ሁሉም የኢትዮጵያ ፖለቲካ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚ፣ የሀገር ክብር እና የግዛት አንድነት ትልሞች በሰላም ብቻ ነው ዘላቂ በሆነ መንገድ ሊሳኩ የሚችሉት ብሎ ከማመን እንደሚነሳ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተደጋጋሚ ሲገልፁት ይሰተዋላል፡፡ ሰላምን በሰላማዊ መንገድ ብቻ!!

## አደጋን ... ከገጽ 8 የዞረ

በበኩላቸው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የህሊና፣ የመተባበር እና ምንም ዓይነት ክፍያን ሳይጠይቁ እንዲሁም ጾታንና ቦታን ሳይለዩ የሚከናወን በጎ ተግባር ነው፡፡ የዘንድሮው ስራም የትራፊክ አደጋ ቅነሳን ጨምሮ በ18 ዓይነት የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዘርፎች በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በተለይም በክረምት ወቅት የዝናብና የቅዝቃዜን ፈተና ተቋቁመው የመንገድ ላይ ደህንነትን ማስጠበቅን ባህል ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ እየተከናወነ ያለው የትራፊክ ማስተናበር የበጎ ፈቃድ አገልግሎት፤ የዜጎችን ህይወትና ንብረት ከአደጋ በመታደግ ረገድ የላቀ ፋይዳ እያበረከተ ይገኛል። የበጎ ፈቃደኞች አቅመ-ደካሞችንና አይነ-ስውራንን፣ ህጻናትን መንገድ በማሻገር የትራፊክ ፍሰትን የማሳለጥ ተግባር በማህበራዊ እሴቶቻችንም የሚደገፍ ነው። የትራፊክ አደጋን ለማስቀረት ከበጎ ፈቃደኞች ጥረት ባሻገር አሽከርካሪዎች እና እግረኞች የትራፊክ ህግ በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡ ህብረተሰቡ ህግ በማክበርና የበጎ ፈቃደኞችን ጥረት በማገዝ ለሰላማዊና ጤናማ የከተማ እንቅስቃሴ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት ይኖርበታል እንላለን።

## መጽሐፍት ... ከገጽ 11 የዞረ

ልምድ እና መጻሕፍትን የመግዛት አቅም የሌላቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች የታሪኩ ተሳታፊና ባለቤት እንዲሆኑ በር መክፈቱን በጥናቱ አስፍሯል፡፡ ከዚህ አንጻር ተወዳጅና ትልቅ ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸው መጻሕፍት በፊልም መልክ እንደገና መሰራታቸው፣ በተለይ እንደ አፍሪካ ባሉ አገራት ውስጥ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ጥሩ ማሳያ ነው፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ በቀደመው ጊዜ የደራሲ ሐዲስ ዓለማየሁ "ፍቅር እስከ መቃብር" የተሰኘው ድርሰት በሬዲዮ አማካኝነት በትረካ መልክ መቅረቡ ድርሰቱ ይበልጥ እንዲወደድ ማድረጉ አይዘነጋም። ከጥቂት ዓመታት በፊት ደግሞ የደራሲ አዳም ረታ "እቴ ሜቴ የሎሚ ሽታ" ከተሰኘው የልብ ወለድ ስብስብ መጽሐፉ ውስጥ ራሱ "እቴ ሜቴ የሎሚ ሽታ"ን ወደ ፊልም ተቀይሯል። በዳይሬክተር አብርሃም ገዛኸኝ አማካኝነት ወደ ሲኒማ ስክሪን የተቀየረው ይኸው ተወዳጁ ድርሰት፣ በኢትዮጵያ የፊልም ታሪክ ውስጥ እጅግ የጎላ ስፍራ ሊሰጠው የሚገባው የአዳፕቴሽን ሙከራ ተደርጎ በብዙዎች ዘንድ ተወስዷል። ዳይሬክተሩም በዚህ ሥራው በፊልም ተመልካቾችና ድርሰቱን አስቀድመው ባነበቡ ተደራሲያን ዘንድ አድናቆትን አስገኝቶለታል፡፡

ደራሲ አዳም ረታ በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ የራሱን አሻራ ያሳረፈበት "እቴ ሜቴ የሎሚ ሽታ" የተሰኘው ድርሰቱ፣ በተለመደው መስመራዊ የታሪክ አወቃቀር (Linear Storytelling) የተደረሰ ሳይሆን፣ የተቆራረጡ በሚመስሉና እርስ በእርሳቸው የተሳሰሩ የበርካታ ገጸ-ባህሪያትን ሕይወት በዝርዝር የሚመረምር ድርሰት ነው። መጽሐፉ በዋናነት የአንዲትን ሴት የሕይወት ውጣ ውረድን፣ ማህበራዊ ጠባሳዎችን፣ ሥነ-ልቦናዊ ስብራትን እና በከተማ ኑሮ ውስጥ የሚፈጠሩ ሰብአዊ መስተጋብሮችን በጥልቅ ፍልስፍናዊ እይታ ይዳስሳል። የአዳም ረታ ብዕር በቃላት ሥዕልን የመሳል እና ረቂቅ ስሜቶችን የማጉላት ልዩ ባህሪ ስላለው፣ መጽሐፉን ለፊልም ሰሪዎች እጅግ ማራኪ እና በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ ውስብስብ ያደርገዋል።

የአዳም ረታን ሥራዎች ወደ ፊልም የመቀየር ትልቁ ፈተና፣ ደራሲው የሚጠቀምበትንና የሕይወትን ውስብስብ ትስስር የሚያሳየውን የ"ሕጽናዊነት" (ከተለያዩ ብጥስጣሽ ታሪኮች አንድ ወጥ ውበት መፍጠር) ሥነ-ጽሑፋዊ ፍልስፍና ወደ ምስል ቋንቋ መተርጎም ላይ ነው። ዳይሬክተር አብርሃም ገዛኸኝ ይህንን ከባድ ኃላፊነት በመውሰድ፣ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ረቂቅ ሀሳቦች፣ ድባቦች (Atmosphere) እና የገጸ-ባህሪያቱን ውስጣዊ ጭንቀት በካሜራ ቅንብር፣ በብርሃንና ጥላ አጠቃቀም እንዲሁም በምስል ፍሰት (Cinematography) ሕያው ለማድረግ ሞክሯል። ይህ ሙከራ ፊልም ሰሪው ለደራሲው የፈጠራ ዓለም የሰጠውን ጥልቅ ክብር እና የሲኒማ ጥበብን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ያደረገውን ቁርጠኝነት ያሳየ ነው በሚል ዳይሬክተሩ በብዙዎች ዘንድ ተደንቋል፡፡

በአጠቃላይ፣ አንድ መጽሐፍ ከወረቀት ገጾች ተነስቶ ወደ ሲኒማ አዳራሽ የሚያደርገው ጉዞ ቀላል በሆነ ወይም ቃል በቃል የመተርጎም ሂደት ሳይሆን፣ የኪነ-ጥበብ ዳግም ውልደት ነው። አዳፕቴሽን የተደራሲውን የግል ምናብ በትልቁ ስክሪን ላይ የሚፈታተን ቢሆንም፣ ታሪኮችን ከዘመንና ከባህል ገደብ አሻግሮ የብዙሃኑ የጋራ ቅርስ የማድረግ ታላቅ አቅም አለው። ሲኒማው ከመጽሐፉ ጀርባ ያለውን ማዕከላዊ ጭብጥ ሳያጠፉ በምስል ቋንቋ አዲስ ሕይወት ሲዘራበት፣ ተመልካችም 'መጽሐፉ ይበልጣል ወይስ ፊልሙ?' ከሚል መስመር ወጥቶ፣ ሁለቱንም እንደየራሳቸው የጥበብ ቋንቋ ማጣጣም ይጀምራል። ያኔ ነው እንግዲህ ብዕር እና ካሜራ ተቃቅፈው የሰውን ልጅ ምናብ በጋራ የሚያስደምሙት።

# ማስታወቂያ

ወ/ሮ/ወ/ሪት/አቶ/እነ/ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 02 ክልል ውስጥ በአለማዝ ደበበ ወርቄ በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA00007020296338l0106 በሴሪ ቁጥር C-0310030 የተመዘገበው የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካች ድርቤ ጫካ ጉዮ በቀን 06/11/2018 ዓ/ም በተፃፈ ማመልከቻ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 04 የካርታ ቁጥር ለ/ኩ/18/3/4/160817/00 የሴሪ ቁጥር 168150l የቤት ቁጥር B-393/23 የቤቱ ስፋት በሰነድ 35.77 ሜ.ካ የቤቱ አገልግሎት ለመኖርያ የሆነ ኮንዶሚኒየም ቤት ኦርጅናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ምትክ እንዳገኝ ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኃላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 13 ቀበሌ 03 በአዲሱ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 1908 በእነ አቶ በኩረ ይመኔ (6 ሰዎች) ስም የወጣው ቁጥሩ አ/12/43/3141/02 ሴሪ ቁጥር 110304 በቀን 03-13-2014 ዓ.ም ወጪ የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ዋና ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 09/11/2018 በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አራዳ ክ/ከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ካልቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ሙሉ መኮንን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 00669/1 ሴሪ ቁጥር 040528 የይዞታ ስፋት 112 ካ.ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን በቁጥር ወማ/10/26707/18 በቀን 05/10/18 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የሰራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ወ/ሮ ወ/ት አድማሱ ቸርነት ወ/ፃዲቅ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር ..... በስሜ ተመዝግቦ የተሰጠኝ የካርታ ቁጥር የካ/170917/04 ሴሪ ቁጥር 014891 ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለው የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 02 ቀበሌ 11 በአዲሱ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር የለም ኑር መስጊድ ስም የወጣው ቁጥሩ አ/ሊዝ/02/06/1078/00 ሴሪ ቁጥር 001172 በቀን 04-10-10 ዓ/ም ወጪ የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ዋና ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 16/11/2018 በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አራዳ ክ/ከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ካልቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 08 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር AA00007080l080320428 በሴሪ ቁጥር C 209993 በውድነሽ ገላ ጎንፋ ስም የተመዘገበው የቤት ባለይዞታነት እና ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ ነስሬ ናስር ሰዒድ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 ካርታ ቁጥር 01/90/59894/00 ቁጥር ይዞታ የሴሪ ቁጥሩ 020658 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

**ጉዳዩ፡- የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ።**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 13 አቶ ጥበበ ደገፋ ሀይሌ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ የቤት ቁጥር 9999/1 ባለቤትነት የይዞታ የመለያ ቁጥር AA000051311681 ሴሪ L0210559 የተሰጠበት ቀን 18/02/218 ዓ/ም የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቀን 17/11/2018 ዓ/ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ 30 ቀን ውስጥ በይዞታው መብት አለኝ የሚል እና ይህ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ያገኘ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ የይዞታ ካርታው መጥፋቱን በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣላቸው ሲሆን ካርታ መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ለአመልካቹ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 13 ቀበሌ 03 በአዲሱ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 1910 በእነ አቶ በኩረ ይመኔ (6 ሰዎች) ስም የወጣው ቁጥሩ አ/12/43/46/05/00 ሴሪ ቁጥር 110405 በቀን 13-02-2016 ዓ.ም ወጪ የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ዋና ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 09/11/2018 በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አራዳ ክ/ከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ካልቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ለመኖሪያ አገልግሎት በካርታ ቁጥር 15/284/823315/00 በሴሪ ቁጥር 07145203 በመኮንን ነገሰ ዱብሬ ተሰጥቷቸው የነበረው ማህደር ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት የገዤዋለሁ የሚል በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይገዤዋለሁ የሚል ከሌለ ሌላ ማህደር እንደሚከፈትላቸው እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 14 የቤት ቁጥር 470/471 በአቶ ኬኔ ጉርሙ ሄይ ስም የተመዘገበው 14 የቤት ቁጥር 470/471 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር 14/01/1/683 የተሰጠበት ቀን 10/08/2015 ሴሪ ቁጥር 07229768 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 17/11/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉ ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 02 ቀበሌ 11 በአዲሱ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር ኑር መስጊድ ስም የወጣው ቁጥሩ አ/01/02/01/0358 ሴሪ ቁጥር 058766 በቀን 2-7-97 ዓ/ም ወጪ የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ዋና ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 16/11/2018 በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አራዳ ክ/ከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ካልቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በ ውድነሽ ከበደ ዶሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የጋራ መኖሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000061102372637 0216 ሴሪ ቁጥሩ C061637 የሆነው ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግንቼዋለሁ የሚል ግለሰብ ይሁን ሌላ አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ በጽ/ቤታችን ቀርቦ እንዲያሳውቅ ካላቀረበ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ተዘጋጅቶ እንደምንሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ዘውዱ ጌራወርቅ ተሰማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 1 የሚገኘው ይዞታ /ቤት/ ልዩ መለያ ካርታ ቁጥር AA0000801043022340216 ሴሪ ቁጥር 041206 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 13 ቀበሌ 03 በአዲሱ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 1909 በእነ አቶ በኩረ ይመኔ (6 ሰዎች) ስም የወጣው ቁጥሩ አ/12/43/3442/02 ሴሪ ቁጥር 110303 በቀን 03-13-2014 ዓ.ም ወጪ የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ዋና ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 09/11/2018 በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመቾ ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አራዳ ክ/ከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ካልቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ ድሌቦ ጃቢር አደም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር AA000080101618830214 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካች አቶ መድፉ ሐብቴ በቀን 21/11/2018 ዓ/ም በተፃፈ ማመልከቻ የካርታ ቁጥር የካ/194960/08 የሴሪ ቁጥር 112517 የቦታው ስፋት በሰነድ 435 ሜ.ካ የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ይዞታ ኦርጅናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ምትክ እንዳገኝ ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኃላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ ብርነሽ ደበላ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 12 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር 15/102/1092/00 ሴሪ ቁጥር 020604 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 አስተዳደር ውስጥ በካርታ ቁጥር አቃ/3/2/18/124447/00 በሴሪ ቁጥር 1630799 ኬናሳ ፍቃዱ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋባቸው ስለሆነ ካርታ የያዘ ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በየውብነሽ እሸቱ ወልዴ ስም በልደታ ክ/ማ በቀድሞ ወረዳ 08 ቀበሌ 01/08 በአዲሱ ወረዳ 09 የካርታ ቁጥር ል.01/.001/193/00 ሴሪ ቁጥር 001364፣ ጠቅላላ የቦታ ስፋት 27051 ካ.ሜ፣ የቤቱ ስፋት 27.87 ካ.ሜ፣ የቦታው ስፋት በፕሮፓርሽን 26.84 ካ.ሜ ሆኖ የተመዘገበ የይዞታ ካርታ ጠፋብኝ ብለው በቀን 16/11/2018 ዓ.ም በማመልከቻ ጠይቀውናል፣ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመቾ ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳይ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 በሴሪ ቁጥር R 0221932 በይዞታ መለያ ቁጥር AA000010702491 በ አብይ አበራ አለምነህ ስም በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የተሰጣቸው የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) የጠፋብኝ በመሆኑ ምትክ ይሰጠኝ በማለት ያመለከቱ በመሆኑ ይኸው የይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) በእኔ እጅ ይገኛል ይዤዋለሁ የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በአየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 1381/2017 አንቀፅ 36(3) መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አራዳ ክፍለ ከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ቅ/ጽ/ቤት በመቅረብ እንዲያመለክት ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአራዳ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 752 በወ/ሮ ወርቋ ብሩ መገናስ ስም የተመዘገበው የካዳስተር ምዝገባ ልዩ መለያ ቁጥር AA000020600490 ሴሪ ቁጥር L036833 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 20/11/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካች ለማ ገጂ አረዶ በቀን 13/11/2018 ዓ/ም በተፃፈ ማመልከቻ በራሳቸው ስም የተመዘገበ መኖርያ ቤት የካርታ ቁጥር ቦሌ10/29/8/2/23925/00 የሴሪ ቁጥር 030820 የቦታው ስፋት በሰነድ 72 የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ኦርጅናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኃላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

አቶ አህመድ ወዳጄ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤት ቁጥር 423/ሀ በካርታ ቁጥር 27743 በስማቸው ተመዝግቦ በእጃቸው መገኘት የነበረበት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህን አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም ተቃዋሚ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ20 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎቱን የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

መቅደስ መለሰ ይርጋ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 14 ውስጥ የሚገኝ ኮንደምንየም ቤት ካርታ ቁጥር AA000080104623158004028 ሴሪ ቁጥር 0349973 በስማቸው የተመዘገበ ሰርተፍኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ብርክታዊት ምትኩ ማሞ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ካርታ ቁጥር ቦሌ12/61/5/6/188026/256453/02 ሴሪ ቁጥር 0184321 ኦርጅናል /ዋናው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በተለያየ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው 30 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት የይዞታ አገልግሎትና ማስተካከል ዳሬክቶሬት ካልቀረበ በምትኩ ሌላ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት አስተዳደር ቢሮ ቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ጂ/አይ/ኤስ/ሊዝ/ዕጣ/8134 ስም ሴሪ ቁጥር 019509 በአቶ አለማየሁ ሚናስ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸው ተደራጅቶ በመመሪያ መሰረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆንን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

# የስፖርት ማዘውተሪያዎቹ በዘመናዊው መንገድ

**በሳህሉ ብርሃኑ**

በዋና ስፖርት፣ ዓለም አቀፍ አሸናፊዎችን የምታፈራው ካናዳ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተደራሽ የሆኑ ዘመናዊ የውሃ ማሰልጠኛ ማዕከላት በመገንባት ትታወቃለች። በተመሳሳይ ኮሪያ በቴኳንዶ ስፖርት ዓለምን እንድትመራ ያስቻላት አዳጊዎች ከህፃንትነታቸው ጀምሮ ዝግጅት የሚያደርጉበት ዘመናዊ አሰራርን የሚከተሉ ማዕከላት በመዘርጋቷ ነው።

በእግር ኳስ ስፖርት ስኬታማ ከሆኑ ሀገራት መካከል እንደ ጀርመን፣ ስፔንና ፈረንሳይ ያሉ ሀገራት ታሪክም የሚያሳየው ይህንኑ ነው፡፡ እነዚህ ሀገራት ዛሬ ላይ በስፖርቱ ዓለም ስማቸው የገነነው ከዕድል ጋር ተያይዞ የመጣ ሳይሆን፣ በረጅም ጊዜ ዕቅድ፣ በተቋማዊ አደረጃጀት እና በትውልድ ቅብብሎሽ ላይ መሠረት በመጣላቸው ጭምር ነው።

በተቃራኒው እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በስፖርቱ ዓለም ስኬት የራቀቸው ሀገራት ደግሞ ለስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት፤ እንዲሁም የታዳጊ ወጣቶች የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ላይ በቂ ስራ ባለመስራታቸው ከስፖርቱ ስኬት ተቋዳሽ ሳይሆኑ ቆይተዋል፡፡

እንደ አዲስ አበባ ከዚህ ቀደም ይሰሩ የነበሩ የልማት ስራዎች ለስፖርታዊ ጉዳዮች የሚሰጡት ትኩረት ያን ያህል የተጠናከረ ባለመሆኑ የስፖርቱ እድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ ስለመምጣቱ ብዙዎች ይስማማሉ። ይሁንና በአካልና በአዕምሮ የዳበሩ ብቁ ስፖርተኞችን ለማፍራት የስፖርት መሰረተ ልማት ወሳኝ መሆኑን የተረዳችው አዲስ አበባ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ትኩረት በመስጠት ለትውልዱ እያዘጋጀች ትገኛለች፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በስፖርቱ ቤተሰብ ለሚነሱ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት ብዙ ስራዎች ስለመሰራታቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ መረጃ ያሳያል፡፡ እነዚህ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ለመዲናዋ ወጣቶች በሚኖሩበት፣ በሚማሩበትና በሚሰሩበት አካባቢ ደረጃቸውን በጠበቁ መጫወቻ ሜዳዎች ስፖርታዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ትልቅ ዕድል ፈጥሯል፡፡ ደረጃቸውን ያልጠበቁ መጫዎቻ ሜዳዎች ዛሬ ላይ ዘመናዊ የሜዳ ንጣፍ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ መቀመጫዎችና አጥር ተሰርቶላቸው ምቹ የመጫወቻ ቦታዎች ሆነዋል፡፡

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በፍትህዊነት ለመጠቀም ይረዳ ዘንድ




ፎቶ፦ ኤ አይ ጄሚናይ

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አገልግሎት አሰጣጥ በኦንላይን በመተካቱ ለስፖርቱ አፍቃሪያን እፎታን ሰጥቷል

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አስተዳደር ደንብ አዘጋጅቷል። የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በአግባቡ ለመጠቀም የወጣው ይህ ደንብ አስተዋፅኦው ከፍተኛ ስለመሆኑ የሚገልጹት ደግሞ በቢሮው የማዕከላትና ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ አስተዳደር ልማት ዳይሬክተሩ አቶ ብርሃኑ ባዩ ናቸው፡፡

ይህ ደንብ በመዲናዋ የሚገኙት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ለሌላ ዓላማ እንዳይውሉ ጥበቃና ከለላ ማድረግ፣ ከህገወጥ ወረራ በመከላከል ደህንነታቸውን መጠበቅ የሚያስችል ነው፡፡ እነዚህ ከተማውን እንዲመጥኑ ተደርገው የተሰሩት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ሁልጊዜ በመንግስት በጀት መደገፍ ስለማይችሉም የራሳቸውን በገቢ እንዲችሉ ለማድረግ ሀብት የሚያመነጩበት አሰራርም በደንቡ ላይ ተካቷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በመዲናዋ የሚገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን አገልግሎት ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስችል የኦንላይን የቦታ ማስያዣ እና የክፍያ ሲስተም በይፋ መዘርጋቱንም አስታውቋል። ይህም የመዲናዋ ስፖርት አዘውታሪዎች የት ልጫዎት? ከሚል ጥያቄ እንዲወጡና በአካባቢያቸው ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን በቀላሉ አውቀው እንዲጠቀሙ፣ ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩና በነጻነት እንዲዝናኑ ዕድል የፈጠረ ስለመሆኑ ቢሮው ይገልጻል፡፡

የቢሮው ኃላፊ አቶ አሰግደው ኃይለጊዮርጊስ እንደገለጹት አዲሱ አሰራር የተዘረጋው በከተማ አስተዳደር ካቢኔ በፀደቀው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች መተዳደሪያ ደንብ እና የክፍያ ተመን መሰረት ነው። ቀደም ሲል በነበሩ የአሰራር ክፍተቶች ምክንያት በየአካባቢው ይነሱ የነበሩ የፍትሐዊነት አጠቃቀም ቅሬታዎችን እና የአሰራር ውስብስብነቶችን በዘላቂነት ለመፍታት ታቅዶ የተጀመረ ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በፀደቀው መተዳደሪያ ደንብ እና የክፍያ ተመን ላይ ተመስርቶ የተዘረጋው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጠው ዘመናዊ አሰራር የስፖርት ቤተሰቡን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንደሚያረጋግጥ ተነግሯል፡፡

የኦንላይን ቦታ ማስያዣና የክፍያ ሲስተም የቴክኖሎጂ ሽግግር ከመሆኑ ባሻገር የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን እንደሚያረጋግጥ የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ዳዊት ትርፋ ይገልጻሉ፡፡

ቢሮው ይህንን ዘመናዊ አሰራር በስፋት ተግባራዊ ከማድረጉ አስቀድሞ በቦሌ እና በየካ ክፍለ ከተሞች በፓይለት ፕሮጀክትነት ሲተገበር መቆየቱን የገለጹት አቶ አሰግደው በሙከራ ጊዜው የተገኘው ውጤት እጅግ ስኬታማና አበረታች እንደነበር ተናግረዋል።

በዚህም መሰረት ሲስተሙ አሁን ወደ ሁሉም ክፍለ ከተሞች እና ወረዳዎች በስፋት እንዲተላለፍ ተደርጓል። በአጠቃላይ 1 ሺ 730 ማዘውተሪያዎች ወደ ዳታቤዝ የገቡ ሲሆን ማንኛውም አካል ካለበት ቦታ ሆኖ ሜዳዎችን በኦንላይን በመያዝ የመጠቀም መብቱን በግልፅ ማረጋገጥ ያስችላል። በተጨማሪም የተጠቃሚዎችን ጊዜ የሚወስዱ እና አድካሚ የሆኑ የቢሮክራሲ አሰራሮችን በማስቀረት ክፍት የሆኑ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በስርዓቱ መመልከት እንዲቻል በማድረግ ግልጽነትን ይፈጥራል።

የዝግጅት ክፍላችንም በመዲናችን የሚገኘውና በተለምዶ «ጫካ ሜዳ» በመባል ወደሚታወቀው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ተገኝቶ የአካባቢውን ወጣቶችና ተጠቃሚዎች ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ተከታትሏል። ቀደም ሲል ቦታ በመያዝ ሂደት ይፈጠሩ የነበሩ አለመግባባቶችና ረጅም ወረፋዎች ዛሬ በኦንላይን አሰራሩ መተካታቸው ለአካባቢው ስፖርት አፍቃሪዎች ትልቅ እፎይታን ሰጥቷል። አዲሱ አሰራር የመጫወቻ ሰዓትና ቦታን በግልጽ ዲጂታል መንገድ ስለሚወስን ቀደም ሲል በሜዳ ወረፋ ምክንያት በወጣቶች መካከል ይፈጠሩ የነበሩ አላስፈላጊ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ችሏል።

የአካባቢው ነዋሪ የሆነው ወጣት ቢኒያም ምንዳዬ እንደገለጸልን፣ አዲሱ የቦታ ማስያዣ ሲስተም የሜዳ አጠቃቀም ፍትሐዊነትን ማረጋገጡ ብቻ ሳይሆን፣ ወጣቶች ጊዜያቸውን ሳያባክኑ፣ በግልጽነትና በነጻነት ስፖርታዊ እንቅስቃሴያቸውን እንዲያካሂዱ ትልቅ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል።

“ቀደም ሲል ሜዳ ለማግኘት እንግልትና መገፋፋት ነበረ፤ አሁን ግን በጥቂት ደቂቃ ስልካችን ላይ ቦታችንን አስይዘን በሰዓታችን መጥተን እንጫወታለን” ሲል የተናገረው ወጣት ቢኒያም፣ አሰራሩ ግልጽነትን በማስፈን የወጣቱን ጊዜና ጉልበት ከማዳኑ ባሻገር በአካባቢው ያሉ ታዳጊዎች ሳይቀሩ በጊዜ ሰሌዳቸው መሰረት በነጻነት ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ መንገድ መክፈቱን በደስታ አብራርቷል።

በሌላ በኩል በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ታዳጊዎች፣ አካል ጉዳተኞች እና መክፈል የማይችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ከዚህ የኦንላይን ክፍያ ነጻ ሆነው ቀደም ሲል በየአካባቢው በተዘጋጀላቸው ፕሮግራም መሰረት አገልግሎቱን እንደሚያገኙ ተገልጿል። እነዚህ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የአዳጊ ወጣቶች ስልጠናን ዘመናዊ እና ዓለም አቀፍ የስልጠና መርህን በተከተለ መልኩ ለማካሄድ፣ ተተኪ ስፖርተኞችን በብዛትና በጥራት ለማፍራት በር እንደከፈቱ ቢሮው ይገልጻል፡፡

አዲስ የተዘረጋው አሰራር ከስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የሚሰበሰበውን ገቢ በአግባቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ያስችላል የተባለለት ሲሆን ክፍያው ሙሉ በሙሉ በቴሌብር (telebirr) የሚፈፀም በመሆኑ የአካል ንክኪን በማስቀረት የዘመናዊ ከተማ መገለጫ የሆነ አሰራርን እንደሚያጠናክርም ተነግሯል።

አገልግሎት ፈላጊዎች www.addissport.gov.et ድረ-ገጽን በመጠቀም የፈለጉትን ሜዳ መምረጥ፣ የሰዓት ምርጫ ማድረግ፣ በቴሌብር ክፍያ መፈጸም እና የኪውአር ኮድ (QR Code) ማረጋገጫን በመያዝ አገልግሎቱን በቀላሉ ማግኘት ይችላሉ።